አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በአዲስ አበባ መስተዳደር በተመረጡ ሶስት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ዉስጥ አመራር ትግበራ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ልእልት ግደይ

ግንቦት 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በአዲስ አበባ መስተዳደር በተመረጡ ሶስት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ዉስጥ አመራር ትግበራ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


ለተግባራዊ ሥነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር

ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY


በ


ልእልት ግደይ



ግንቦት 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በአዲስ አበባ መስተዳደር በተመረጡ ሶስት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ዉስጥ አመራር ትግበራ

በ

ልእልት ግደይ

ግንቦት 2004 ዓ.ም

**የፈተና ቦርድ አባላት**

የአማካሪ ስም ________________ ፊርማ ________________

የፈታኝ ስም ________________ ፊርማ ________________

________________ ________________

# ምስጋና

የዚህ ጥናት ዓላማ ግቡን እንዲመታ ያለምንም መታከት እና መሰላቸት ሙሉ ጊዜያቸውን ጭምር ተጠቅመው ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ጽሑፌን በጥንቃቄና በትጋት አንብበው የማሻሻያ ሃሳቦችን በመለገስ፣ በማረም፣ ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት ከጎኔ በመሆን ወደር የሌለውን ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬና መምህሬ አቶ ጌታቸው እንዳላማው የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በነበረኝ ግላዊ ችግር ምክንያት ትምህርቴን ሳላቋርጥ ይህን ጥናት እንዳከናውን ብዙ ጊዜያቸውን ሰውተው የምክር እና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ለተባበሩኝ ለዶ/ር ጌታቸው አዱኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን ወጭዎች በመሸፈን ለተባበሩኝ ለትግራይ ወጣቶች ማህበር፣ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ቢሮ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በሃሳብ እና በሞራል እየደገፉ እስከ ጥናቱ መጨረሻ ድረስ ከጎኔ ላልተለዩት ጓደኞቼ አበበች ገብሩ፣ አግዓዚት ገብሩ፣ ወርቂ ሙሳ ፣ በተለይ አማረ ተሾመ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ረቂቁን በመተየብ ለተባበረችኝ ለወሪ/ት አርማዬን አደራ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## ማውጫ

ይዘት ገፅ


ምስጋና ....................................................................................................I

ማውጫ ....................................................................................................II-IV

የሠንጠረዥ ማውጫ ....................................................................................................V

አጠቃሎ ....................................................................................................VI

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ .................................................................................... 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ .................................................................................... 3

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ .................................................................................... 3

1.4 የጥናቱ ወሰን .................................................................................... 4

ምዕራፍ ሁለት

2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት .................................................................................... 5

2.1 የክፍል ውስጥ አመራር ምንነት እና አስፈላጊነት .................................................................................... 5

2.2 የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ አስፈላጊነት .................................................................................... 8

2.3. የክፍል ውስጥ አመራር መርሆችና ትኩረቶች .................................................................................... 9

2.4. በክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦች .................................................................................... 10

2.4.1. የመምህራን የማስተማር ልምድ እና ዕድሜ .................................................................................... 10

2.4.2. የመምህራን አመለካከትና ባህሪ .................................................................................... 11

2.4.3. የመምህሩ ሥልጠና .................................................................................... 12

2.4.4. የተማሪዎች ብዛት .................................................................................... 13

2.4.5. የተማሪው ዳራዊ እውቀት .................................................................................... 13

2.4.6. የተማሪዎች ፍላጎት .................................................................................... 14

2.4.7. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ .................................................................................... 15

2.5. የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር አለባውያን .................................................................................... 15

2.5.1. ማቀድ .................................................................................... 16

2.5.2. የተግባቦት ተግባር .................................................................................... 17

2.5.3. የተቆጣጠሪነት ተግባር ........ 18
2.5.4. የአደራጅነት ተግባር ........ 19
2.5.5. የማነሳሳት ተግባር ........ 20
2.5.5.1. ውስጣዊ ተነሳሽነት ........ 22
2.5.5.2. ውጫዊ ተነሳሽነት ........ 23
2.5.6. የቅጣት ተግባር ........ 24
2.5.7. የአመራር ስጭነት ተግባር ........ 25
2.5.7.1. አምባገነን አመራር ስጭነት ........ 26
2.5.7.2. ዲሞክራሲያዊ አመራር ........ 27
2.5.7.3. ለዘብተኛ አመራር ስጭነት ........ 27
2.5.8. የገምጋሚነት ተግባር ........ 28
2.5.9. የጊዜ አጠቃቀም ተግባር ........ 28
2.5.10. ምቹ ሁኔታን መፍጠር ........ 30
2.5.11. የደንብና ሰርዓት ተግባር ........ 31
2.6. የቀደምት ጥናቶች ቅኝነት ........ 32

ምዕራፍ ሶስት

3. የአጠናን ዘዴ ........ 35
3.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 35
3.1.1. የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ ........ 35
3.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 35
3.1.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 36
3.1.4. የመምህራንና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 36
3.1.4.1. የተጠኝ መምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 36
3.1.4.2. የተጠኝ ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 37
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 37
3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 37
3.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ ........ 38
3.2.2.1. የተጠኝ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ........ 38
3.2.3. የተጠኚ መምህራን ቃለመጠይቅ ........ 39

3.3. የመረጃ አተናተን ........................................ 39
3.3.1. የክፍል ምልከታ መረጃ አተናተን ........................................ 40
3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች አተናተን ........................................ 40
3.3.3. የቃለ መጠይቅ መረጃዎች አተናተን ........................................ 41
ምዕራፍ አራት
4. የመረጃዎች ትንተና ውጤት ........................................ 42
4.1. የመረጃዎች ትንተና ........................................ 42
4.1.1. አጠቃላይ መረጃዎች ........................................ 42
4.1.1.1. የተጠኝ መምህራን ዳራ ........................................ 42
4.1.1.2. የመምህራን ስልጠና ........................................ 44
4.1.1.3. መምህራን ለሞያውና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና ፍላጎት ........................................ 44
4.1.2. የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ዳራ ........................................ 46
4.1.3. ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ........................................ 46
4.2. የመምህራን የክፍል አመራር ችሎታ ከስድስት አላባውያን አንጻር የቀረበ ትንተና ........................................ 47
4.2.1.የዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራ ........................................ 47
4.2.2.የማነሳሳት ተግባር ........................................ 51
4.2.3. የተግባቦት ተግባር ........................................ 57
4.2.4. የቅጣት ተግባር ........................................ 62
4.2.5. የመምራት ችሎታ ........................................ 67
4.2.6. ምቹ ሁኔታን መፍጠር ........................................ 73
ምዕራፍ አምስት
5. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች ........................................ 78
5.1. ማጠቃለያ ........................................ 78
5.2. የመፍትሄ ሃሳቦች ........................................ 81
ዋቢ ጽሑፎች ........................................ 84
አባሪዎች
አባሪ አንድ
አባሪ ሁለት
አባሪ ሶስት

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ማውጫ ገፅ

ሠንጠረዥ አንድ:- የረዳት ምልከታ አድራጊዎቹ ዳራዊ መግለጫ............................38

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የተጠኝ መምህራን ግላዊ መረጃ ..................................................43

ሠንጠረዥ ሶስት፡- የመምህራን ስልጠና በተመለከተ ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ..44

ሠንጠረዥ አራት፡- መምህራን ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎትና አመለካከት
በተመለከተ ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ..................................44

ሠንጠረዥ አምስት፡- የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች በፆታና በዕድሜ ........................46

ሠንጠረዥ ስድስት፡- የመምህራን የእቅድ ተግባራት ክንውን በተመለከተ
ከምልከታ የተገኘ ውጤት......................................................................48

ሠንጠረዥ ሰባት፡- የማነሳሳት ተግባራትን በተመለከተ ምልከታዊ መረጃ ........................53

ሠንጠረዥ ስምንት ፡- የማነሳሳት ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች
የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ..............................................................55

ሠንጠረዥ ዘጠኝ፡- የተግባቦት ተግባራት ክንውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ.........58

ሠንጠረዥ አስር፡- የተግባቦት ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ
መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........................................................................60

ሠንጠረዥ አስራ አንድ፡- የመምህራን የቅጣት አሰጣጥ ተግባራትን በተመለከተ ከምልከታ
የተገኘ መረጃ፡ ..................................................................63

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፡- የመምህራን የቅጣት አተገባበርን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ
መጠይቅ የተገኘ መረጃ ..........................................................64

ሠንጠረዥ አስራ ሶስት፡- የመምህራን የአመራር ሰጭነት አተገባበር በተመለከተ ምልከታዊ
መረጃ ..............................................................................68

ሠንጠረዥ አስራ አራት፡- የመምህራን አመራር ሰጪነት ችሎታ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቅ
የተገኘ መረጃ ......................................................................70

ሠንጠረዥ አስራአምስት፡- ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግራባትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ
የተገኘ መረጃ ........................................................................74

ሠንጠረዥ አስራ ስድስት፡- ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባራትን ማከናወን በተመለከተ
ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ..........................

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ቀዳሚ አላማ በአዲስ አበባ መስተዳድር በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል አመራር አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። በተጨማሪም በትግበራው ወቅት የሚያጋጥምዋቸውን ችግሮች መለየት እና የችግሮቹን መንስኤዎች በመጠቆም የመፍትሄ ሃሳቦችን ማስቀመጥ ጥናቱ ያተኮረባቸው ነጥቦች ናቸው። ይህ ጥናት የተመሠረተበት የአጠናን ዘዴ ዓይነታዊ (Qualitative Research ) ሲሆን አቀራረቡም ገላጭ ነው። ተተኳሪ መምህራኑ የተመረጡት የእጣ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ነው። በተመሳሳይ መልኩ የፅሑፍ መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች ናሙና የተወሰደው በእጣ ናሙና ዘዴ ሲሆን መጠይቁን በሚገባ ሞልተው የመለሱት 150 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ከዚህም ባሻገር መረጃዎቹ የሦስትዮሻዊ ጎነዮሻዊ መርህን የተከተለ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል። በቀረበው መረጃ መሠረትም በአዲስ አበባ መስተዳድር በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከተመረጡት ስድስት የክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን አንፃር በተግባቦት ተግባራት ጥሩ የአተገባበር ክህሎት ያላቸው ሲሆን በአምስቱ ማለትም ተነሳሽነትን በመፍጠር ተግባር፣ በቅጣት አሰጣጥ ተግባር፣ በእቅድ አተገባበር፣ በአመራር ስጪነት ተግባርና ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ተግባር አንፃር የአተገባበር ክህሎታቸው ደግሞ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደትን ውጤታማ ለማድረግ እንደመነሻ በመሆን ከሚያገለግሉት እና በትምህርቱ ሂደት የተፈለገውን ውጤት ለማምጣት ከሚያስችሉት መንገዶች ውስጥ አንዱ የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎት ነው። እንደ Harmar (1991:235) ገለፃ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ መምህራን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ያደረግዋቸውን እንቅስቃሴዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ በማረጋገጥ ረገድ እገዛ ያደርጋል። ይህም የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ (ክህሎት) መኖር አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል። በተጨማሪም Gebhard (1996) የመማር ማስተማር ሂደቱ ትርጉም የሚሰጥ እና ተማሪዎችን በቀጥታ በትምህርቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ መምህራን ተገቢ የሆነ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ሊኖራቸው እንደሚገባ ገልፀዋል። ከዚህም ሀሳብ የምንረዳው በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እና ውጤታማ እንዲሆኑ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎታቸውን ማዳበር እንደሚገባቸው ነው።

በተጨማሪም የክፍል ውስጥ አመራር ብቃት ከተማሪዎች የመጨረሻ ውጤት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳለው እና ከመማር ማስተማር ሂደት ጋር በተያያዘ አያሌ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይታመናል። ከዚህም ጋር በተያያዘ Belln (1992) Hawline and Roztaitize(1984)ን ጠቅሶ እንደገለፀው ጥሩ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ በአዎንታዊ ጎኑ ከተማሪዎች ውጤት ጋር ግንኙነት እንዳለው እና ተማሪዎች መልመጃዎችን በመስራት በኩል ያላቸውን ተሳትፎ በመጨመር (በማሳደግ) ረገድ በቀላል የማይገመት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በሌላም እይታ Edward and Galloway (1992) እንደገለፁት በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ አጠቃላይ ተማሪዎች ሁሉንም የመማር ማስተማር እንቅስቃሴያቸውን በሙሉ ተከታትለው ውጤታማ በሆነ መልኩ ማስተማር ቀርቶ የተወሰኑ ቡድኖችንም (ጥቂት ቁጥር ያላቸው ተማሪዎችን) በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በሚገባ ተከታትሎ ማስተማር ቀላል ነው ብሎ ማሰብ ያዳግታል። ለምን ቢባል መምህሩ ትምህርቱን በተገቢው መንገድ ለማካሄድ በሚሞክርበት ጊዜ በርካታ ችግሮች ያጋጥሙታልና።

ስለዚህ መምህራን አንድን ትምህርት ከማስተማራቸው በፊት ሆነ እያስተማሩ እያለ በክፍል ውስጥ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ችግሮቹ እንዳይከሰቱ ለመከላከል እና ከተከሰቱም በኋላ መፍትሔ ሰጥቶ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ አስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ለአንድ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት መሳካት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ችሎታ ደግሞ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን እንቅስቃሴዎች በሙሉ የሚያጠቃልል በመሆኑ ብዙ መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ እንደሚቸገሩ ለምሳሌ ሒሩት ካሳ (1997)፣ አንተነህ ውዱ (1998) ፣ አበበ እስጢፋኖስ (2001) በጥናቶቻቸው ጠቁመዋል፡፡

እስከ አሁን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታን በተመለከተ የተሰሩ የተወሰኑ ጥናታዊ ጽሑፎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ጥናታዊ ጽሑፎች በአብዛኛው የሚያተኩሩት በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል በሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ በተመለከተ ያላቸውን ልዩነት ማሳየት ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም በሴት እና በወንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል ያለውን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ልዩነት ከክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን አንፃር አተገባበራቸው በመገምገም ከሴት እና ከወንድ መምህራን የተሻለ የአተገባበር ችሎታ ያለውን በመለየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንተነህ ውዱ (1998)፣ ሂሩት ካሳው (1997)፣ አበበ እስጢፋኖስ (2001) ተጠቃሽ ናቸው ፡፡ አሁን የተጠናው ጥናት ግን ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ጥናቶች በተለየ መልኩ ትኩረት የሚያደርገው በአዲስ አበባ መስተዳደር በተመረጡ 3 የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ከተመረጡ 6 አላባውያን አንፃር አተገባበራቸውን መፈተሽ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት እንዲደረግ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች 3 ሲሆኑ እነሱም፡-

1. ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከተመረጡ የክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን አንጻር የመምህራኑን አተገባበር ለመፈተሽ ምንም አይነት ጥናት አለመደረጉ፣
2. ይህ ጥናት ይዟቸው የተነሳ ዓላማዎች ከዚህ ቀደም በተጠኑት ጥናቶች ላይ በስፋት ታይተው አለመጠናታቸው፣
3. ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከተመረጡት ስድስት አላባውያን አንጻር አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ሲባል

ይህን ጥናት እንዲጠና አነሳሽ ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ያደርጋል፣

- በአሁኑ ጊዜ በመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከስድስቱ የክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን አንፃር አተገባበራቸው ምን ይመስላል?
- የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ እንዳይሆን በክፍል ውስጥ አመራር አለባውያን ትግበራ ወቅት ጎልተው የሚታዩ ችግሮች እና መንስኤዎቻቸው ምንድናቸው? ለሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ላይ የሚያተኩር ነው።

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ መስተዳድር በተመረጡት ሶስት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር አተገባበራቸው መፈተሽ ሲሆን የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች አሉት።

1. የመምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎት ከተመረጡት ስድስት አላባውያን አንፃር አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል መፈተሽ፣
2. መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር አለባውያንን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ሚያጋጥሟቸውን ዋና ዋና ችግሮች መለየት፣
3. የችግሮቹ ምንጮች (መንስኤዎች) ምን ምን እንደሆኑ መለየት፣
4. ችግሮቹን መሰረት ያደረጉ መፍትሔዎች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ማስቀመጥ፣

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

እንደ Belln (1992፣124) ገለፃ ስኬታማ የሆነ የመማር ማስተማር ክንውን አስተማሪው በሚያስተምረው የትምህርት አይነት እውቀት ብቻ የተገደበ ሳይሆን የመምህሩን የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎት መዳበር ጭምር የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም የሚሰጠው ትምህርት ከታቀደለት ግብ ላይ የሚደርሰው ምቹ የሆነ የመማሪያ ድባብ ሲፈጠር ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎት መዳበር ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ አለው። በዚህም መሰረት ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል።

1. አጥኚዋም ሆነች ሌሎች መምህራን ስለ ክፍል ውስጥ አመራር ትግበራ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳል።

2. ጥናቱ በተደረገባቸው ትምህርት ቤቶች መምህራን እና የአስተዳደሩ ሰራተኞች ከጥናቱ የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ አወያይቶ ስለ ክፍል ውስጥ አመራር ትግበራ ግንዛቤ ለመስጠት ይረዳል፡፡
3. መምህራን የክፍል አመራር አላባውያን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮችን እንዲረዱ እና የክፍል አመራር ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ያሳያል፡፡
4. ውጤታማ እና ሳቢ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ለመፍጠር የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ አመራር ብልሃቶችን ለመምህራን፣ ላስተዳደር ሰራተኞች ለማሳወቅ ይረዳል፡፡
5. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ትግበራ ላይ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መንስዔዎችን ለመለየት እና የመፍትሔ አቅጣጫ ለማቅረብ ይረዳል፡፡
6. ተመሳሳይ ችግር ይዘው ጥናት ለማካሄድ ለሚነሱ እንደመነሻ ሀሳብ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን /ክልል/

ይህ ጥናት የክፍል ውስጥ አመራር ክንዋኔዎችን ከክፍል አመራር አላባውያን ውስጥ፡-

1. የመምህራኑ የእቅድ ዝግጅትና በእቅድ የተመሰረተ ትምህርት ትግበራ፣
2. በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ተሳታፊ ለማድረግ የመምህራኑ የማነሳሳት ትግበራ፣
3. በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን የተግባቦት ትግበራ፣
4. ለማንኛቸውም ትምህርታዊ ተግባራት የመምህራኑ አመራር ሰጭነት ትግበራ፣
5. ተማሪዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ሲያውኩ የሚችሉ ተግባራት ሲያከናውኑ የመምህራኑ የቅጣት አሰጣጥ ትግበራ ፣
6. የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አንጻር የመምህራኑ አተገባበር በመመልከት በትግበራው ወቅት የሚታዩ ችግሮች እና መንስኤዎች በመመርመር ላይ ያተኩራል፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ ሁለት ለጠቅላላ እውቀት ይረዱ ዘንድ የተጠቀሱትን የክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን ማለትም የተቆጣጣሪነት ተግባር፣ የአደራጅነት ተግባር፣ የገምጋሚነት ተግባር፣ የጊዜ አጠቃቀም ተግባር፣ የደንብና ሥርዓት ተግባር በዚህ ጥናት ውስጥ አልተዳሰሱም፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1. የክፍል ውስጥ አመራር ምንነት እና አስፈላጊነት

የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ሲባል በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥሩ መንገድ እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ይህም ማለት የክፍሉ አደረጃጀትን፣ ተማሪዎች መቆጣጠርን፣ በትምህርቱ ዙሪያ በቂ የሆነ ዝግጅት ማድረግን፣ ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚረዱ አጋዥ መረጃ መሳሪያዎችንና ተገቢውን የማስተማሪያ ዘዴ መርጦ መጠቀምን፣ የተማሪውን የተስተምህሮ ስልት ማደራጀትን እና ማቀናጀትን አካቶ ይይዛል (Clark 1986፣94)፡፡

እንደ Arends (1997) ገለጻ የክፍል ውስጥ አመራር ሲባል የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ መተጋገዝ (መረዳዳት) ከመጨመር ባሻገር የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያውኩ ነገሮች ለመቀነስ መምህሩ ተግባራዊ የሚያደርገውን (እያደረገ ያለውን) የክፍል አደረጃጀትና አወቃቀር የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም እንደምሁሩ ገለጻ ለመማር ማስተማሩ ስኬት የክፍል ውስጥ አመራር በራሱ ብቻውን በቂ ነው ተብሎ ባይታሰብም የመምህሩ የመሪነት ሚና ግን ለመማር ማስተማሩ ስኬት አንዱ አካል ነው፡፡ ይህም ሀሳብ የክፍል ውስጥ አመራር ከሌሎች የመማር ማስተማር ተግባሮች ተነጥሎ መታየት እንደሌለበት ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ መምህሩ የትምህርት እቅድ ያወጣል፣ ያወጣውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን ምቹ የሆነ የመማሪያ ክፍል በመፍጠር የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ማድረግ አለበት፡፡

እንደ Elliott (2000) ገለጻ የክፍል ውስጥ አመራር እንደ ደንብና ቅድመ ሁኔታ በመጠቀም ትዕዛዝ ለመስጠትና ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ይህ ማለት የክፍል ውስጥ አመራር የክፍል ውስጥ ሥነ ሰርዓትን ማስከበር ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዴት ባህሪያቸውን ማንፀባረቅ እንዳለባቸው፣ ግዴታቸውን እንዴት መወጣት እንዳለባቸው፣ ከጓደኞቻቸው እና ከቡድን አጋሮቻቸው ጋር እንዴት መስራት እንዳለባቸው ወዘተ. በአጠቃላይ ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ ለማሳየት የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ የጎላ ድርሻ አለው፡፡

እንደ Wolfagng (2005) ገለጻ የክፍል ውስጥ አመራር ሲባል የተማሪዎችን አቀማመጥ፣ መርጃ መሣሪያዎች፣ የወንበሮችና ጠረጴዛዎች አደረጃጀት እና አጠቃላይ የክፍሉን እንቅስቃሴ አካቶ የያዘ ነው። በተጨማሪም የክፍል ውስጥ አመራር ማለት የተማሪዎችን አደረጃጀት፣ አካባቢያዊ ሁኔታ (Physical Environment)፣ ተቋማዊ ግብአት ወዘተ. አሟልቶ ለመማር ማስተማሩ ስኬት ቅድሚያ የሚሰጥ ነው።

በሌላም በኩል Belln (1992፣124) Laseelin (1981)ን ጠቅሰው እንደገለጹት የክፍል ውስጥ አመራር ጥበብም ሳይንስም ነው። ጥበባዊ ሲባል መምህሩ የራሱን ተፈጥሮአዊ ዕውቀት እና ክህሎት በመጠቀም ክፍሉን ለመቆጣጠር የሚሞክርበት ስልት ሲሆን ሳይንሳዊ ሲባል ደግሞ የተለያዩ ምሁራን የጠቀሷቸውን የክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን ተጠቅመው ተግባራዊ በማድረግ የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ለማድረግ የሚረዳ ዘዴ ነው።

እንደ Moore (1982፣132-133) ገለጻ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር የጊዜ አጠቃቀምን፣ የተስተምህሮ ፅንስ ሃሳብን፣ ግላዊ አመለካከትን፣ ውሳኔ አሰጣጥን፣ አመራርን፣ ማቀነባበርን፣ ማደራጀትን፣ ቅደም ተከተል ማስያዘን ወዘተ. አካትቶ የያዘ ነው። እነዚህም በዝርዝር እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

- ሰዓትን በአግባቡ ከፋፍሎ መጠቀም፣
- የመማር ጥቅምን ጠንቅቆ ማወቅና አግባብነት ያለው ትምህርት በጥሩ የአቀራረብ ስልት ተግባራዊ ማድረግ፣
- የተማሪውን ችግር እና አጠቃላይ ባህሪ ተመልክቶ አቀራረብን ማስተካከል፤
- ውሳኔ አሰጣጥና አመራርን ማወቅ፣
- በክፍል ውስጥ የተለያየ ችግር ያሉባቸውን ተማሪዎች/ የመስማት፣ የማየት የስነ ልቦና ችግር..../ ችግራቸውን ተረድቶ ልዩ እገዛ በማድረግ ማስተናገድ፣
- የአጭርና የረጅም ጊዜ፣ የመንፈቅ ዓመትና የዓመት እቅድ አዘጋጅቶ መቅረብ መቻል፣
- የሥነ ምግባር ጉድለት ያለባቸውን ተማሪዎች በተገቢው ጊዜ ተገቢውን እርምጃ ወስዶ ማስተካከል፣
- በስተመጨረሻም ውጤታማ ባለሙያ የመማሪያ ክፍሉን ሁኔታ ተከታታይ ምዘና በመስጠትና በመገምገም ምጋቤ ምላሽ መስጠት የሚሉትን ዝርዝር ጉዳዮችን ያካትታል (Moore 1982፣132-133)።

በአጠቃላይ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ዝርዝር ጉዳዮች ተግባራዊ በማድረግ ችግሮችን በመሉ አስወግዶ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያወኩ ነገሮች ከመቀነስ አንፃር ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ድባብ ለመፍጠር መምህራን ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በተጨማሪም የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ባግባቡ ካልተከናወነ ቀጥሎ ምን ይከተላል? አጥፊ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ቢኖሩስ? አንድ መምህር እንዴት እና መቼ ነው የሥነ ሥርዓት ደንብ መተግበር ያለበት? የሚሉትን ጉዳዮች አውቆ በተገቢው መንገድ ማከናወን አለበት።

እንደ Jarolimek and Foster (1997፣116) ገለጻ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ሲባል የተማሪውን ጉድለት ከማስተካከል ጎን ለጎን ሌላም የተሻለ ሥራ ማከናወንን ያካትታል። የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች በህብረት የመኖር ልምድን የሚያዳብሩበት ቤተ-ሙከራ ከመሆኑ ባሻገር ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ለተወሰኑ ወራት በሚቆዩበት ጊዜ ስለራሳቸው የሚያውቁበት እና የሚረዱበት ቦታ ነው። ስለዚህ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር በራሱ እንደ ግብ ታቅዶ የሚከናወን ሳይሆን በመምህራንና በተማሪዎች መካከል በሚኖረው መስተጋብር የሚከናወንን ሂደት አካትቶ የያዘ ነው። ይህም ማለት ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የሚያሰሟቸውን አዋኪ ድምፆች እና የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር፣ የተማሪዎችን ባህሪ ማረቅ እና ማስተካከል፣ ሽልማት አሊያም ማነቃቂያ መስጠትንና መቅጣትን ሁሉ ያጠቃልላል። መምህራን ለማስተማር ከመዘጋጀታቸው በፊት የተማሪዎችን ፍቅር ለማግኘት መጣር አለባቸው። ይህም የሚሆነው በሥራቸው ጥሩ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ማለትም ክፍሉን በማደራጀት፣ በማስተዳደር፣ ጥሩ አመራር በመስጠት እና ፕሮግራም በማውጣት ሲታገዝ ነው (Jarolimek and Foster 1997፣117)::

በአጠቃላይ ስለክፍል ውስጥ አመራር ምንነት ቀደም ሲል የተለያዩ ምሁራን ካነሷቸው ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ለቋንቋ ትምህርቱ የመማር ማስተማር ክዋኔ አመቺ ሁኔታን መፍጠር መቻል ነው። ይኸውም የተማሪዎችን ችግር መፍታት፣ የተማሪዎችን ስራ መቆጣጠር መገምገም፣ ለበለጠ ስራ ማነሳሳት፣ ምጋቤምላሽ መስጠት፣ የክፍል ውስጥ ደንቦች በማዘጋጀት ማስፈፅም፣ ተማሪዎችን ለተግባራዊ ስራ (task) ማዘጋጀት፤ የተማሪዎችን ፍላጎት እና ስሜታቸውን መጠበቅ ወዘተ. ያጠቃልላል።

## 2.2. የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ አስፈላጊነት

የመማሪያ ክፍል መምህራን ሁሉንም የትምህርት ተግባራቸውን የሚያከናውኑበት የመጨረሻ ቦታቸው ነው፡፡ በትምህርት ተግባሮች /Educational efforts/ ውስጥ መምህሩ ትምህርቱን በማስተማር ተግባር (ስራ) ላይ ብቻ አይወሰንም፡፡ የትምህርቱን ተግባር ቀላል እና አዝናኝ ሊያደርግ በሚችልበት ተግባር ላይም ይሰማራል እንጂ፡፡

የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ የመማር ማስተማሩን ሂደት ምቹና ውጤታማ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህሩ የትምህርቱን አሰጣጥ ሂደት ግቡን የመታ እንዲሆን ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፡፡ ለምን ቢባል የመማር ማስተማሩን ሂደት በመምህሩ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ የተወሰነ ስለሆነ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ Belln (1992፣124) ጥሩ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ከተማሪዎች ውጤት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ በመሆኑም የመምህሩ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ በተማሪዎች ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ፡፡

እንደ Montague (1987፣254) ገለፃ በክፍል ውስጥ አመራር የክፍል መመሪያ ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ፣ለመምህራኖች አስፈላጊውንና ለማስተማር አመቺ የሆነውን ድባብ ለመፍጠር ይረዳቸዋል፡፡ ይህ ማለት የክፍል ውስጥ መመሪያ ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ በክፍል ውስጥ ውጤታማ የሆነ የአመራር ዘዴን ለመጠቀም፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማዳበር፣ ተማሪዎች በጥልቀት እንዲሰሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ተግባር በተቃራኒው ደካማ ከሆነ ተማሪዎች ከተፈለገው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲርቁና ተገቢ ያልሆነ ባህሪ እንዲያንፀባርቁ ያደርጋቸዋል፡፡

የመማር ማስተማሩ ሂደት እስካልተገታ ድረስ በየትኛውም የክፍል ደረጃ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ የላቀ ድርሻ አለው፡፡ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ በሌለበት ሁኔታ ትምህርቱን በተሳካ መንገድ ማከናወን ቀርቶ ‹‹ሀ›› ተብሎ ትምህርቱን እንዴት ማስተማር መጀመር እንዳለበት ማወቁ አስቸጋሪ ነው፡፡ ተማሪዎች የተፈለገውን የቋንቋ ክህሎትና እውቀት ተቀራራቢነት ባለው መልኩ ያገኙ ዘንድ መምህሩ ከትምህርት እውቀት በተጨማሪ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ Harmer (1991) መምህሩ በሚያስተምረው ትምህርት ውጤታማ መሆኑን እና የሚያከናውናቸውን እንቅስቃሴዎች ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጾዋል፡፡

እንደ Belln (1992፣124) ገለጻ ከውጤታማ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ትግበራ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ግምታዊ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ ክፍሉን መቆጣጠር እንደሚቻል ያስረዳሉ።

- መምህሩ የመጨረሻው ባለሥልጣንና መመሪያ ሰጭ አካል ነው፣
- ጥሩ የክፍል ውስጥ አመራር ከቃላዊ መመሪያ ትግበራዎች ጋር የተዛመደ ነው፣
- የክፍል ውስጥ አመራር ችግሮች እንዳይከሰቱ መከላከል ላይ እንጂ ለችግሮች አፃፋ መስጠት ላይ ማተኮር የለበትም፣
- በስፋት ሲታይ የክፍል ውስጥ አመራር የመከላከልና የማስተካከልን ክንዋኔን ያጠቃልላል፣

በአጠቃላይ መምህሩ ለስራ ከተፈለገው ጉዳይ ጋር አጣጥሞ የክፍል ውስጥ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ የማይችል ከሆነ የሚያስተምረው ትምህርት ትርጉም ሳይኖረው ይችላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ Harmer (1991) በእጅጉ ተቀባይነት ያላቸውን ሥራዎች መምህሩ በተገቢው መንገድ ካላደራጃቸው ጠቃሚ ላይሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም በአዋኪ ተግባራት ላይ ቁጥጥር የማያደርግ ከሆነ የክፍሉ ፅጥታ ይበላሻል። ይህ ከሆነ ደግሞ የታቀዱት አላማዎች ግባቸውን አይመቱም፤ ተማሪዎች ከትምህርቱ ማግኘት ያለባቸውን እውቀት ሳይቀስሙ የመማር ማስተማሩ ሂደት ይቋጫል።

## 2.3. የክፍል ውስጥ አመራር መርሆችና ትኩረቶች

አንድ መምህር ስኬታማ የሆነ (ግቡን የመታ) የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታን ለመፍጠር ለሚያከናውናቸው ማናቸውም ተግባራት ጥንስስ ሀሳብ በመሆን ከሚያገለግሉት እና የጥቅልነት ባህሪ ከሚታይባቸው የክፍል ውስጥ አመራር መርሆች ጋር ራሱን ማስተዋወቅ እና ማዋሃድ ይኖርበታል። ለምን ቢባል ሁሉንም የክፍል ውስጥ አመራር አላባውያንን ተግባራዊ ለማድረግ እንደ መነሻ ጽንሰ ሀሳብ በመሆን ያገለግላሉ ተብለው ስለሚታሰቡ ነው።እንደ Good and Brophy (1987፡132) ገለጻ የክፍል ውስጥ አመራር አጠቃላይ መርሆች ቀጥለው የተጠቀሱት ናቸው።

- ተማሪዎቹ የሚሰጣቸውን ትምህርታዊ ተግባራት፣ መመሪያዎች ተከታትሎ መረዳታቸውንና መቀበላቸውን የመረዳት መርህ፣

- የተማሪዎችን መሻት(ፍላጎት) ያገናዘበ ይዘት በማቅረብ ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ የሥነ ምግባር ጉድለቶችን ለመቀነስ የሚያስችል መርህ፣
- በተማሪዎች ላይ በሚስተዋሉ አላስፈላጊ ባህሪያት በመቆጣጠር ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ውጤታማ የሆነ የመማሪያ ድባብ ለመፍጠር በሚያስችሉ ተግባራት የማተኮር መርህ፣
- የመምህሩ አላማ መሆን ያለበት ተማሪዎቹ እራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩበትን መንገድ እንዲያዳብሩ በማድረግ እንጂ ሁሉን ነገር እኔ ልቆጣጠር ማለት የለበትም የሚሉ መርሆች ናቸው፡፡

የክፍል ውስጥ አመራር ትኩረቶች በተመለከተ Good and Brophy (1997፡130) Gettinger (1988)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ስኬታማ የሆነ የክፍል ውስጥ አመራር የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባሮችን ማእከል ያደረገ ነው ፡፡

- የከፍል ውስጥ አመራር ችግሮች እንዳይከሰቱ መከላከል ላይ እንጂ አፃፉ ላይ አያተኩርም፣
- የክፍል ውስጥ አመራር ዘዴዎችን በማቀናጀት ተማሪዎቹ በትምህርቱ ቀጥታ የሚሳተፉበትንና ውጤታማ የሚሆኑበትን መንገድ ያመቻቻል፣ ያበረታታል፣
- የአንድን ተማሪ ባህሪ ከማጥናት ይልቅ ክፍሉን እንደ አንድ ቡድን መምራት ወይም መቆጣጠር ላይ ማተኮር አለበት፡፡

ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው አንድ መምህር የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታው ወይም ዘዴው የተሳካ ይሆንለት ዘንድ በክፍል ውስጥ የሚተገብራቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት ከክፍል ውስጥ አመራር መርሆች ጋር እያዛመደ፣ እያዋሃደ ተግባር ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፡፡

## 2.4. በክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

### 2.4.1. የመምህራን የማስተማር ልምድ እና ዕድሜ

አዳዲስ መምህራን ጥሩ የትምህርት ይዘት መርጦ በማሰተማሩ እና የማስተማሪያ መጻሕፍትን በመምረጡ ረገድ ጥሩ ቢሆኑም በክፍል ውስጥ አመራር ችሎታቸው ላይ ግን ችግር እንዳለባቸው Moore (1982፣131) ገልጸዋል፡፡ ያለክፍል ውስጥ አመራር ብቃት መምህራን



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በማስተማር ሂደት ላይ ውጤታማ አይሆኑም። Moore (1982) እንደምሳሌ ያቀረቡትን የአንድን መምህር ሁነት እንመልከት አንድ መምህር የማስተማር ብቃት እንዳለው በከፍተኛ ተቋም ተመስክሮለት በአንድ ትምህርት ቤት ተቀጥሮ ማስተማር ጀመረ። እንደጀመረም ብዙ ሳይቆይ ችግሮች መታየት ጀመሩ። ይህም ሁኔታ በክፍል ውስጥ ጫጫታና ሁካታን አስከተለ፤ የችግሩ መንስኤም መምህሩ የክፍል አመራር ችሎታ አለማዳበሩ ነበር። እንደ Doyle (1988፣ 441) እና Arends (1997፣5) ገለፃ ብዙ የማስተማር ልምድ ያላቸውና መካከለኛ ልምድ ያላቸው መመህራን የተሻለ የክፍል አደረጃጀት፣ ምቹ የሆነ የመማር ማስተማር ሁኔታን የመፍጠር፣ የተቆጣጠሪነት ተግባር የመፈፀም ብቃታቸው፤ ልምድ ከሌላቸው ወጣት መምህራን የተሻሉ ናቸው።

Cruic Kshank, (1999፣4) Borness (1987)ን በመጥቀስ የማስተማር ልምድ እና እድሜ በክፍል አመራር ችሎታ ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅእኖ እንደሚያሳድሩ ገልጸዋል። የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን ክፍልን በአግባቡ የመምራት ብቃታቸው ከፍተኛ ሲሆን ልምድ የሌላቸው መምህራን ግን ክፍሉን በመምራት ተግባር ችግር ይገጥማቸዋል። በእርግጥ አዳዲስ መምህራን ለለውጥ የሚዘጋጁና በቀላሉ የሚለወጡ ቢሆኑም ቶሎ ሥር የሰደደና መሰረት የያዘ ለውጥ ፈጥኖ ለማምጣት ግን ይቸገራሉ። ልምድ የሌላቸው መምህራን ‹‹አይ በምድር ላይ ያለህ ሰው›› እንዳለው ፈረሰኛ ገና ከመጀመሪያው ራሳቸውን የተሻሉና ብቁ አድርገው ስለሚቆጥሩ ገብተው ሲሞክሩት ግን ችግር ሲገጥማቸው ይታያሉ። ከዚህም በተጨማሪ እንደ Bress (2000፣28) ገለጻ መምህራን የማስተማር ልምዳቸው እየጨመረ በሄደ መጠን ክፍልን በአግባቡ መምራት ከመቻላቸውም በላይ በመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘግባሉ።

### 2.4.2. የመምህራን አመለካከትና ባህሪ

የመምህራን ባህሪይ እና አመለካከት በክፍል ውስጥ አመራር ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት ተላውጦዎች አንዱ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ለክፍል ውስጥ የሥነ ሥርዓት ችግር መፈጠር እንደ ዋነኛ መንስኤ ሊወሰዱ እንደሚችሉ  የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ። ለምሳሌ እንደ Harmer (1991) ገለጻ የመምህራን ባህሪ (ፀባይ) በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል  ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል እና በሚማሩት ትምህርት ላይ የጥላቻ ስሜትን እንዲያሳዩ አለያም በጥቅሉ ትምህርቱን እንዲጠሉት ሊያደርግ እንደሚችል ያስረዳሉ። ይህም

ማለት አንድ መምህር ለሚያስተምረው የትምህርት አይነት፣ ለሙያው ያለው አመለካከት፣ ለተማሪዎች ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ፣ ለተማሪዎቹ የሚኖረው ፍቅር እና አክብሮት ወዘተ. በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ በአሉታዊ አለያም በአዎንታዊ ጎኑ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑን ነው፡፡

በሌላም በኩል መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚኖራቸው አመለካከት አዎንታዊ (ቀና) ካልሆነ እና ተማሪዎቹን እንዲሁ በውሃ ቀጠነ የሚያስፈራሯቸው እና የሚደበድብዋቸው ከሆነ ተማሪዎች እያደር ትምህርትን የመጥላት ስሜት ያድርባቸዋል፡፡ በቀላሉ የሚጎዱ (ቶሎ የሚከፋቸው) ተማሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ Harmer (1991) መምህራን ተማሪዎቻቸውን አላስፈላጊ ቅጣት በመቅጣት ለማስፈራራት (ለማሸማቀቅ) የሚሞክሩ ከሆነ፤ የተለያዩ መልመጃዎችን በሚሰሩበት ጊዜ የማያበረታቷቸው ከሆነ አላስፈላጊ ባህሪዎች በተማሪዎቹ ላይ ሊንፀባረቁ ወይም ጎለተው ሊታዩ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው መምህራን ተማሪዎችን ማስፈራራት፣ ማደናገጥ፣ ማስጨነቅ አስፈላጊ አለመሆኑን ተገንዝበው  አስፈላጊ ነው የሚባለውን ምክርና ድጋፍ በመስጠት አዎንታዊ ባህሪን እንዲያጎለብቱ ማድረግ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም ምክርን በመለገስ፣ ፍቅር በመስጠት፣ እንደጓደኛና እንደ አንድ የራስ የሆነ ነገር በመቁጥር ወዘተ. ነገሮችን በማመቻቸት የተማሪዎችን አዎንታዊ  አመለካከት ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡ መምህር በራስ የመተማመን ስሜት ሊያድርበት እና በሚያስተምረውም ትምህርት በቂ እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ በጥቅሉ መምህር በሁሉም ነገር እራሱን በተሻለ ደረጃ በማዘጋጀት በራስ የመተማመን ስሜትን አዳብሮ የተማሪዎችን ደህንነት መቆጣጠር ይችላል፡፡

### 2.4.3. የመምህሩ ሥልጠና

በመምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ተላውጦዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ጉዳይ  የመምህሩ የሥልጠና ሁኔታ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍል ውስጥ በ Evertson (1983) የተጠናው ጥናት በመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ሙያ የሰለጠኑ መምህራን በሃይል በመቆጣጠር ክፍልን ከሚመሩ መምህራን የተሻለ ችሎታ አላቸው፡፡ በተጨማሪም ስልጠና የወሰዱ መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ችሎታቸው የተሻለ ለውጥ እንዳሳዩ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ለመምህራን ስለ መሰረታዊ የክፍል

ውስጥ አመራር አላባውያን በተመለከተ ትምህርት ወይም ሥልጠና መስጠቱ የተሻለ ሙያዊ ብቃት ያጎናጽፋቸዋል (Arends 1997፣177)።

### 2.4.4. የተማሪዎች ብዛት (Class Size)

በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ የብዙ ተማሪዎች መኖር በክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል። በዚህም ሳቢያ በትምህርት ጥራት ላይ ችግር ይፈጠራል። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ Deighton (1971) እንደገለጹት በቁጥር ብዛት ያላቸው ተማሪዎች በሚኖሩበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋ እኩል የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ እድል ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ ተአማኒነት አይኖረውም፣ ለምን ቢባል መምህሩ የእያንዳንዱ ተማሪ የሥራ ውጤት እየተከታተለ ማየትና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ይቸገራል። ስለዚህ በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር ከመጠን በላይ መብዛቱ ለመምህርም ሆነ ለተማሪዎች አመቺ ሊሆን አይችልም።

ቀደም ሲል ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ በተመለከተ Edward and Galloway (1992) በአንድ ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸውን ተማሪዎች ለማስተማርም ሆነ ለመቆጣጠር አስቻጋሪ ነው። ትምህርቱ ውጤታማ ሊሆን የሚችለውም አነስተኛ የተማሪ ቁጥር ባለበት ክፍል ውስጥ ሲካሄድ ነው። ለምን ቢባልም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል አመርቂ እና ገንቢ የሆነ አስተያየት ለመስጠት ያለው ጊዜ የተሻለ መሆኑን ገልጸዋል።

### 2.4.5. የተማሪው ዳራዊ እውቀት (Students background knowledge)

አንድ መምህር የእለቱን ትምህርት ከማቅረቡ በፊት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መፈተሽ አለበት። የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ያላገናዘበ ትምህርት ማስተማር በክፍል ውስጥ አመራር ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህን ሀሳብ በተመለከተ Cangelosi (1997) እንደገለጹት አንድ ቋንቋ ነክ የሆነ ሥራ አንዱን ተማሪ ሊያነሳሳ፣ ሌላኛውን ደግሞ ላያነሳሳ ላያበረታታ)፣ ወይም አንዱን የማያነቃቃ የቋንቋ ትምህርት ሌላኛውን ሊያነቃቃ ይችላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ማስተማር ውስብስብነት የሚታይበት ጥበብ መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም መምህሩ የክፍሉን አመራር በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ ያመቸው ዘንድ አስቀድሞ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት መፈተሽ አለበት።

እንደ Belln (1997፡130) ገለፃ በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች መምራት ብዙ ጊዜን እንደማይጠይቅ፤ በመካከለኛ የክፍል ደረጃ የሚገኙትን ተማሪዎች መቆጣጠር ደግሞ ብዙ ጊዜ ጠያቂ እና አስቸጋሪ እንደሆነና በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ተከታታዮችን ለመምራት የሚደረገው እንቅስቃሴ ብዙም አድካሚ አይደለም። እንደ Underwood (1987፡45) ገለፃ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ማወቅ ለመምህሩ ጠቀሜታ አለው። በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የተለያየ ዳራዊ እውቀት ሊኖራቸው እንደሚችል አያጠራጥርም። ይህ ደግሞ የክፍል ውስጥ አመራሩን ሂደት አቅጣጫ ሊቀይር እንደሚችል ግልጽ ነው። ስለዚህ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት በጥልቀት በመፈተሽ የክፍል ውስጥ አመራሩን ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## 2.4.6. የተማሪዎች ፍላጎት

በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ፍላጎት መለያየት በክፍል ውስጥ አመራር ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽእኖ ያሳድራል። ይሁን እንጂ የሚቀርበው ትምህርት ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተስማማ ከሆነ መምህሩ በክፍል ውስጥ አመራር ላይ ችግር አይፈጠርበትም። ይህ እንዲሆን ደግሞ መምህሩ በተማሪዎች ላይ የፍላጎት አሰሳ (Need Asessment) ማካሄድ ይኖርበታል። ይህን በሚመለከት Belln (1997) መምህሩ የተማሪዎችን ፍላጎት ከተረዳ አዋኪ የሆኑ ተግባራትን በመከታተል ተማሪዎችም የትምህርቱን ዓላማ በቀላሉ እንዲረዱት ማድረግ እንደሚቻል ገልፀዋል።

በተጨማሪም Underwood (1987) እንደገለጹት ተማሪዎች የምናስተምረውን ትምህርት በንቃት እንዲከታተሉ የምናቀርበው ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት ያገናዘበ መሆን አለበት። ያን የመማር ፍላጎታቸውን ደግሞ ፈልጎ ማግኘት ተገቢ ነው። በተመሳሳይ መልኩ እንደ Borich (1988) ገለጻ ተማሪዎችን በተሻለ መልኩ ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራት ለማቅረብ ተማሪዎችን ጠይቆ ከመረዳት የተሻለ መንገድ እንደሌለ ግልጽ ነው ። ይህን ሀሳብ በተመለከተ Harmer (1991፣263) ተማሪዎች ምን መማር እንደሚፈልጉ በመምህራቸው ተጠይቀው የሚገኙው ምላሽ መምህሩ የብዙ ተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት በመፍጠር የሚያሳትፍ እና ብዙዎቹ ተማሪዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ክፍል ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራትን አዘጋጅቶ ለማቅረብ እንደሚረዳው ገልጸዋል።

ከዚህም ሀሳብ መረዳት የተቻለው መምህሩ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማርን ሂደት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት ያስችለው ዘንድ አስቀድሞ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ጠንቅቆ ማወቅ እና መረዳት እንዳለበት ነው፡፡

### 2.4.7. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ (Physical Condition)

የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ በክፍል ውስጥ አመራር ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለው እሙን ነው፡፡ ይኸን በመተለከተ Belln (1992) Arnds (1987)ን በመጥቀስ የመማሪያ ክፍሉ አደረጃጃት በተመለከተ በተማሪዎች ባህሪና ዝንባሌ (Beahvior and attitude) ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን የመማር ማስተማር ስራውን ከመጀመራቸው በፊት የክፍል ውስጥ አደረጃጃቱን ማስተካከል ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያመች ማድረግ አለባቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Belln (1992)፣ Weristen (1987)ን በመጥቀስ ተማሪዎች በረድፍ እንዲቀመጡ ማድረግ ምንአልባትም መረጃዎችን ለመለዋወጥ እና ተናጥላዊ ሥራዎችን ለማከናወን አመቺ መንገድ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ Harmer (1991፣5) የመማሪያ ክፍል ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የጎላ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን ተነሳሽነት በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ መልኩ ሊለውጠው እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም እንደ Borich (1988:58) ገለፃ የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት አላስፈላጊ ድርጊቶች እንዲከሰቱ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲታወክ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ በመሆኑ መምህራን በተማሪዎች የሚፈጸሙ ተቀባይነት የማይኖራቸው ድርጊቶች የመማሪያ ክፍሉን ገጽታ በማሻሻል መከላከል ይቻላል፡፡ ይህም በተማሪዎች ሥነ-ልቡናዊ ባህሪ (Psychological Characterstic) እና ውጫዊ ባህሪ ላይ ከማተኮር ይልቅ የክፍሉን ውስጣዊ እና ውጫዊ ገጽታ በመለወጥ ማስተካከል ይቻላል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ መምህራን የመማሪያ ክፍሉን ለመለወጥ የሚያስችል የፈጠራ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 2.5. የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር አለባውያን

አንድ መምህር የመማር ማስተማር ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆንለት ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን አለበት፡፡ ከነዚህም ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 2.5.1. ማቀድ /Planning/

አንድን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ምቹና ተስማሚ የሆነ የመማሪያ አካባቢ ፈጥሮ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ ከሚያስፈልጉት እና በመምህራን በቀዳሚነት መፈጸም ካሉባቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ የእቅድ ማውጣት ስራ ነው፡፡ እቅድን መሰረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ሂደታቸው ብዙውን ጊዜ ውጤታማ ናቸው፡፡ ስኬታማ የአመራር ችሎታ ያለው መምህር ከሁሉም በፊት ምን እንዴትና መቼ እንዲሁም በምን ዘዴ እንደሚያስተምር አስቀድሞ በመወሰን ያቅዳል፡፡ እቅዱንም በጽሁፍ ካሰፈረ በኋላ ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት ለተማሪዎቹ ዕቅዱን በመግለፅ ምን ለምን አላማ እንደሚማሩ አስቀድመው እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡ ለምን አላማ እንደሚማር የተረዳ ተማሪ ደግሞ የመማር ተነሳሽነቱ ከፍተኛ እንደሆነ Freeman (1991፡137) ገልጸዋል፡፡ ይህም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ጊዜውን ያለ አግባብ እዳያባክንና ከአንዱ ተግባር ወደ ሌላው ተግባር ያለምንም መደናገር (ግራ መጋባት) ጊዜ ሳያጠፋ እንዲሸጋገር ይረዳዋል (Clark and Starr 1986፡97)፡፡

መምህር ሁልጊዜም ወደ መማሪያ ክፍል ሲገባ ግልጽ ዓላማ ይዞና አቅዶ፣ ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ የሚችል ትምህርት አዘጋጅቶ ወደ ክፍል መግባት ይኖርበታል፡፡ ይህን ያላደረገ መምህር ክፍል ውስጥ የሥነ ሥርዓት መጓደል ችግር እንዲፈጠር ሰበብ ይሆነዋል (Moore 2001፣243)፡፡ በተጨማሪም ስኬታማ መምህር የሚባለው ሁል ጊዜ ወደመማሪያ ክፍል ውስጥ ሲገባ ምን ማድረግ እንዳለበት በጥንቃቄ የሚያስብና የመማር ማስተማሩን ሂደት አስቀድሞ ባዘጋጀው እቅድ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ማቀድ የመጀመሪያው የስኬታማ አመራር ተግባር እንደሆነም (Harmer 1991፣256) ገልፀዋል፡፡ የመምህራን የትምህርት ዝግጅት በቀን፣ በሳምንት፣ በወር ወዘተ. ተከፋፍሎ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን የትምህርት ዝግጅቱ ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች አመራረጥና አደረጃጀት የተማሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉና ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ የዚህ አይነቱ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ተማሪዎች ምን እንደሚማሩ ለምን ዓላማ እንደሚማሩ አሰቀድመው ስለሚጠቁሙና እንዲዘጋጅ እድል የሚሰጡ በመሆናቸው የመምህራን የክፍል ውስጥ አመራር አስቸጋሪ አያደርጉትም (Moore 2001፡58)፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ መምህራን ከመማር ማስተማር ሂደቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የትምህርት ዕቅዶች በሚያወጡበት ጊዜ ከተማሪዎቻቸውና ከሌሎች አካላት ጋር በመወያየት

እቅዶቻቸውን ወደ ተግባር መለወጥ በሚችሉበት መልኩ ማዘጋጀት እንዳለባቸው Underwood (1987)፣ Cangelosi (1997፣41) እና Adams (1997) ገልፀዋል።

### 2.5.2. የተግባቦት ተግባር

በአንድ ክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመጀመርም ሆነ የተጀመረውን ትምህረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማከናወን በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ጤናማ የሆነ ተግባቦት ወይም ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ግድ ነው። ለምን ቢባል ውጤታማ ተግባቦት ለስኬታማ የክፍል ውስጥ አመራር መፍጠር ከሚያስፈልጉት የመምህር የክፍል ውስጥ ተግባራት አንዱ ነው (Dimmock 1993) ።

የመግባባት ችሎታ በመማር ማስተማር ሂደት መልካምና ጥሩ የማስተማር ክንውን እንዲኖር የሚያደርግ ነው። ጤናማ የሆነ የመምህርና የተማሪዎች ግንኙነት ለትምህርቱ ስኬታማነት ወሳኝ ነው። ይህም ሲባል መምህሩ ብቻ ተናጋሪ ተማሪውም አድማጭ ሳይሆን ከዚህ በተሻለ መልኩ አጠቃላይ የመማሪያ ክፍሉን ሥርኣት ማስተካከልና መምራትንም ጭምር የያዘ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። ትክክለኛ የተግባቦት ሂደት በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን የሁለትዮሽ፣ የእርስ በርስ መስተጋብር አቅጣጫን የተከተለ ነው። በተግባቦት ሂደት የመናገርን ብቻ ሳይሆን የማዳመጥንም ተግባር እንድናከናውን የሚጠይቅ ነው (Moore 2001፣62) ።

መምህራን በትክክል የተማሪዎቻቸውን ሀሳብና አመለካከት ተረድተው መግባባት ላይ ከደረሱ የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት ለመለየት፣ የትምህርቱን ዓላማ ለመወሰንና የክፍል ውስጥ ተግባራትን ለማዘጋጀት ከሚያስችል ውሳኔ ላይ መድረስ ይችላሉ (Cangelosi 1997፣136)።

እንደ Underwood (1987፣35) ገለጻ ማንኛውም ተማሪ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚሠራውን ሥራ በአግባቡ ካወቀና ከተረዳ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው። ዋናው ነገር ይህንን ሁኔታ በመፍጠር ከተማሪዎች ጋር መግባባትና እርስ በርሳቸው እንዲግባቡ ማድረግ የግድ ነው። ዋናው ነገር መግባባትን ለመፍጠር ምን ማድረግ እንዳለብን ማወቅ ነው። በተለይም ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመተግበር በተግባር ሂደቱም ስኬታማ መሆን ይቻላል።

- እያንዳንዱ ተማሪ በስሙ ጠርቶ ማበረታታት እና ማሳተፍ፣
- የምናስተምረውን ትምህርት በትክክል ማቀድና የተማሪዎችንም ነፃ ሃሳብ ሳይገድቡ መቀበል፣
- ባቀድነው ትምህርት ውስጥ ለማግኘት ያሰብነውን እቅድ ምን ያህል እንደተሳካ መናገር፣
- ውሱን ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ተማሪዎች እድል በመስጠት ማሳተፍ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በተማሪውና በአስተማሪው መካከል ብቻ ሳይሆን በተማሪውና በተማሪው መካከል ጭምር እንዲሆን መጣር፤ ላወጣውና ለተናገረው መመሪያ ሁሉ በትክክል ተገዥ መሆን "አደርጋለሁ" ብለን ለተማሪዎች የተናገርነውን ነገር አድርገን ማሳየት (Underwood 1987፣35)፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ መግባባት ለመፍጠር ተገቢ የሆነ ቋንቋ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ወቅት ተማሪዎችን ልናስተምራቸው የምንፈልገውና እኛም የምንጠቀማቸውን ሥነ ምግባር የተላበሱ አባባሎችን ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ ለመጀመሪያዎቹ ክፍለ ጊዜያት የሚከተሉትን አባባሎች ማስተማርና መናገር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም ይቅርታ፣ አመሰግናለሁ፣ እንደምን አደራችሁ፣ እንደምንዋላችሁ፣ የምለውን ተረድታችሁኛል? የመሳሰሉትን በምን ሁኔታ መጠቀም እንዳለባቸው ተማሪዎች ቀድመው እንዲያውቋቸው ማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለሚደረገው ተግባቦታዊ መስተጋብር አስተዋጽኦ አለው፡፡ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ተማሪዎች ጥያቄ ሲያቀርቡ እንደ ስህተት መቁጠርና ትህትና ያልተላበሱ ቃላትን (አባባሎችን) መጠቀም በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ አለመግባባት ስለሚፈጥር ይህን ተረድቶና ተገንዝቦ በአግባቡ ምላሽ በመስጠት ክፍሉን ማሳተፍ ያስፈልጋል (Underwood 1987፣38-39)፡፡

### 2.5.3. የተቆጣጠሪነት ተግባር

ቁጥጥር ለመማር ማስተማር ሂደት የራሱ የሆነ ሚና አለው፡፡ ይህን በተመለከተ Harmer (1991፣236) መምህራን ክፍሉን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ተግባርን ያከናውናሉ፡፡ ተማሪዎች የሚሰሯቸውን ሥራዎች ብቻ ሳይሆን መቼ መናገር ምን አይነት ቋንቋ መጠቀም እንዳለባቸው የሚቆጣጠሩ መሆን አለባቸው፡፡ በሌላ በኩል የመምህራን ቁጥጥር ያልተለየው የተማሪዎች ሥራ ውጤታማ እንደሚሆን Belln (1992) ገልጸዋል፡፡ እንደ Jarolimek and Foster (1997፡117) ገለጻ ቁጥጥር በራሱ እንደ መማሪያ ክፍል አመራር ችሎታ ግብ ተደረጎ ሊታሰብ

የሚችል ባይሆንም ይልቁን የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ የሚወሰድ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ አንዳንድ መምህራን በተማሪዎች ላይ እጅግ በጣም የጠበቀና ሰብአዊ መብትን የሚጋፋ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ ክፍሉ ፀጥታ የሰፈነበት እንዲሆን ለማድረግ ሲሉ ተማሪዎች እንዳይናገሩ፣ እንዳይንቀሳቀሱ፣ የሚሰጥዋቸውን ተግባር በተቀመጡበት ብቻ እንዲሰሩ በማድረግ የመናገር፣ የመንቀሳቀስ መብታቸውን ፈፅሞ በመከልከል የቁጥጥር ተግባራቸውን ይፈፅማሉ፡፡ ሆኖም ግን ቁጥጥርን አስመልክቶ መምህሩ ዓላማ ሊያደርገው የሚገባ የማስተማሪያ ክፍሉን ስነ ስርአት በማስጠበቅና ተማሪዎች የሚሰሯቸውን ትምህርታዊ ተግባራት ትክክለኛነት የመቆጣጠር ሃላፊነት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች የማገናዘብና ራሳቸውን የመምራት ሓላፊነት ተላብሰው ማደግ እንዲችሉ ከማድረግ አኳያ የተቆጣጣሪነት ተግባር ሊተገበር ይገባል፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው ተግባራት መምህሩ የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት፡፡ የቤት ሥራና የክፍል ሥራ መሥራት አለመስራታቸውን፣ መመሪያ መከተላቸውን፣ ትምህርቱን መከታተል አለመከታተላቸውን መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን መምህሩ በሚያስተምርበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ለመስራት በሚነጋገሩበት ጊዜ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን ጭምር መቆጣጠር ያስፈልጋል (Harmer 1991፣236)፡፡

### 2.5.4. የአደራጅነት ተግባር/Organiser/

ተማሪዎችን የማደራጀት ስራ አንዱ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታን የሚጠይቅ ነው፡፡ የማደራጀት ተግባር ተማሪዎች ምን መሥራት እንዴት መስራት እንዳለባቸው ከማቀድ ጀምሮ ለሥራዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ እስከመስጠት ድረስ የሚያከናወኑትን ልዩ ልዩ ተግባራትን ያካትታል፡፡ ይኸውም የትምህርቱን ይዘት መምረጥ፣ የመልመጃ አሰራሩን መጠቆምና ለመልመጃ ጥያቄዎች ምጋቤ ምላሽ መስጠትን ወዘተ ያጠቃልላል፡፡ ይህን በተመለከተ Harmer (1991) የብዙዎች የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎች ውጤታማነት የሚወሰነው በቅንጅቱ ጥሩነትና ተማሪዎች ለሚሰሩት ስራ ግልፅ የሆነ መመሪያ በማስቀመጥ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

አንድ መምህር ምንና እንዴት መስራትና ማሰራት እንደሚፈልግ በቅድሚያ ካላወቀ ወይም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ግልፅ መመሪያ ካልሰጠ እና ተገቢ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ካልተጠቀመ በክፍል ውስጥ የአፈፃፀም ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡እንደ Harmer (1991፣241) እና Jarolimek and Foster (1997፣130) አገላለፅ በማንኛውም የመማር ማስተማር ሂደት

ውስጥ የሚከናወን እንቅስቃሴ የማደራጅቱ ተግባር የመምህሩ ነው። የአደረጃጀቱ ተግባር የሚፈፀምበትን ሁኔታ በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን። ይህም በመማሪያ ክፍል ውስጥና ውጭ ሲሆን፤ ማደራጅቱ የሚጀምረው ከመማሪያ ክፍል ውጭ ነው። ስለዚህ መምህሩ የትምህርቱን ይዘት እንዴት ማቅረብ እንዳለበት ይወስናል፣ ያቅዳል እቅዱም የዓመት የምዕራፍ ወይም ዕለታዊ ሊሆን ይችላል። ከዚያ ወደ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ከገባ በኋላም የማደራጀት ስራ ይጠብቀዋል። ይህም ተማሪዎች በቡድን፣ በጥንድ፣ በግል እንዲሰሩ ማድረግና አቀማመጣቸውን በመወሰን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰንና መከታተል የማደራጀት ተግባራት ናቸው።

የማደራጅት ተግባራት ከመምህሩ ሥራ ውስጥ ጠንከር ይላል የሚባለው ነው። ይህን ተግባር ስንመለከተው ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደቱ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ለስኬታማ የመማር ማስተማር ውጤት ሁሉ ማደራጀት ቀዳሚ ተግባር ነው። ይህ ሳይሆን ከቀረ ግን የጊዜና የተግባር ብክነት ይከሰታል። ባግባቡ ያልተደራጀና ተቀነባብሮ ያልተሰራ ሥራ ውጤታማ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም። በመሆኑም መምህሩ በመጀመሪያ ለማደራጀት ሥራ ቅድሚያ ግልፅ መመሪያ ሊሰጠውና የሚሰራውን ሊያውቅ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ምኑንም ሳያውቀውና ሳይረዳው ግራ ተጋብቶ ይቀራል። በመሆኑም ተማሪው ሥራውን በሚገባ መሥራት እንዲችል አደራጀ አመራር የግድ ያስፈልገዋል (Harmer 1991፣239)። እንደ Arends (1997፣41)፣ Harmer (1991፣243-248)፣ Underwood (1987:76) አገላለጽ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ሂደት እንደተማሪው እንቅስቃሴና እንደሚከናወነው ተግባር ሊደራጅ ይችላል። ምሳሌ በአቀማመጥ፣ በማህበር፣ በፆታ፣ በመጡበት አካባቢ ወዘተ. ሊከናወን ይችላል። Underwood እንደሚሉት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደት ስኬታማ ለማድረግም ተማሪዎች በአራት መንገድ ማለትም በጥቅል፣ በጥንድ፣ በቡድን በግል በማደራጀት ተማሪዎችን ማሳተፍ ይቻላል።

### 2.5.5. የማነሳሳት/motivation/ ተግባር

በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የቀረበውን ትምህርት በአንክሮና በትጋት እንዳይከታተሉ ወይም ችግር እንዲፈጥሩ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ የማነሳሳት ሥራ ከትምህርቱ በፊት ተግባራዊ አለመደረጉ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ። ይህን በተመለከተ Belln

(1992) እንደገለጹት መምህራን ሁሉንም ተማሪዎች አነሳስቶ ወደ እለቱ ትምህርት ለማምራት ከፍተኛ የሆነ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ተቋቁሞ ውጤታማነት ያለውን ትምህርት ለማካሄድ በምርምር የተገኙ ልዩ ልዩ የማነሳሻ ስልቶችን በመጠቀም፣ እንዲሁም የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ የማነቃቂያ ስልቶችን ማጎልበት ይገባል፡፡ በተጨማሪም Borich (1988) እንደገለጹት በክፍል ውስጥ የሚፈጸሙ የሥነ ሥርዓት ችግሮችን ለመከላከል የመጀመሪያው ደረጃ ተማሪዎችን በማነሳሳት ለትምህርት ያላቸውን ፍላጎት እንዲጨምር ማድረግ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ቀዳሚ ሥራ ወይም ለአንድ የመማር ማስተማር ሥራ የጀርባ አጥንት እንደሆነ የሚጠቀሰው ተነሳሽነት ነው፡፡ በመሆኑም መምህሩ የመማር ተነሳሽነት የሌላቸውን ተማሪዎች በመለየትና ለትምህርቱ ከጅማሮው ተነሳሽነት ያላቸውን ተማሪዎች የመማር ተነሳሽነታቸውን በማሳደግ የቋንቋውን ትምህርት ማካሄድ ይጠበቅበታል (Wright፣ 1987፣53)፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመመማር ተነሳሽነት የሌላቸው ከሆነ፣ መምህሩም የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ለመፍጠር ሁኔታዎችን የማያመቻች ከሆነ የመማር ማስተማሩን ሂደት ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ ስለሚሆን የሚፈለገውን፣ የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ በተማሪዎች ላይ ለመፍጠር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሆኑም መምህራን ከሁሉም በፊት ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው በማድረግ የመማር ተነሳሽነትን የማጎልበት ሥራ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

ተነሳሽነት ለመማር ማስተማር ሂደት እንደ ማእዘን ድንጋይ የሚቆጠር ነው፤ ይሁን እንጂ በተማሪዎች ላይ የመማር ተነሳሽነት ፈጥሮ ወደ እለቱ ትምህርት ለመግባት የሚደረገው ሂደት አስቸጋሪና ፈታኝ እንደሆነ ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ይህን በተመለከተ እንደ Whitaker (1995፣160) ገለፃ በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት ክንውን በጣም ጠቃሚ የሆነውና በክፍል ውስጥ አመራር ላይ ፈታኝ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ከፍተኛ የመማር ተነሳሽነት የመፍጠሩ ሁኔታ ነው፡፡

የመምህሩ የማነሳሳት ትግበራ የሚወሰነው እንደ ተማሪዎቹ የመማር ፍላጎትና ስሜት ነው፡፡ መምህሩ በቅድሚያ የተማሪዎችን ፍላጎት መፈተሽ እንዲሁም የማነሳሳት ሂደቱን ሊያደናቅፍ የሚችሉ ውጫዊ ሁኔታዎችን መቃኘት አለበት ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Belln (1992) እና Borich (1988) እንደገለጹት መምህሩ ተማሪዎችን በተሻለ መንገድ ለትምህርት ለማነሳሳት ውስጣዊ ሁኔታ (ፍላጎት፣ ስሜት) እንዲሁም የክፍሉን አደረጃጀት ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡

የሚያስተምረውን ትምህርት ለማስተማር ተነሳሽነት ያለው መምህር የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በመቀስቀስ በኩል ከፍተኛ የሆነ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ Wright(1987) እንደሚለት መምህሩ በክፍል ውስጥ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተማሪዎች የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማነሳሳት በኩል የጎላ ድርሻ አለው፡፡ ይህም በመሆኑ በእያንዳንዱ ደቂቃ ተማሪዎችን ያበረታታል፡፡

በተመሳሳይ እንደ Underwood (1987) ገለጻ ተማሪዎች በሙሉ ስሜት በትምህርቱ እንዲሳተፉ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች ለጥያቄዎች ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ስም በመጥራት፣‹‹ልክ ነው››፣ ‹‹ጥሩ››፣ ‹‹ጎበዝ ልጅ››፣‹‹በትክክል ተመልሷል››፣ ቢያንስ ቢያንስ እንኳ ጭንቅላትን በማንቀሳቀስ ማበረታታት ይገባል፡፡ እነዚህን ነገሮች ማከናወንም የጥሩ አመራር ተግባር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

እንደ Cangelosi(1997፣98) ፣ Rinne (1997፣3-4) ፣ Brown (1994፣155) እና Harmer (1991፣3-4) አገላለጽ ተነሳሽነት በጥቅሉ በሁለት ይከፈላል፡፡

### 2.5.5.1. ውስጣዊ ተነሳሽነት /interinsic motivation/

ውስጣዊ ተነሳሽነት ተማሪዎቹ የቋንቋ ትምህርቱን ለመማር ውስጣዊ ግፊት ወይም መበረታታት ሲኖራቸው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Rinne (1997) እና Harmer (1991) እንደገለጹት ውስጣዊ ተነሳሽነት ተማሪዎች አንድን ትምህርት ለመማር ከቤት ይዘውት የሚመጡትን አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ስሜት፣ ብቃት፣ ግላዊ ሁኔታና በራስ የመወሰን ችሎታን ያጠቃልላል፡፡ ይህንንም ደግሞ መምህሩ የአነሳሽነት ተግባሩን በተገቢው መንገድ ከተወጣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሊያዳብሩት ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ከመምህሩ አነሳሽነት ጥረት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥን ያለው ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም መምህሩ የሚመርጧቸው የትምህርት ይዘቶች የትምህርት ዝግጅቱን ለመማር መስተማር የሚጠቀምባቸው ስልቶች እና የራሱ የመምህሩ አቀራረብ የተማሪውን ውስጣዊ ተነሳሽነት ጠንካራ ወይም ደካማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

እንደ Belln (1992፣88-89) እና Harmer (1991፣4-6) ገለጻ በውስጣዊ ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም ፡-

*የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ* :- የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ በተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። ማለትም የመብራቱ ሁኔታ፣ የክፍሉ ንጽሕና፣ የመቀመጫዎችና የሌሎች ቁሳቁሶች አደረጃጀት ምቹ አለመሆን፣ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት የተማሪዎቹን የመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዲቀንስ ያደርጉታል። በመሆኑም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ተነሳሽነት እንዲቀንስ የሚያደርጉ ነገሮችን ማስወገድ ያስፈልጋል።

*የመምህሩ ሁኔታ*:- መምህሩ የሚጠቀመው የማስተማሪያ ዘዴ፣ በሚያስተምረው ትምህርት ላይ ያለው አውቀት፣ ለተማሪዎች ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ፣ ለተማሪዎች ያለው አመለካከት ወዘተ. በተማሪዎች ውስጣዊ መነሳሳት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል (Harmer 1991)። በመሆኑም አንድ መምህር የተማሪዎችን ውስጣዊ ተነሳሽነት ለመጠበቅ የሚያስተምረውን ትምህርት በሚገባ ማወቅና ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል ዓይን ከማየቱ ባሻገር ችሎታቸውን ያገናዘበ የመማር ክንውን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

### 2.5.5.2. ውጫዊ ተነሳሽነት /Exterinsic motivation/

ውጫዊ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት የሚመነጨው ከግለሰቡ ውጭ ሲሆን ከሌላ አካል በሚገኝ ማበረታቻና አዎንታዊ ምላሽ የሚዳብር ነው። ይህም ጥሩ፣ ጎሽ፣ በርታ በማለት ሽልማት በመስጠት፣ ስራ የሥራ ጊዜ በመስጠት፣ ቅጣትን በማስወገድ ማብረታታትና ውጫዊ ተነሳሽነት መፍጠር ይቻላል። ስለሆነም ውጫዊ አነሳሽነት የተማሪውን የመማር ፍላጎት /ተነሳሽነት/ በመጨመር ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለው።

በሌላም በኩል Charles (1982፣94) እንደገለጹት መነሳሳት በሰዎች ውስጥ የሚፈጠር ለአንድ ክንውን ወይም ግብ የሚገፋፋ ውስጣዊ ሁኔታ ነው። ይሁን እንጂ መነሳሳት የተለያዩ ገጽታዎች አሉት እነዚህም:-

- ለመማር መነሳሳት
- ለድል መነሳሳት
- ለተለያዩ ዓላማዎች መነሳሳት
- ተቀባይነት ለማግኘት መነሳሳት የመሳሰሉት ናቸው (Charles 1982፣95)።

እንደ Charles (1982፣95) ገለጻ የሚከተሉትን ተግበራት በማከናወን ተማሪዎችን ማነሳሳትና ትኩረታቸውን መሳብ ይቻላል። እነዚህም:-

* ማራኪ መርጃ መሳሪያዎችን መጠቀም፣
* የተማሪዎችን ትኩረት የሚሰቡና አመራመሪ የሆኑ ክንውኖችን በመስጠት፣
* የግልና የቡድን ፕሮጀክት ሥዎችን በመስጠትና ውዥንብር (ግራ መጋባት) በማስወገድ ከተማሪዎች ምን እንደሚጠበቅ በግልፅ በመንገር፣
* ተከታታይነት ያለው ምጋቤ ምላሽ ማጠናከርያ በመስጠት፣
* ተማሪዎች ሥራቸውን የሚያቀርቡበትን አጋጣሚ በመፍጠር፣
* ተገቢ ሥራ መሥራትን፣ ሥነ ምግባርን፣ የመሥራት ልምድንና ተጠያቂነትን በተመለከተ ለተማሪዎች ሃፊነት መስጠት ናቸው፡፡

### 2.5.6. የቅጣት ተግባር

በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት በክፍል የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመከላከል በቋንቋ መምህራን ከሚወሰዱት እርምጃዎች አንዱ ቅጣት ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን በክፍል ውስጥ በተማሪዎች የሚከሰቱ የሥነ ሥርዓት ችግሮችን ለመቆጣጠር የተለያዩ የሥነ ሥርዓት እርምጃዎች ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ከነዚም መካከል በተማሪዎች ላይ የሚወሰዱ አሉታዊ ገጽታ ያላቸው መሳደብ፣ አካላዊ ቅጣቶች፣ ከክፍል ማስወጣት ወዘተ. የመሳሰሉት እና አዎንታዊ ገጽታ ያላቸው መምከር፣የተለየ ድጋፍ ማድረግ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው (Arends 1997፣158፣ congelosi 1997፣260)፡፡

መምህራን ተማሪዎቻቸውን በክፍል ውስጥ በሚፈፅሟቸው የሥነ ሰርዓት ችግሮች ላይ በማነጣጠርና ትምህርቱን በማቋረጥ ቅጣት ለመወሰድ ከመፍጠን ይልቅ ተማሪዎችን ከክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ማሳየት ያለባቸውን ባህሪያት በማስተማሩ አልያም በመምከሩ ላይ በማተኮር ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸውን ተማሪዎች መፍጠር አለባቸው (Good እና Brophy 1997፣173)፡፡

Moore (1982፣134) የሥነ ሰርአት ርምጃ መውሰድ ማለት ክፍልን ማስተዳደር ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራርን ውጤታማ ለማድረግ ቅጣት ኀታች ነው፡፡ ስለሆነም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሥነ ስርዓት ሲጓደል ርምጃ ከመውደስ ይልቅ የሚከተሉትን ጠቃሚነት ያላቸውን ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- በመጀመሪያ ደረጃ ምን እንደተደረገ በጥልቀት መመርምርና ያጠፉትን ተማሪዎች ነጣጥሎ ለየብቻቸው ሁኔታውን በመጠየቅ ማጣራትና ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ አለበለዚያ በህብረት ለማጣራት መሞከሩ አስቻጋሪ ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ይገባል፣
- ጥፋት ፈፃሚውን ለይቶ ተጠያቂ ማድረግ ተገቢነው፣
- ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባ የተሻለውን ሥነ ምግባር ማሳየትና እንዲከተሉት መገፋፋት፣ ሊከተሉት የማይገባውን ረብሻና መጥፎነት ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት(ችግር) ሁሉ መንገር፣
- ማክበር የሚገባቸውን ህግና ደንብን ሁሉ በማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ በመለጠፍ አሊያም በተሻለ መንገድ እንዲያውቁት በማድረግ ‹‹ ሳላወቅ ነው›› የሚለውን ሀሳብ በማስወገድ የርምት ርምጃ ተግባራዊ ማድረግ (Moore 1982)፡፡

መምህራን ተማሪዎችን መምከር አለባቸው፡፡ ምክር በመልካም አመራር ወቅት ያለው ጠቃሚነት የጎላነው፡፡ ስለሆነም ልክ እንደራሳቸው ልጆች ተማሪዎቻቸውን መምከር ይገባል፡፡ ይህም ሲደረግ ባሕሪን ለመለወጥ ችግሩን አውቆ ተመጣጣኝ የባሕሪ ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል እንቅስቃሴ ማድረግ ነው፡፡ መጥፎ ባሕርይ አይቶ ማለፍ አይገባም፡፡ ሊደረግ የሚገባውን ወዲያውኑ አግባብነት ያለው የምክር ርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ ተጨማሪ የትምህርት ስራ እንደ ቅጣት መስጠት ግን ተገቢ አይደለም፡፡ ትምህርታዊ ክንውን እንደቅጣት ከተተገበረ የትምህርት ሥራ መሆኑን ሳይሆን ቅጣትነቱን ስለሚያስብ የቤት ሥራውን በትምህርት መልክ አያየውም፡፡ ሌላው ጉዳይ ደግሞ በጥቂት ተማሪዎች ጥፋት ሁሉንም የክፍል ተማሪዎች መቅጣት የሚደገፍ ልማድ አለመሆኑን ሊታወቅ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ጥሩ ሥነ ምግባር ያላቸውን ተማሪዎች ስነ ልቦና ሊጎዳ እንደሚችል መታወቅ አለበት (Moore 1982፣138)፡፡

## 2.5.7. የአመራር ስጭነት ተግባር

በክፍል ውስጥ ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር በተያያዘ ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው የክፍል ውስጥ ሰራዎች ተማሪዎች ምን መቼና እንዴት መስራት እንዳለባቸው ግልፅ መመሪያ በማስተላለፍ በኩል ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት መምህራን ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ የቋንቋ መምህር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚሰሯቸው ሰራዎች ግልፅ የሆኑ መመሪያዎችን የሚሰጥ ከሆነ ተማሪዎች ምን ለምን እና እንዴት መስራት እንዳለባቸው አስቀድመው ስለሚረዱ በቀረበው ትምህርት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ የመምህሩ

የክፍል ውስጥ አመራር ሂደትም የተሳካ ይሆናል (Good and Brophy 1997):: ይህም ማለት ተማሪዎች ግልፅ የሆነ መመሪያ ሳይሰጣቸው በክፍል ውስጥ የሚሰሯቸውን ሥራዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወን ይችላሉ ብሎ መናገር አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም አንድ መምህር ለተማሪዎቹ ምን እንዴት መስራት እንዳለባቸው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ግልፅ የሆነ መመሪያ ካልሰጠ በክፍል ውስጥ የሥነ ስርዓት ወይም የአፈፃፀም ችግር ይገጥመዋል (Harmer 1991፣240)::

Clark እና Starr (1986፣ 93) Moore (2001፣ 54-55) መምህራን በክፍል ወስጥ በሚያሳዩት የአመራር ሰጭነት አከናወን ሂደት ላይ ልዩነት ይንፀባረቅባቸዋል። መምህራን ከሚጠቀሟቸው አመራር ስጭነት ውስጥም በዋነኛነት የሚጠቁሱት ሶስት ናቸው።

## 2.5.7.1. አምባገነን አመራር ስጭነት (Authoritarian leadership)

በዚህ የአመራር ስጪነት ስልት በአብዛኛው የመምህሩ የበላይነት ጎልቶ የሚስተዋልበት ስልት ነው። በዚህ የአመራር ሰጭነት የሚመደቡ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደት በበላይነት የሚቆጣጠሩ እና የትምህርት አሰጣጡ ሂደት ከመምህሩ ወደ ተማሪው ልክ እንደመሰኖ ውሃ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲፈስ የሚፈልጉ ናቸው። በአጠቃላይ የመማር ማስተማሩ ሂደት መምህር ተኮር የሆነ ገለፃ የበዛበት፣ የተማሪዎች ፍላጎት ያላገናዘበ ውሳኔና አመራር የሚሰጥበት ዘዴ ነው። በዚህም ዘዴ በመምህሩና በተማሪዎቹ መካከል ያለው ሁኔታ የአዛዥና ታዛዥነት ግንኙነት የሚንፀባረቅበት ነው።

አምባገነናዊ አመራር በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት ተማሪዎች ምንም ዓይነት ስህተት እንዲፈፅሙ አይፈለግም። ስህተት ፈጽመው ከተገኙ የቅጣት ርምጃ ይወስድባቸዋል። ቅጣቱ ስድብ ወይም አካላዊ ቅጣት ሊሆን ይችላል። ይህ የአመራር ሥልት የተማሪዎቹን ስህተትና የስህተት ምንጭ ተረድቶ የማስተካከያ ርምጃ በመስጠት ፋንታ በስህተት ፈፃሚዎቹ ላይ የቅጣት ርምጃ የሚወሰድበት በመሆኑ የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት የሚቀንስ በክፍል ውስጥ አመራሩ ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር (Arends 1997፣27) እና (Moore 2001፣53-54) ::

### 2.5.7.2. ዲሞክራሲያዊ አመራር /Democratic leadership/

ሃላፊነትን አብሮ የመወጣት ስሜት ደግሞ የዲሞክራት መምህር ባህሪ ነው፡፡ ይህ አይነት አመራር በማዘዝ እና በመታዘዝ ሳይሆን በማበረታታት ችግርን መፍታት እንዲቻል ያደርጋል፡፡ ይህም መምህር ደግ፣ የተማሪዎችን ስህተት እንደ ነውር የማይቆጥር፣ ደስተኛ ብሎም ጠንካራ መሪ ነው፡፡ ሲያስተምርም ተማሪዎች በበቂ ሁኔታ በክፍል ውስጥ በሚከናወኑት ተግባራት ላይ ያሳትፋል፤ ሃሳብ እንዲሰጡና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ እና እርስ በርስ እንዲወያዩ ይፈቅዳል (Moore 2001፣54)፡፡ ዲሞክራሲያዊ አመራር በመምህራንና በተማሪዎች መካከል በክፍል ውስጥ ያለውን ግንኙነት የአዛዥና ታዛዥ ሁኔታ ስለማይንፀባረቅበት ተማሪዎች የሚሰማቸውን ነገር ሁሉ ነፃ ሆነው እንዲገልፁ ዕድል ይሰጣል፡፡ በተማሪው ላይም በራስ የመተማመን ስሜት ይፈጥራል፡፡ የተማሪዎችንም የመማር ተነሳሽነት ይጨምራል (Arends 1997፣246)፡፡

በአጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ አመራር በመማር ማስተማር ወቅት በክፍል ውስጥ ብሩህ ድባብ በመፍጠር ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ የሚጥር ከተማሪዎቹ ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት ያለው፣ የተማሪዎችን ችግር የራሱ ችግር እንደሆነ ቆጥሮ ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር የሚፈታ፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሃሳባቸውን ነፃና ግልፅ ሆነው እንዲያቀርቡ ሁኔታቸውን የሚያመቻች፣ የሚያበረታታ ነው፡፡

### 2.5.7.3. ለዘብተኛ አመራር ስጭነት/laissez-faire leadership/

የለዘብተኛ አመራር ሰጭ መምህር ባህሪ ደግሞ መምህሩ ግድ የሌለውና ሁሉም ነገር በዘፈቀደ እንዲከናወን የሚፈቅድ ነው፡፡ የዚህ አመራር ስልት ወደ ግራ መጋባት የሚያመራና ሥራን የሚያበላሽ አመራር ነው (Moore 2001፣54)፡፡ ለዘብተኛ አመራር ከጉልበት አመራር ወደ መብትን አክባሪ /ዲሞክራሲያዊ/ ወደ ሆነው ነፃነትን ሰጥቶ በምርጫው ባግባቡ እንዲቀሳቀስ ወደ ሚያደርግ አመራር ቢለወጥ ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ነፃነት ሲባልም በህግ የተገዛ እንጂ ልቅ ማለት አይደለም፡፡ ተማሪዎች ጥሩ እንዲሆኑ መልካም አመራር ያስፈልጋቸዋል፡፡

### 2.5.8. የገምጋሚነት ተግባር

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ስኬታማነት መገምገም የመምህሩ አንዱ ተግባር ነው፡፡ መምህራን በተለያዩ ጊዜያት በክፍል ውስጥ በሚያቀርቧቸው የትምህርት ይዘቶች ተማሪዎቻቸውን ምን ያህል ተሳታፊና ውጤታማ እንደሆኑ በመፈተሽ የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የመጠቆም ሀላፊነት አለባቸው፡፡

መምህሩ በዕለት ተዕለት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪው የሰራውን ሥራ ምን ያህል አመርቂ እንደሆነ የተለያዩ ዘዴዎችን በመከተል ግምገማውን ያካሂዳል፡፡ ይህም ተግባር የተሰጠውን ተሳትፎ በመመልከት ተማሪዎቹ ያለባቸውን ደካማና ጠንካራ ጎን መገምገም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሲነጋገሩ ወይም ሲፅፍ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በመከታተል ፈተና በመስጠት መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም ግን ተማሪው ስህተት ሲፈጽም ጨዋነት በተላበሰ መልኩ ተማሪውን ሳያደናግጥ ማስተካከል አንዱ የዚህ የገምጋሚነት ስልት ሂደት ነው፡፡ ተማሪው ስህተት በሚፈፅምበት ጊዜ በፍጥነት ማስተካከሉ ተገቢ ቢሆንም ሂደቱ ግን መሆን ያለበት ስህተቱ እንዴት እንደተፈጠረና እንዴት መስተካከል እንዳበለት በማሳየት ላይ ሚያተኩር ሊሆን ይገባል (Harmer 1991፣273)፡፡ በተጨማሪም Harmer (1991፣238) እንደገለጹት የተማሪውን ስህተት ለማስተካከል የስህተቱን ሁኔታ አጉልቶ ለማሳየት ግምገማን በስርአት ለመተግበር የሰሩትን ስህተት በወረቀት እንዲመዘግቡ በማድረግ፤ በመቅረጸ ድምጽ ስህተትን በመቅዳት መልሶ በማስማትና በመቅረጸ ምስል መልሶ በማሳየት የሰሩትን ስህተት ራሳቸው እንዲያወጡ በማድረግ ግምገማን መተግበር ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የመምህሩ ሚና በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወነውን ተግባር ማስፈጽምና ማስተማር ብቻ አይለደም፡፡ ከማስተማሩም ተግባራት ጎን ለጎን በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን አጥንቶ ለነዚህ ችግሮች መፍትሄ ማፈላለግ፣ አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መሞከር፣ የመረጃ መሳሪያዎችን መስራት፣ አጠቃቀማቸውንና ብቃታቸውን አስመልክቶ ምርምር ማድረግ ተገቢ ነው (Harmer 1991፣242)፡፡

### 2.5.9. የጊዜ አጠቃቀም ተግባር

ከስኬታማ የክፍል ውስጥ አመራር ተግባሮች አንዱ ጊዜን በአግባቡ ስራ ላይ የማዋሉ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ብቃታቸውንና በሚያስተምሩት የቋንቋ

ትምህርት ውጤታማ ለመሆን እያንዳንዱ የክፍል ውስጥም ሆነ የውጭ ስራዎችን በሰዓቱ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ አመራር በቃቱ ስኬተማ የሆነ መምህር በራሱና በተማሪዎች ለሚከናወኑ አንዳንድ የክፍል ውስጥ ተግበራት ተገቢና ተመጣጣኝ የሆነ ጊዜ በመመደብ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡ ይኸውም ሥራውን መቼ መጀመርና መጠናቀቅ እንዳለበት አስቀድሞ ማቀድና መወሰን ያስፈልጋል (Rinne 1997፣130-131)፡፡

Moore (2001፣59)፣ Jarolimek and Foster (1997፣130-131) እንደሚሉት ጊዜ ከማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ ዋናው ጉይ ነው፡፡ ስኬታማ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ያለው መምህር በመማር ማስተማሩ ሂደት የጊዜ አጠቃቀሙን ከእያንዳንዱ ደቂቃ ጀምሮ ያውቃታል፡፡ የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ መምህራን የማስተማር ሥራውን ሲጀምሩም ሆነ ሲጨርሱ አስቀድመው ባቀዱት መሰረት መሆን አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ ተማሪዎች ጊዜያቸውን አላስፈላጊ በሆነ ሁኔታ ያባክናሉ፡፡ ለምሳሌ ተማሪውን ወደ ኋላ ዞሮ በማናገር፣ ከመቀመጫ በመነሳት፣ አላስፈላጊ ንግግሮችን በመናገርና ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን መፈጸም የመሳሰሉት የተለመዱ ጉዳዮች መምህራኑ ከስራ የሚያዘናጋቸው ተግባሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም መምህራን ጊዜን በአግባቡ ካለመጠቀም አኳያ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ወይም ለመቋቋም፣ እያንዳዱ የክፍል ውስጥ ክዋኔ በጊዜው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህን ሁኔታ ደግሞ ክፈሉን በአግባቡ ለመምራት ይረዳቸዋል፡፡

እንደ Rinne (1997፣131-133) ገለፃ በአንድ የመማር ማስተማር ሂደት ወቅት ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም የሚከተሉትን መሰረታዊ ስልቶች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ለእያንዳዱ ክፍለጊዜ የሚሆን ተግባራትን ወስኖ ተግባራዊ ለማድረግ ማቀድ፣
- የትምህርቱ የመጨረሻ ግብ እና ተግባሩ የሚጨርሰውን ጊዜ አስቀድሞ ለተማሪዎች ማሳወቅ፣
- እንደ ጥያቄዎቹ ቅለትና ክብደት አመዛዝኖ ተመጣጣኝ የሆነ የመስሪያ ጊዜ መስጠት፣
- ለስራው የተመደበው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ምን ያህል ጊዜ እንደቀረው ማሳወቅ፣
- በቀሩት ጥቂት የመጨረሻ ደቂቃዎች ትምህርቱን ተግባራዊ መሆኑን በማረጋገጥ ማጠቃለያ መስጠት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በተጨማሪም መምህራን በክፊል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ወቅት እያንዳንዱን ደቂቃ ከተማሪዎቻቸው ጋር በልዩ ልዩ ትምህርታዊ ክንዋኔዎች ላይ በማሳለፍ ጊዜን እንዴት በአግባቡ ተጠቅሞ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል መምከርና ማስተማር አለባቸው።

## 2.5.10. ምቹ ሁኔታን መፍጠር

በክፊል ውስጥ አመራር ስኬት ሌላኛው አስፈላጊ ነገር የመምህሩና የክፍሉ አጠቃላይ ገጽታ እና ሁኔታ አመቺነት ነው። የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ የሚሆነው የመማሪያ ቦታው የተማሪውን ቀልብ የሚማርክ ሆኖ ሲገኝ ነው። አንድ መማሪያ ክፍል አይን በሚስቡ የማስተማሪያ ማሳሪያዎች ለምሳሌ በፖስተሮች፣ በመጽሔት፣ በጋዜጦች ያሸበረቀ ሊሆን ይገባዋል። ይህም ክፍሉ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ያደርገዋል (Moore 1982 ፣139) ።

ስኬታማና ታታሪ መምህር ምንጊዜም መማሪያ ክፍሉን ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ይህም በክፍል ውስጥ ንጹሕ አየር እንዲኖር፣ የመማሪያ ክፍሉ ንጹሕ እንዲሆን፣ ግድግዳዎቹ ሁሉ ስለትምህርቱ እንዲናገሩ ፣ ተንቀሳቃሽ እና ምቹ የሆኑ የመማሪያ ወንበሮች ማዘጋጀትን ይመለከታል። በተጨማሪም የተለያዩ የማስተማር ሥልቶች ጠቃሚ እንደሆኑ ቢታመንም መምህሩ ግን ለራሱ የሚጠቅመውንና የሚመቸውን መምረጥ መቻል እንዳለበት ይታመናል። በዚህም ወቅት ከሌሎች ልምድ በመቅሰም ከስህተት በመራቅ ራስን ማዘጋጀት ነው።

ውጤታማ የክፍል አመራር ሰጭዎች የምንላቸው ኃላፊዎች ክፍሉን በስርዓት የሚያደራጁትን ነው። ይህን የማይከተሉ መምህራን የትምህርቱ ሥራ በአግባቡ ማከናወን ይሳናቸዋል። በመሰረተ ሃሳብ ደረጃም ውጤታማ የክፊል አመራር አተገባበር ስንል የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች በህብረትና በአንድነት ተግባብተው በመስራት ችግርን ለማስወገድ ሲንቀሳቀሱ ነው (Moore 1982፣140)።

በሌላ በኩል በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ሆነ በኮሌጅ ደረጃ መምህራን ቋንቋን በጥሩ ሁኔታ ለማስተማር በመጀመሪያ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለባቸው። ለምሳሌ የተለያዩ ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የግድግዳ ላይ ሥዕሎች፣ ፓስተሮች መጠቀም ይቻላል። እነዚህ ነገሮች የተሟሉበት የመማሪያ ክፍል ወዲያውኑ የተማሪውን ቀልብ የመሳብ ሀይል

ሰላለው በዚህ ክፍል ውስጥ ማስተማር ውጤታማ ለመሆን ያግዛል፡፡ በመሆኑም ከክፍል ክፍል የሚዘዋወሩም ከሆነ ይህኑ ሁኔታ በሌሎችም ክፍሎች እንዲኖሩ ማመቻቸት ይገባል (Underwood 1987፣46)፡፡

በተጨማሪም እንደ Underwood (1987፣46) ገለጻ የማስተማሪያ ክፍሎች የመማር ማስተማሩ ሂደት ሳቢና አጓጊ እንዲሆን ለማድረግ ቀጥለው የቀረቡትን ሁነቶች ማሟላት አስፈላጊ ነው፡፡

- መምህሩንና ተማሪዎቹን እንደተፈለገው ሊያንቀሳቅስ የሚችል የመማሪያ ክፍል፣
- ድምፅን በቀላሉ ሊያስማ የሚያስችል ክፍል፣
- በቂ የሆነ ብርሃን ያለው፣
- ለመማር ምቹ የሆነ ንፁህ አየር የሚገባበት፣
- ጥቁር ሰሌዳው ለተማሪውም ለአስተማሪውም በትክክል የሚታይ፣
- የክፍሉን ሁኔታ እንደተፈለገ በቀላሉ ለመለወጥ እና ለማስተካከል የሚያስችል፣
- ግድግድዳው ፓስተሮችንና ካርታዎችን የመሳሰሉትን ሁሉ ለመለጠፍ የሚያስችል፣
- የማስታወቂያ መለጠፊያ ሠሌዳ በክፍል ውስጥ መኖርና የመሳሰሉትን ሁሉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን አሟልቶ መገኘት የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ያደርገዋል፡፡ ይህም ተግባር የጥሩ አመራር ሰጭነት ምልክት ነው Underwood (1987፣46) ፡፡

### 2.5.11. የደንብና ስርዓት ተግባር

በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት ችግሮች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ወይም ችግሮቹን ለማቃለል የቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ ደንቦችንና ሥርዓቶችን በቅድሚያ ለተማሪዎቻቸው የማሳወቅን ሥራ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እንደ Rinne (1997፣132-133) ገለጻ መምህራን የአመቱን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት በመጀመሪያው የትምህርት ሳምንት ወይም የትምህርት ቀናት በዓመቱ የትምህርት ጊዜ በክፍል ውስጥ ምን ምን ነገሮችን መከተልና ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው የሚጠቁማቸውን የክፍል ውስጥ ደንብና ሥርዓት በግልፅ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

Cristison (1994) በበኩላቸው ስኬታማ አመራር ላወጣቸው የክፍል ውስጥ ደንብና ስርዓቶች በቅድሚያ ራሱ ተገዥ ሆኖ በአርአያነት መታየት የሚችል ነው፡፡ መምህሩ ለክፍል ውስጥ

ደንቦችና ሥርዓቶችን ተገዥ የማይሆን ከሆነ ተማሪዎችም ደንብና ስርአት ሊጥሱና ላያከብሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በክፍል ውስጥ አመራሩ ላይ ሆነ በትምህርት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ገልፀዋል፡፡

እንደ Belln (1992፣281)፣ እና Arends (1997፣40) ገለጻ የክፍል ውስጥ ደንብና ሥርዓት ከበርካታ ነገሮች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-

- በሰርዓቱ ወደ መማሪያ ክፍል መግባትና መውጣት፣
- የክፍል ውስጥ ንብረትን መንከባከብ (ወንበር፣ጥቁር ሰሌዳ፣ጠረጴዛ) ወዘተ.፣
- የክፍልና የቤት ስራ መስራት፣
- የመማሪያ ቁሳቁስ ይዞ መገኘት፣
- ያለ ፈቃድ በክፍል ውስጥ ከቦታ ቦታ አለመዘዋወር ፣
- ያለ ፈቃድ ከትምህርት ቤት አለመቅረት፣
- ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል መመልከት (አለማዳላት)፣
- ሥራዎችን በሰርዓት መጀመር እናማከነወን ፣
- የዕለቱ ትምህርት በአግባቡ መከታተል ፣
- የክፍል ውስጥ ንብረት አለመስረቅ
- የሚሉትን እና ሌሎችንም ያጠቃልላል፡፡

በአጠቃላይ እንድ ስኬታማ አመራር የመማር ማስተማሩን ሂደት ጤናማ በሆነ መንገድ ለማካሄድ ወይም በክፍል ውስጥ የሚፈጠሩ ችገሮችን ለመከላከል፣ ለመቀነስ በዓመቱ የትምህርት መጀመሪያ ሳምንት ባሉት ቀናት ውስጥ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሊከተላቸው የሚገባቸውን የክፍል ውስጥ ደንቦችና ሰርአቶችን በግልፅ ማወያየትና ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

## 2.6. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ሥር ለመቃኘት  የተሞከረው  ከዚህ ጥናት ጋር በርዕስ፣ በዓላማና ከአጠናን ዘዴ አንፃር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸውን ሥራዎችን ነው፡፡ በመሆኑም በሀገራችን ውስጥ ከክፍል አመራር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች ተጠንተዋል፡፡ ጥናቶቹም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠኑ ናቸው፡፡ ከነዚህም  ውስጥ፡-

ሒሩት ካሳው (1997) በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር በሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የወንድና የሴት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል አመራር ችሎታ ላይ የተደረገ ንፅፅራዊ ጥናት ነው። በጥናቱ መጨረሻ የተገኘው ውጤትም ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው።

በሌላም በኩል አንተነህ ውዱ (1998) በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በሚገኙ በአየር ጤናና በመድሃኔ ዓለም የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በኮከብና በእናት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ የተሻለ የክፍል አመራር ያላቸው የትኞቹ ናቸው? በሚል የተደረገ ንፅፅራዊ ጥናት ነው። በጥናቱ መጨረሻም የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን በክፍል አመራር ችሎታቸው የተሻሉ መሆናቸውን ነው።

ሌላው አበበ እስጢፋኖስ (2001) በሆሳእና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ብቃት የሚዳሰስ ሲሆን በጥናቱ መጨረሻ የተገኘው ውጤትም የሆሳእና ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የክፍል አመራር ብቃት በተወሰኑ የክፍል አመራር አላባውያን አተገባበር ላይ ዝቅተኛ የሆነ ደረጃ ቢኖራቸውም በአብዛኛው ሲታይ ግን የአተገባበር ክህሎታቸው ከፍተኛ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ስንመለከት በሂሩት (1997) እና በአንተነህ (1998) የተጠኑት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው አንድነት ስንመለከት ጥናቱ በተካሄደበት ክልል እና የክፍል ደረጃ እንዲሁም ሁሉም ጥናቶች የተመሠረቱት በመምህራን የክፍል አመራር ርዕስ ዙሪያ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል። ልዩነታቸው ደግሞ፡-

- ጥናቱ በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች፣
- የቀደምት ጥናቶቹ ሥርዓተ ፆታን መሠረት በማድረግ በወንድና በሴት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል ያለውን የክፍል አመራር ክህሎት ልዩነት እና በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ያለውን የአመራር ክህሎት ልዩነት ላይ በማተኮር የተደረጉ ንፅፅራዊ ጥናቶች መሆናቸው፣

- በአጠናን ስልታቸው እና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያቸው እንዲሁም ጥናቶቹ ይዘውት በሚነሱት አላማ፣
- ይህ ጥናት በስድስት የክፍል አመራር አላባውያን ዙሪያ ብቻ ማተኮሩ ነው፣

እንዲሁም በአበበ እስጢፋኖስ (2001) የተደረገው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን አንድነት እና ልዩነት ስንመለከት አንድነታቸው በተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴና በክፍል አመራር አላባውያን ዙሪያ የተመሠረቱ መሆናቸው ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ:-

- ጥናቱ በተካሄደበት ክልል፣
- ጥናቱ በተጠናባቸው ትምህርት ቤቶች እና የክፍል ደረጃ፣
- ይህ ጥናት በተወሰኑ ማለትም በስድስት የክፍል አመራር አላባውያን ዙሪያ ብቻ በማተኮሩ ነው፣

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በአዲስ አበባ መስተዳድር በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል አመራር ትግበራቸው በመገምገም እና በትግበራ ወቅት የሚያጋጥምዋቸውን ችግሮች በመለየት የመፍትሄ ሃሳብ መስጠት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከሌሎች ጥናቶች የሚለይበት ዋናው ነጥብ ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የሚከተለው የአጠናን ዘዴ ዓይነታዊ ምርምር(Qualitative Research) ነው፡፡ አቀራረቡም ገላጭ (descriptive) በመሆኑ ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት በርዕስ ጉዳዩ ላይ ጸሃፍት ለንባብ ያበቋቸውን መጽሐፎችን በመመርኮዝ በክለሳ ድርሳን ላይ በተነሱት ነጥቦች መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ አተገባበራቸውን ይፈትሻል፡፡ የጥናቱን መረጃዎች ለመሰብሰብ ሦስት የሚሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በሥራ ላይ ውለዋል፡፡ በዚህ ምእራፍ ስር ለጥናቱ የተመረጠው ክልል፣ ትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ተጠኚ መምህራን፣ መጠይቁን በመሙላት የተሳተፉት የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ፣ መረጃዎችን የማጠናቀርና የአጠናን ስልት አካትቶ የያዘ ነዉ፡፡

### 3.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

#### 3.1.1. የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው አዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር ነው፡፡ ምርጫው የተካሄደው አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ አዲስ አበባ የተመረጠበትም ምክንያት ለጥናቱ የሚሆን መረጃ በዓይነትና በመጠን ወካይ ናሙና ለመሰብሰብ ያስችለኛል የሚል እምነት ስላደረብኝ ነው፡፡

#### 3.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታቸውን ከምርምር አላባውያን አንፃር አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ በዚህም ጥናት ውስጥ የተካተቱት ትምህርት ቤቶች የመንግስት የሆኑት ብቻ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በአዲስ አበባ የሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከማስተማሪያ መሳሪያዎች ዓይነት፣ ከክፍለ ጊዜያት ምደባ፣ ከተማሪዎች ብዛት እና ባሕርይ ወዘተ. አንፃር ተመሳሳይ በመሆናቸው ሁሉም በተመሳሳይ መስፈርት ለማመዛዘን ስለሚያመች ነው፡፡ ለታቀደው አላማ ስኬት ከአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሰረት አዲስ አበባ ውስጥ መቶ ስልሳ ስምንት /168/ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኙት 4 ትምህርት ቤቶች በእጣ ናሙና ዘዴ

ተመርጠዋል። ከ4ቱ ትምህርት ቤቶች መካከል 3ቱ በነሲብ የናሙና አመራረጥ (Random Sampling) ዘዴ ተመርጠዋል። ይህም የናሙና መረጣ ዘዴ ለትምህርት ቤቶች እኩል እድል ይሰጣል ተብሎ ይታመናል (Belln፣ 1987)። በአመራረጡም ሂደት አራት በእኩል በአራት ማእዘን ቅርፅ በተዘጋጁ ወረቀቶች በቁመታቸው በተመሳሳይ ሁኔታ ከተጠቀለሉ በኋላ በየተራ እጣ እንዲወጣ ተደርጓል። በእጣ በወጡት ሶስት ወረቀቶች ላይ የተጻፉት ትምህርት ቤቶችም በናሙናነት ተወስደዋል። እነዚህም ትምህርት ቤቶች እንጦጦ አምባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቀጨኔ መድኃኒአለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ድልበር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው።

### 3.1.3. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በአዲስ አበባ መስተዳደር ሥር ከሚገኙት የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከፍ ሲል በተጠቀሰው መንገድ በጥናቱ እንዲካተቱ የተመረጡት እንጦጦ አምባ፣ ድልበር፣ ቀጨኔ መድሃኔዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። በትምህርት ቤቶቹም ውስጥ ከ9ኛ-10ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥ በመሆኑ ቀጣዩ የአጥኝዋ ሥራ ተጠኝ መምህራን የሚያስተምሩበትን የክፍል ደረጃ መለየት ነበር። በመሆኑም በጥናቱ የሚገኘውን ውጤት በተሻለ መጠን አስተማማኝ ለማድረግ አጥኚዋ በተጠኚዎች ላይ ተደጋጋሚ የሆነ ምልከታ ለማድረግ ረዘም ያለ ጊዜ የሚያስፈልጋት በመሆኑ ከክፍል ደረጃዎቹ መካከል ዘጠነኛ ክፍል በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ምክንያት በትምህርት ቤቶች የሚቆዩባቸው ጊዜያት አጭር በመሆኑ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የማያመቹ በመሆናቸው ነው።

### 3.1.4. የመምህራንና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

#### 3.1.4.1. የተጠኝ መምህራን ናሙና አመራረጥ

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ስር ከሚገኙ ሶስት ተጠኝ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዘጠኝ የሚሆኑት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። ከዘጠኞቹ መምህራን ውስጥ ስድስቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በእጣ ናሙና ዘዴ ለጥናቱ ተመርጠዋል።

### 3.1.4.2. የተጠኝ ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ከአጠቃላይ (population) 600 ተማሪዎች ውስጥ ከመካከላቸው 25% ማለትም 150 ተማሪዎችን ለመምረጥ እጣ የማዉጣት ዘዴን በመጠቀም ተጠኝ ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ ምርጫውም የተካሄደው የ600 ተማሪዎችን የክፍል ቁጥር በተቆራረጡ ወረቀቶች ላይ ከተፃፉ በኂላ ወረቀቶቹን በመጠቅለል ጎድጓዳ በሆነ ሰሃን ውስጥ አድርጎ በማወዛወዝ 150 ተማሪዎች እስኪመረጡ ድረስ አንድ ባንድ እጣዎቹ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

ይህ ጥናት በዋናነት ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የተጠቀመበት ዘዴ የክፍል ውስጥ ምልከታ ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲደረግም እንደየጥናቱ ዓላማና ትኩረት ይለያያል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ የሆነው ግን ውሱን ምልከታ (fixed observation) የምልከታ ስልት ነው፡፡ ይህ የምልከታ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ በመማር ማስተማሩ ሂደት ጊዜ በክፍል ውስጥ በመምህራን ተግባራዊ ከሚደረጉት ክንዋኔዎች መካከል ለጥናቱ የሚፈለጉትንና ከጥናቱ ዓላማ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸውን ተግባራት መርጦ በማመሳከሪያ ሰነዱ (observation cheeklist) አማካኝነት የመምህራኑ የክፍል ውስጥ አመራር ትግበራ በቀላሉ ተከታትሎ ለመገምገም የሚያስችል ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው በአቀራረቡ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ድርጊቶች “ተከናውኗል” ወይም “አልተከናወነም ” በማለት የሚገለፅ ነዉ፡፡ በዚህ ጥናት ምልከታ የተደረገው ማመሳከሪያ ሰነዱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ ጥናት ያደረጉ አበበ (2001)፣ አንተነህ (1998) ሂሩት (1997) ወዘተ. የጠቀሷቸውን ስኬታማ የክፍል ውስጥ አመራር ተግባራት ከሆኑ አላባውያን ውስጥ ለዚህ ጥናት በተመረጡት ስድስት አላባውያን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህን የክፍል ምልከታ ማመሳከሪያ ሰነድ የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ ሲባል በአማካሪዬና በአንድ የመጀመሪያ ድግሪ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪ እና በአንድ የሁለተኛ ዲግሪ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪ ታይቶ አስተያየት እንዲሰጥበት ከተደረገ በኂላ በሙከራ ጥናት ተፈትሾና ታርሞ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡[1]

[1] አባሪ አንድን ይመልከቱ

የክፍል ምልከታው ከአጥኝዋ ግላዊ አመለካከት የፀዳ ለማድረግ በምልከታው ወቅት ሌሎች ሁለት ረዳት ገምጋሚዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል። ከምልከታው የተገኘውን ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ ለረዳት ገምጋሚዎቹ ስለማመሳከሪያ ሰነዱ እና ማመሳከሪያ ሰነዱ ስለያዛቸው ይዘቶች ሰፋ ያለ ገለፃ ተደርጎላቸዋል።

ሰንጠረዥ አንድ፡- የረዳት ምልከታ አድራጊዎቹ ዳራዊ መግለጫ

| ተ.ቁ | ስም | የትምህርት ደረጃ | የስራ ልምድ |
|---|---|---|---|
| 1 | ነፃነት አዋጅ | BA | 7 |
| 2 | አበበች ገብሩ | MA | 9 |

የጥናቱን ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ አጥኚዋ የጥናቱን ዓላማ ለተጠኚ መምህራኑ አልገለፀችም። ለምን ቢባል ጥናቱ በመምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ላይ የሚያነጣጥር ነውና። ተጠኚ መምህራኑ ጉዳዩ እንዲያውቁት ከተደረገ እውናዊ የሆነውን የክፍል ውስጥ ክዋኔ ላያሳዩ ይችላሉ (Best and Kahn 1993) ። ይህ ደግሞ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት ሲያስተምሩ መመልከት እንደምፈልግ በጠየቅኳቸውም መሰረት ሁሉም በመስማማታቸው ከምልከታው የሚገኘው ውጤት በተቻለ መጠን አስተማማኝ ለማድረግ ተሞክሯል። በምልከታውም ወቅት ከላይ የተገለፀውን የምልከታ ስልት በመጠቀም ለጥናቱ የተመረጡት 6 መምህራን በሚገቡባቸው ክፍሎች ለእያንዳንዱ ሶስት ሶስት ጊዜ ምልከታ ተካሂዶባቸዋል። በስተመጨረሻም የሶስት ጊዜው የምልከታ ውጤት እንዲመዘገቡ እና አማካይ ውጤቱ ተሰልቶ ከተወሰደ በኋላ አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እና ለአስተማሪዎች ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ከቀረቡት ምላሾች ጋር በማመሳከር አማካይ ውጤቱ ተወስዷል።

## 3.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ

### 3.2.2.1. የተጠኝ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ

በክፍል ምልከታው የሚገኘው ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ ለተጠኝ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች ተዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል። ተማሪዎቹ የጽሑፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ እንዲሞሉ የተደረገበት ዋናው ምክንያት ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው ጋር ያላቸው

የትምህርት ቤት ቆይታ ረዘም ያለ ጊዜ በመሆኑ የመምህራኖቻቸውን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ በመገምገም መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነባቸውና የክፍል ምልከታውን ውጤት አስተማማኝ በማድረግ በኩል እገዛ ስለሚያደርጉ ነው፡፡

ለተማሪዎች የቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች በሦስት ክፍሎች ተከፋፍለው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ የሆኑ የተማሪዎችን መረጃዎች (እድሜ፣ ፆታ፣ የክፍል ደረጃ፣ የሚማሩበት ትምህርት ቤት) የሚገልጽ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የመምህራንን የክፍል ውስጥ ተግባራት አፈፃፀም ለመገምገም የተዘጋጀ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ጥያቄዎቹም የመምህራንን የክፍል ውስጥ አመራር ከስድስት አላባውያን አንፃር አተገባበራቸውን ለመፈተሽ ከተዘጋጀው የክፍል ውስጥ ምልከታ ማመሳከሪያ ሰነድ (observation cheeklist) ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡

የመጨረሻውና ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ተማሪዎች የራሳቸውን አስተያየት የሚሰጡበት ክፍት ጥያቄዎች የሚገኙበት ክፍል ነው፡፡ ለተማሪዎቹ የተዘጋጁ ጥያቄዎች በአማካሪዬና በሌሎች ባለሞያዎች እንዲገመገሙና እንዲስተካከሉ ተደርገዋል[2]፡፡ በመጨረሻም ጥያቄዎቹ ለ150 ተማሪዎች ከተሰራጩ በኋላ በሁሉም ተማሪዎች ተሞልተው እንዲመለሱ ተደርገዋል፡፡

### 3.2.3. የተጠኚ መምህራን ቃለመጠይቅ

ለመምህራን የቀረቡት ቃለ መጠይቆች ዋና አላማ አንዱ ከክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከፅሑፍ መጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች ውጤት አስተማማኝነታቸው በተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ ይበልጥ ሰፋ ባለ መልኩ ማብራሪያ እንዲሰጡባቸው የተፈለጉ ከጥናቱ አላማ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ጥያቄዎችን ምላሽ ለማግኘት ይረዳል፡፡ ሌላው አላማ ከምልከታ እና ከተማሪዎች የተሞሉትን መጠይቆችን በማየት ተደባብሰው ታልፈዋል የተባሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መረጃቸውን ለማግኘት ታስበው የተዘጋጁ ጥያቄዎች አካትቶ የያዘ ነው፡፡[3]

## 3.3. የመረጃ አተናተን

ይህ ጥናት የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎት በተመለከተ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተገኙትን መረጃዎች እርስ በርስ በማመሳከር፣ በምእራፍ አንድና ሁለት የተዘረዘሩትን

[2] አባሪ ሁለትን ይመልከቱ
[3] አባሪ ሶስትን ይመልከቱ

ሀሳቦች በመጥቀስ የጥናቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚተነትንና የሚያብራራ ገላጭ ምርምር ነው፡፡ በመሆኑም የመረጃ አተናተኑ ዓይነታዊ ምርምር (qualitative) መርህን የተከተለ ሲሆን፣ አተናተኑም እንደሚከተለው ተከናውኗል፡፡

### 3.3.1. የክፍል ምልከታ መረጃ አተናተን

የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎታቸውን ለመፈተሽ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱና ዋነኛው የክፍል ውስጥ ምልከታ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙትን መረጃዎች የተተነተኑት በመጀመሪያ በሦስት ረዳት ምልከታ አድራጊዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ወደ አንድ የምልከታ ማመሳከሪያ ሰነድ ተጠቃልለው እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ከእያንዳንዱ መምህር በሶስት ክፍለ ጊዜያት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ወደ አንዱ የምልከታ ሰነድ እንደገና እየተጠቃለሉ የስድስቱም መምህራን የክፍል አመራር ትግበራ በተዘጋጀው የምልከታ ቅፅ "ተከናውኗል" ወይም "አልተከናወነም" በሚለው ተፈርጀው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ከሁሉም መምህራን የተገኙትን መረጃዎች ከያዙት ጭብጥ ወይም ርዕሰ ጉዳይ አንፃር ተመሳሳይ ሃሳብ የያዙትን ባንድ ላይ በመመደብ ድርጊቶቹ ከተከወኑ ምን ያህል መምህራን እንዳከናወኑት፣ድርጊቶቹ ከልተከናወኑ ደግሞ ምን ያህል መምህራን እንዳላከናወኑት ታሊ በማድረግ በሰንጠረዥ ውስጥ በቁጥር በማስቀመጥ እና የስድስቱም መምህራን የትግበራ ውጤት ተመሳሳይ ከሆነ ደግሞ ከአማራጭ መልሶቹ ውስጥ የመምህራኑ ውጤት ባልሆነዉ ቦታ የ 0 ምልክትን ተጠቅሞ በመግለጽ ተተንትኗል፡፡

### 3.3.2 . የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች አተናተን

በጥናቱ በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ካገለገለው የክፍል ምልከታ በተጨማሪ የጽሑፍ መጠይቅ አንዱ ነው፡፡ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ መወሰን ይቸግረኛል፣ አልስማማም፣ በጣም አልስማማም በማለት በጽሑፍ መጠይቆቹ ላይ የሰጡትን መረጃ ከመተንተናቸው በፊት ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ በወረቀት ላይ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም እያንዳንዱ ተማሪ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጠው ነጥብ እንዲደመርና አማካይ ውጤት እንዲሰላ ከተደረገ በኋላ በአማካይ ውጤቱ መሰረት ከክፍል ምልከታው፣ከቃለመጠይቅና ከተማሪዎች ግምገማ የተገኘውን ውጤት በማያያዝ ትንተናው ተካሄዷል፡፡ በመምህራን የተገኙት ውጤቶችም ወደ መቶኛ ሳይለውጡ እንዳለ በቁጥር እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡ ለምን ቢባል የተጠኝ መምህራን ቁጥር ጥቂት ስለሆነ በቁጥር ማስቀመጡ የተሻለ ነው፡፡

### 3.3.3. የቃለ መጠይቅ መረጃዎች አተናተን

ለጥናቱ እንደ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ሆኖ ካገለገለው የክፍል ውስጥ ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ አንዱ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ከቃለመጠይቁ የተገኙት መረጃዎች የተተነተኑት ለስድስት ተጠኝ መምህራን የተዘጋጁ ቃለመጠይቆች እያንዳንዱ መምህራን የሰጡት ምላሽ ወደ መቶኛ ሳይለወጡ ቀደም ሲል በምልከታ ወቅትና በጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙት መረጃዎች ጋር በማመሳከር እንዳለ በቁጥር እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ቃለመጠይቁ የቀረበላቸው ስድስት ተጠኝ መምህራን ቁጥር ጥቂት በመሆኑ በቁጥር አስቀምጦ መተንተኑ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተና ውጤት

## 4.1. የመረጃዎች ትንተና

ይህ ምዕራፍ በሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በቃለመጠይቅ እና በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ተገልጸው እና ተተንትነው የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ መስተዳድር የሚገኙ ሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር አተገባበር ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ የሚመለስበት ምዕራፍ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጥያቄ ለመመለስ ያስችል ዘንድ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር በስድስት አበይት የክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን ሥር ከተደራጁ በኋላ በአሃዝና በመቶኛ ተሰልተው በሠንጠረዥና በገለጻ እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.1. አጠቃላይ መረጃዎች

#### 4.1.1.1. የተጠኝ መምህራን ዳራ

በአዲስ አበባ መስተዳደር በተመረጡ ሶስት የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ስድስት ተጠኚ መምህራን የክፍል አመራር ክህሎታቸውን በተመለከተ አጋዥ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል የተተኳሪ መምህራኑ አጠቃላይ ዳራቸው ምን እንደሚመስል ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

ከዚህም ቀጥሎ በሚቀርቡት ሦስት ዘንጠረዥች ስለመምህራኑ አጠቃላይ ዳራዊ ሁኔታ የሚገልጹ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የተጠኝ መምህራን ግላዊ መረጃ

| ተ.ቁ | መምህራን | ፆታ | | እድሜ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት ሙያ | | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | | | አብይ | ንዑስ | |
| 1 | መ 1 | | - | 26 | ቢ.ኤ ድግሪ | ጆግራፊን በማስተማር | አማርኛ | 4 |
| 2 | መ 2 | | - | 28 | ቢ.ኤ ድግሪ | አማርኛን በማስተማር | | 5 |
| 3 | መ 3 | | - | 33 | ቢ.ኤ ድግሪ | አማርኛን በማስተማር | | 10 |
| 4 | መ 4 | | - | 27 | ቢ.ኤ ድግሪ | አማርኛን በማስተማር | | 4 |
| 5 | መ 5 | - | | 29 | ቢ.ኤ ድግሪ | አማርኛን በማስተማር | | 4 |
| 6 | መ 6 | - | | 26 | ቢ.ኤ ድግሪ | አማርኛን በማስተማር | | 4 |

ተተኳሪ መምህራኑ ከላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ ከፆታ አንፃር ስለግላዊ ሁኔታቸው ከሰጡት መረጃ መረዳት የተቻለው በአዲስ አበባ መስተዳድር በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ አራቱ መምህራን ሴቶች ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡

እንዲሁም የመምህራኑን የትምህርት ደረጃ ስንመለከት አምስቱም በቢ.ኤ ዲግሪ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የሰለጠኑ ሲሆኑ የቀሩት አንድ መምህር ደግሞ የመጀመሪያ ዲግሪ ጂኦግራፊን በማስተማር የሰለጠኑ ሲሆን አማርኛን በንዑስ ትምህርት (በማይነር ደረጃ) የሰለጠኑ ናቸው፡፡

የማስተማር ልምዳቸውን በተመለከተ ሠንጠረዥ ላይ ያለው መረጃ እንደሚያመለክተው ሁለት መምህራን የአምስት እና የአስር አመት ያገልግሎት ዘመን ያላቸው ሲሆን የተቀሩት አራት መምህራን ግን የአራት ዓመት አገልግሎት ያላቸው ናቸው፡፡ ታዲያ ይህ የሚያመለክተው አብዛኞቹ ተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የረጅም ዓመት የማስተማር ልምድ እንደሌላቸው ነው፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለውና በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.4.1. ላይ እንደተገለጸው

የማስተማር ልምድ የሌላቸው መምህራን ክፍሉን ለመምራት በሚያከናውኑት ተግባር ላይ ችግር እንደሚገጥማቸው ነው፡፡

### 4.1.1.2. የመምህራን ስልጠና

ሠንጠረዥ ሦስት፡- የመምህራን ስልጠና በተመለከተ ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | |
|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይደለም |
| 1 | መሠረታዊ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታዎን ሊያዳብር የሚችል ትምህርት አሊያም ስልጠና ወስደዋል፡፡ | 2 | 4 |

በሠንጠረዥ ሶስት ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራን መሠረታዊ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታቸውን የሚያዳብር ትምህርት አልያም ስልጠና መውሰዳቸውን በተመለከተ አራት መምህራን አለመውሰዳቸውን ሲገልፁ የተቀሩት ሁለት መምህራን ደግሞ አዎንታዊ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም የምንረዳው አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን በክፍል አመራር አላባውያን ዙሪያ ምንም አይነት ስልጠናና ትምህርት አለማግኘታቸው ነው፡፡ ለመማር ማስተማሩ ስኬት ደግሞ ከትምህርት እውቀት ባሻገር የክፍል አመራር ክህሎት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ተተኳሪ መምህራኑ በክፍል አመራር ዙሪያ ምንም አይነት ስልጠናና ትምህርት አለማግኘታቸው በማስተማር ክንውናቸው ውጤታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ መገመት ይቻላል፡፡

### 4.1.1.3. መምህራን ለሞያውና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና ፍላጎት

ሠንጠረዥ አራት፡- መምህራን ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎትና አመለካከት

በተመለከተ ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | |
|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይደለም |
| 1 | ወደመምህርነት ሙያ የገቡት ፈልገው ነው ? | 1 | 5 |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት በምርጫዎ ነው ? | 1 | 5 |
| 3 | በአሁኑ ሰዓት የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመሆንዎ ደስተኛ ነዎት? | 2 | 4 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራኑ ወደ መምህርነት ሙያ የገቡት እና የአማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት መርጠውትና ወደውት የገቡበት ሙያ መሆኑን በተመለከተ ተተኳሪ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ አምስቱ መምህራን ወደ ሙያው የገቡት መርጠውት እና ፈልገውት እንዳልሆነ የገለጹ ሲሆን አንድ መምህር ግን ወደ መምህርነት ሙያ የገቡት ፈልገውት እና መርጠውት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ሰዓት የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመሆንዎ ደስተኛ ነዎት? ለሚለው ጥያቄ ተተኳሪ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ መ1 "… ደስተኛ አይደለሁም ምክንያቱም ሙያው ስኬታማ የሚያደርገኝ ስላልሆነ ብችል ሌላ ስኬታማ ልሆንበት የምችለውን መንገድ ነው የምፈልገው" ሲሉ መልሰዋል፡፡ መ2 በበኩላቸው "ደስተኛ አይደለሁም ለምን አዲስ ነገር አላገኝበትም፣ የማድግበት ሙያ አይደለም፣ ተማሪውም አዲስ ነገር ለማወቅ አይጓጉም፣ በሚከፈለኝ ደሞዝ አልረካም፣ ተማሪዎቹ ለአስተማሪ ያላቸው ክበሬታ የወረደ ነው ስለዚህ እንዴት ደስተኛ ልሆን እችላለሁ" ሲሉ የመለሱ ሲሆን መ3 እና መ4ም መ1 እና መ2 ከመለሱት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መልስ መልሰዋል፡፡ መ5 ግን ከሁሉም በተለየ መልኩ "ምንም እንኳን መጀመሪያ ሙያውን መርጬው እና ፈልጌው የገባሁበት ባይሆንም ከገባሁበት በኋላ ግን የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን በሰሯቸው ስራዎች በጣም ነው የምመሰጠው እና የምደሰተው ያን ጊዜ እኔም እነሱ የደረሱበትን ደረጃ ለመድረስ ጉጉት እያደረብኝ ስለመጣ አሁን አሁን ሙያውን እየወደድኩት ነው" ሲሉ የመለሱ ሲሆን መ6 ደግሞ ሲጀምርም ሙያውን ፈልገውት እና መርጠውት ስለገቡበት የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመሆናቸው ደስተኛ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

ባጠቃላይ ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ ምላሽ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ የቋንቋ መምህራን የመምህርነት ሙያውን ፈልገው እና መርጠውት እንዳልገቡበት እና አሁንም በሙያው ደስተኞች አለመሆናቸውን ነው፡፡ ተተኳሪ መምህራኑ ሙያቸውን ወደውት እና አክብረውት የማይሰሩ ከሆነ በክፍል አመራር ክህሎታቸው ላይ ውጤታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ መገመት ይቻላል፡፡

### 4.1.2. የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ዳራ

ሠንጠረዥ አምስት፡- የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች በፆታና በዕድሜ

| ተ.ቁ | ዕድሜ | ፆታ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | |
| 1 | 14 | 10 | 13 | 23 |
| 2 | 15 | 30 | 21 | 51 |
| 3 | 16 | 27 | 19 | 46 |
| 4 | 17 | 20 | 10 | 30 |
| ጠቅላላ ድምር | | 87 | 63 | 150 |

በሠንጠረዥ አምስት ላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው ለጥናቱ በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አማርኛ ቋንቋን የሚማሩ ተማሪዎች በትክክል መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት ተማሪዎች መካከል 87 ወንዶች ሲሆኑ 63 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መቶ ሃምሳ ተማሪዎች በትክክል የጽሑፍ መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል፡፡

በሌላም በኩል መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች ከዕድሜ አንፃር ስንመለከት አብዛኞቹ ከ15-17 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና ተቀራራቢነት የሚታይባቸው ናቸው ስለሆነም በጥናቱ ውጤት ሊመጣ የሚችል አሉታዊ ተፅእኖ ሊኖር እንደማይችል መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.1.3. ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት

ለተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን የመማር ፍላጎት አለሽ/አለህ? ተብለው ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ 52 ተማሪዎች (34.6%) አማርኛ ቋንቋን የመማር ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹ ሲሆን የተቀሩት 98 ተማሪዎች (65.3%) ደግሞ አማርኛ ቋንቋን ለመማር ምንም አይነት ፍላጎት እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ ተጠኚ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎት እንደሌላቸው ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ጥናቱ የራሱ የሆነ አስተያየት ሰጥቷል ይህም በሰንጠረዥ 4.1.1.2 እና በ 4.1.1.3. ላይ እንደተገለፀው አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን በክፍል አመራር አላባውያን ዙሪያ ስልጠና ወይም ትምህርት አለማግኘታቸው፣ ሙያውን ፈልገውና መርጠውት የገቡበት አለመሆኑን እና አሁንም ድረስ በማስተማር ስራቸው ደስተኞች



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አለመሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ምናልባትም ተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን ፍላጎት እንዲቀንስ ተጽእኖ እንዳሳደረባቸው መገመት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ተተኳሪ መምህራኑ በክፍል አመራር ክህሎት ዙሪያ በቂ የሆነ ስልጠናና ትምህርት አለማግኘታቸው የመማር ማስተማሩን ሂደት በተሳካ መንገድ ለማከናወን፣ ክፍሉን በስርዓት ለመምራት የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ሊፈጥር የሚችል የማስተማሪያ ዘዴ ለመጠቀም ይቸገራሉ፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳሳደረባቸው ለመገመት ተችሏል፡፡

## 4.2. የመምህራን የክፍል አመራር ትግበራ ከስድስት አላባውያን አንጻር የቀረበ ትንተና

### 4.2.1. የዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራ፡-

የመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹና ተስማሚ እንዲሆን፣ የትምህርቱ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ከሚያስፈልጉ እና በመምህራን በቀዳሚነት መከናወን ካሉባቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ የእቅድ ማውጣት ስራ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.1 ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም እቅድን መሠረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ሂደታቸው ብዙውን ጊዜ ውጤታማ ናቸው፡፡ ስኬታማ መምህር ከሁሉም በፊት ምን ዓይነት ትምህርት እንዴትና መቼ እንዲሁም በምን ዘዴ እንደሚያስተምር አስቀድሞ በመወሰን ያቅዳል፡፡ እቅዱን በጽሑፍ ካሰፈረ በኋላ ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት ለተማሪዎች ዕቅዱን በመግለፅ ምንና ለምን አላማ እንደሚማሩ አስቀድመው እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡ ከዚህም አንፃር በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የእቅድ ዝግጅት እና አተገባበራቸውን በተመለከተ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ስድስቱም መምህራን አስቀድመው እቅድ እንደሚያወጡና ባወጡት እቅድ ተንተርሰው የእለቱን ትምህርት እንደሚያስተምሩ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የትኛውን ትምህርት ለምን አላማ እንደሚያስተምሩ ለተማሪዎቻቸው ግልፅ የማድረጋቸውን ሁኔታ ለማወቅ ክፍል ውስጥ ገብተው የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት የሚያከናውኑት ተግባር ምንድነው ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መረጃ መ 1 "..... ያው እንደተለመደው ሰላምታ ሰጥቼ፣ ያለፈውን ትምህርት በመከለስ የእለቱን ትምህርት አስተምራለሁ" ሲሉ መልሰዋል፡፡ መ2 በበኩላቸው "የክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ እቃኛለሁ ያለፈውን ትምህርት ከልሼ የእለቱን

ትምህርት አስተምራለሁ" ሲሉ መልሰዋል። ታዲያ የተቀሩት 4 መምህራንም ከመ1 እና መ2 የተለየ መልስ አልሰጡም።

በአጠቃላይ ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ መረዳት የሚቻለው የዕቅድ ዝግጅት እና አተገባበር በተመለከተ ተተኳሪ መምህራኑ አስቀድመው እቅድ የማውጣት እና ባወጡት እቅድ ተንተርሰው የማስተማር ተግባርን እንደሚያከናውኑ ነው። ነገር ግን ለመምህራኑ ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት የሚያከናውኑት ተግባር ምን እንደሆነ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የትኛውን ትምህርት ለምን አላማ እንደሚማሩ አስቀድመው ግልፅ የማድረግ ተግባራትን እንደማያከናውኑ ለመረዳት ተችሏል። አጥኝዋ ተተኳሪ መምህራኑ የሰጡትን ምላሽ መገንዘብ ከቻለች በኋላ በተተኳሪ መምህራኑ ላይ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ምልከታ አድርጋለች። ይህ የምልከታ ሂደትም ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ተቀምጧል።

ሠንጠረዥ ስድስት ፡- የመምህራን የእቅድ ተግባራት ክንውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | ምልከታው ያተኮረባቸው ክንውኖች | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1.1 | ሳምንታዊ እቅድ አስቀድሞ ማዘጋጀት | 5 | 83.3 | 1 | 16.6 |
| 1.2 | አስቀድሞ በተዘጋጀው እቅድ መሠረት ማስተማር | 2 | 33.3 | 4 | 66.6 |
| 1.3 | ምን ለምን አላማ እንደሚያስተምሩ አስቀድሞ ለተማሪዎች ግልፅ ማድረግ | 0 | - | 6 | 100 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የዕቅድ ተግባር ክነውናቸው ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው። በመሆኑም ሳምንታዊ እቅድ አስቀድሞ ማዘጋጀትን በተመለከተ አምስቱ መምህራን ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ያመለክታል። በአንፃሩ አንድ መምህር ደግሞ አስቀድመው እቅድ የማውጣት ተግባሩን እንደማያከናውኑ በምልከታ ጊዜ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በተጨማሪም መምህራኑ አስቀድመው ባወጡት እቅድ ተንተርሰው ማስተማራቸውን በተመለከተ ሁለት መምህራን አስቀድመው ባወጡት እቅድ ተንተርሰው የእለቱን ትምህርት ሲያስተምሩ

ተስተውለዋል፡፡ ሌሎች ሶስት መምህራን ደግሞ ምንም እንኳ አስቀድመው እቅድ የማውጣት ተግባርን ቢያከናውኑም ባወጡት እቅድ መሠረት ግን የማስተማር ተግባርን አላከናወኑም፡፡ አስቀድመው ያወጡት እቅድ በዕለቱ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር የመለያየቱ ምክንያት ምን አልባትም መምህራኑ ክፍለ ጊዜ በመቅጣታቸው ምክንያት ወደኋላ ስለሚቀሩ አስቀድመው ካወጡት እቅድ ጋር አብሮ የሚሄድ ትምህርትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዳላስቻላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ሌላው አንድ መምህር ደግሞ ሲጀመርም ያዘጋጁት እቅድ ባለመኖሩ በእቅድ የተመሰረተ ትምህርት ተግባራዊ ማድረግ አለመቻላቸውን የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡ ፡ በአጠቃላይ ከምልከታው የተገኙት መረጃዎች መምህራኑ ከሰጡት ቃለ መጠይቅ ጋር ሲነፃፀር በተወሰነ መልኩ የተለያየ ነው፡፡ ይህም መምህራኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን አብዛኞቹን የእቅድ ተግባራትን በተገቢው መንገድ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የገለፁ ቢሆንም ከምልከታው የተገኘው መረጃ ግን አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን አስቀድመው ባወጡት እቅድ መሠረት እንደማያስተምሩ፣ ተማሪዎች ምን ለምን ዓላማ እንደሚማሩ የማሳወቅ ተግባርን እንደማያከናውኑ የሚያሳይ ነው፡፡ ለምን አላማ እንደሚማሩ የማያውቁ ተማሪዎች ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ ሊሆኑ እንደማይችሉ፣ እንዲሁም ተማሪዎች ለሚሰሯቸው ስራዎች አስቀድመው እንዲዘጋጁ እድል እንደማይኖራቸው እና መምህሩም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሥነ ስርዓት መጓደል ችግር እንደሚገጥመው በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.1. ተጠቅሷል፡፡

በሌላም በኩል የእቅድ ተግባራትን ክንውን በተመለከተ ተማሪዎች ነፃ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ መምህራችሁ የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመሯ/ሩ በፊት ምን ለምን አላማ እንደምትማሩ ታሳውቃለች/ ያሳውቃል? በምን መልኩ? ተብለው ለተጠየቁት 44 ተማሪዎች (29.3%) ይህ ተግባር በመምህራቸው እንደሚከናወን የገለጹ ቢሆንም በምን መልኩ እንደሚከናወን ግን የሰጡት ምሳሌ አልነበረም፡፡ በአንፃሩ የተቀሩት 106 ተማሪዎች (70.6%) ደግሞ ይህ ተግባር በመምህራቸው ተግባራዊ እንደማይደረግ በመግለፅ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም ከላይ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የትኛውን ትምህርት ለምን አላማ እንደሚማሩ አስቀድመው እንዲያውቁ የማድረግ ተግባርን እንደማያከናውኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለቀረቡት ልዩ ልዩ የማቀድ ተግባራት ክንውን በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበላቸው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ የሚያስረዳው በአብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን

የሚያስተምሩትን ትምህርት አላማ ለተማሪዎቻቸው ግልጽ የማድረግ ሁኔታ እጅግ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከምልከታ ከተገኘው መረጃ እና ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር ተቀራራቢነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ከምልከታም ሆነ ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚጠቁመው ተተኳሪ መምህራኑ የእለቱን ትምህርት በዝርዝሩ ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ለተማሪዎቻቸው ትምህርቱን ለምን አላማ እንደሚማሩ አውቀውት እንዲሄዱ የሚያደርግ ሁኔታን አለመፍጠራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

በሌላም መልኩ አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን አስቀድሞ እቅድ የማዘጋጀት ትግበራቸው የተሻለ መሆኑን በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ከክፍል ምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን መምህራን አስቀድመው ባዘጋጁት እቅድ መሠረት የእለቱን ትምህርት የማስተማራቸው ሁኔታ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምንም እንኳ ሁሉም መምህራን አዎንታዊ ምላሻቸውን ቢሰጡም በክፍል ምልከታ ጊዜ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ግን መምህራኑ ያወጡት እቅድና በእለቱ የሚያስተምሩት ይዘት የማይጣጣም መሆኑን ነው፡፡ ተተኳሪ መምህራኑ ባዘጋጁት እቅድ መሰረት እንደሚያስተምሩ የሰጡት ምላሽ ምንአልባትም በስራዬ ላይ የተለየ አሉታዊ ተፅእኖ ይደርስብኛል በሚል ፍራቻ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.1. Moore (2001) እና Harmer (1991) ስለ እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በተመለከተ ከአንድ ታታሪ መምህር የሚጠበቀው ተግባር ምን መሆን እንዳለበት ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡ ይኸውም መምህር ምንጊዜም ወደ መማሪያ ክፍል ሲገባ ግልጽ የሆነ ዓላማ ማቀድ ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ የሚችል ትምህርት ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህን ያላደረገ መምህር ክፍሉ ውስጥ የሥነ ሥርዓት ችግር ያጋጥመዋል፡፡ በተጨማሪም ወደ ክፍል ሲገባ ምን ማድረግ እንዳለበት በጥንቃቄ በማሰብ የመማር ማስተማሩን ሂደት አስቀድሞ ባዘጋጀው እቅድ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ማቀድ የመጀመሪያው የስኬታማ አመራር ተግባር ነው፡፡ የመምህራኑ የትምህርት ዝግጅት በቀን፣ በሳምንት፣በወር ወዘተ ተከፋፍሎ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን እቅድ ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን የመማር ማስተማሩን ሂደት በተዘጋጀው እቅድ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ ጭምር ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱን የትምህርት እቅድ ዝግጅት ተማሪዎች ምን እንደሚማሩ፣ ለምን አላማ እንደሚማሩ አስቀድሞ ስለሚጠቁሙ እንዲዘጋጅ እድል የሚሰጡ በመሆናቸው የመምህራን የክፍል ውስጥ አመራርን አስቸጋሪ አያደርጉትም፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል እነ Moore ከጠቀሷቸው የእቅድ

ተግባራት አንፃር በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ተጠኝ መምህራን በተገቢው መንገድ የማከናወን ችሎታቸው አብዛኞቹ መምህራን አስቀድሞ እቅድ የማዘጋጀት ትግበራቸው የተሻለ ቢሆንም ባዘጋጁት እቅድ መሰረት የዕለቱን ትምህርት የማስተማር ትግበራቸው እና ትምህርቱን በዝርዝር ማስተማር ከመጀመራች በፊት ተማሪዎች ምን ለምን አላማ እንደሚማሩ የማሳወቅ ተግባራት እንደማያከናውኑ ከምልከታ ከፅሑፉ መጠይቅ እና ከቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ተተኳሪ መምህራኑ አስቀድመው ባዘጋጁት እቅድ መሠረት የእለቱን ትምህርት እንደሚያስተምሩ በቃለመጠይቅ አዎንታዊ ምላሻቸውን ቢሰጡም በምልከታ ጊዜ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ግን መምህራኑ ይህን ተግባር የማከናወናቸው ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ከነዚህ ከተተነተኑት መረጃዎች በመነሳት ተተኳሪ መምህራኑ የተጠቀሱትን የእቅድ ተግባራት ያለማከናወናቸው ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ ለመገንዘብ ሞክሯል፡፡ ምንም እንኳን በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.1. እቅድን መሠረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ክህሎታቸው ብዙውን ጊዜ ውጤታማ መሆናቸውን ቢገልጹም አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራኑ ግን ምናልባት ያላቸው የማስተማር ልምድ አናሳ መሆን፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመሆናቸው ደስተኞች አለመሆናቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ ክፍለ ጊዜ ስለሚቀጡ የእቅድ ተግባራቱን በተገቢው መንገድ ተግባራዊ እንዳያደርጉ ምክንያት እንደሆንዋቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.4 Freeman (1991) እና Moore (2001) የጠቅስዋቸው ተግባራት በአተገባበር ሂደት በተገቢው መንገድ ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ ከምልከታ፣ ከጽሑፍ መጠይቅ እና ከቃል መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያስረዳው ተተኳሪ መምህራኑ ምንም እንደኳን አስቀድመው እቅድ የማዘጋጀት ትግበራቸው የተሻለ ቢሆንም ባዘጋጁት እቅድ መሠረት የማስተማራቸው እና ተማሪዎች የትኛውን ትምህርት ለምን አላማ እንደሚማሩ የማሳወቅ ትግበራቸው ግን በጣም ዝቅተኛ እንደሆኑ የሚያመለክት ነው፡፡

### 4.2.2. የማነሳሳት ተግባር

በክፍል ውስጥ የሚፈፀሙ የሥነ ምግባር ችግሮችን ለመከላከል የመጀመሪያው ደረጃ ተማሪዎችን በማነሳሳት ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት እንዲጨምር ማድረግእንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.5. ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደትም የመምህሩ ቀዳሚ ስራ እና ለመማር ማስተማሩ ሂደት የጀርባ አጥንት እንደሆነ የሚጠቀሰው ተነሳሽነት ነው፡፡ ከዚም አንፃር በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ መምህራን የማነሳሳት

ተግባራትን ከማከናወን እና ካለማከናወን አንፃር ትግበራቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሸ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ የቃለመጠይቁ ምላሽ የሚያመላክተውም ከተተኳሪ መምህራኑ ውስጥ አራቱ የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፉ የሚችሉ የተለያዩ ግጥሞች፣ ልቦለዶች፣ አጫጭር ታሪኮች በማቅረብ የማነሳሻ ተግባራትን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በመማር ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ እንደሚያበረታቷቸው፣ በተቻለ መጠን የወንበሮቹን አቀማመጥ ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺ እንደሚሆኑ አድርጎ በማስተካከል፣ የክፍሉን ንፅህና በማስጠበቅ እና ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁም ሆነ መልስ ሲመልሱ ስማቸውን በመጥራት እንደሚያሳትፏቸው ገልፀዋል፡፡ የተቀሩት ሁለት መምህራን ግን ከላይ የተጠቀሱትን የማነሳሳት ተግባራትን በመማር ማስተማሩ ሂደት በተገቢው መንገድ ተግባራዊ እንደማያደርጉ ገልፀዋል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት ያቀረቡት ፡-

- በሳምንት የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ ባለመሆኑ ከመጽሐፍ ውጭ የሆኑና ተማሪዎችን በተለየ መልኩ ሊያነቃቁ የሚችሉ ተግባራት ለማቅረብ አለመመቸቱን፣
- ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠየቁም ሆነ መልስ እንዲመልሱ እድል ሲሰጣቸው ሁሉም በጅምላ የመመለስ ልማድ ስላላቸው ተማሪዎችን በተናጥል ለማሳተፍ እድሉን ማግኘት አለመቻሉ፣
- ከሌሎች የትምህርት አይነቶች አማርኛን በጣም ቀላል እና ፋይዳ የሌለው አድርገው ስለሚያስቡት በትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ አለመሆናቸው፡፡
- በትምህርት ቤቱ ውስጥ በቂ የሆነ መርጃ መሳሪያ አለመኖሩ፣
- የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ተማሪዎችን በተለያዩ የማነሳሻ ተግባራት ለማሳተፍ አመቺ አለመሆኑ፡፡

ይህም ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ መምህራን የተነሳሽነት ተግባራትን በተገቢው መንገድ እንደሚያከናውኑ ነው፡፡ በሌላም በኩል ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የማነሳሻ ተግባራትን በተመለከተ በተተኳሪ መምህራኑ ላይ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ምልከታ የተካሄደ ሲሆን ውጤቱም ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

ሠንጠረዥ ሰባት፡- የማነሳሳት ተግባራትን በተመለከተ ምልከታዊ መረጃ

| ተ.ቁ | ምልከታው ያተኮረባቸው ክንውኖች | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2.1 | የእለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ የሚችሉ ልዩ ልዩ የማነሳሳት ተግባራትን ማከናወን | 1 | 16.6 | 5 | 83.3 |
| 2.2 | በተለያየ ምክንያት አማርኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት | 0 | - | 6 | 100 |
| 2.3 | የመማሪያ ክፍሉ ንፅህና የመማር ተነሳሽነት እንዲጨምር ማድረግ | 1 | 16.6 | 5 | 83.3 |
| 2.4 | የወንበሮቹ አቀማመጥ የመማር ተነሳሽነት እንዲጨምር ማድ | 0 | - | 6 | 100 |
| 2.5 | ተማሪዎች መልስ በመለሱም ሆነ ጥያቄ በጠየቁ ቁጥር ስማቸውን በመጥራት ተሳትፊ እንዲሆኑ ማድረግ | 0 | - | 6 | 100 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራኑ ወደ ክፍል ገብተው የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራትን ማከናወን በተመለከተ አንድ መምህር ማስተማር ከመጀመሩ በፊት አጫጭር ግጥሞችን በማንበብ ተማሪዎች ተነቃቅተው እንዲማሩ ሲጥር ተስተውሏል፡፡ የተቀሩት አምስት መምህራን ግን ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት የተማሪዎችን ወቅታዊ ሁኔታ ተረድተው ተማሪዎቹን ሊያነቃቁ የሚችሉ ምንም አይነት የማነሳሻ ተግባራትን ሲያከናውኑ በምልከታ ጊዜ አልተስተዋሉም፡፡ በተጨማሪም በተለያየ ምክንያት አማርኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት በተመለከተ ስድስቱም መምህራን ተግባሩን ሲያከናውኑ አልተስተ ዋሉም፡፡

በሌላም በኩል የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ሊያደናቅፉ የሚችሉ ውጫዊ ሁኔታዎችን (የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ) ማለትም የክፍሉ ንፅህና፣ የወንበሮቹ አቀማመጥ በማየት የመማር ተነሳሽነት እንዲጨምር የማድረግ ትግበራቸውን በተመለከተ መ1 ወደ ክፍል ከገቡ በኋላ ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት የክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ በመቃኘት ክፍል ውስጥ

ተቀዳድደው የተበታተኑ ወረቀቶችን ባዩ ጊዜ "ይህን ያደረገው ማነው! ለምንድነው በተዘጋጀላቸው የቆሻሻ መጣያ ክርታስ ላይ የማትጥሉት..." በማለት ከምንም በላይ የክፍሉን ንፅህና መጠበቅ እንዳለባቸው መልእክት ሲያስተላልፍ ተስተውሏል፡፡ የተቀሩት አምስት መምህራን ግን ክፍሉ ምንም ይሁን ምን ክፍል ገብተው አስተምረው ሲወጡ እንጂ ይህን አይነት ተግባር ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም፡፡ በተጨማሪም የወንበሮቹን አቀማመጥ በተመለከተ ስድስቱም መምህራን ከበላይ አካላት በወረደው ትእዛዝ መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን የአንድ ለአምስት አደረጃጀት የተከተለውን የወንበር አቀማመጥ ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን እንደልብ ተንቀሳቅሰው ለመማር እና ለማስተማር እንደማይመች እያወቁት ክፍል ውስጥ ሲገቡ ሆኖ እንዳገኙት ነው ማስተማር የሚጀምሩት፡፡ የወንበሮቹ አደረጃጀት ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራኑ እንደማይመች እያወቁት እንኳን የመማር ተነሳሽነትን ሊፈጥር በሚችልበት መልኩ ሁኔታዎችን የማስተካከል ተግባራትን ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም፡፡ ለዚህም ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው እንደምክንያት ያቀረቡት የአንድ ለአምስት የተማሪዎች አቀማመጥ ተከትሎ የማያስተምር መምህር ቅጣት ስለሚጠብቀው ማንም የወንበሮቹን አሰላለፍ መቀየር እንደማይችል ገልፀዋል፡፡

በሌላም በኩል ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች መልስ ሲመልሱም ሆነ ጥያቄ ሲጠይቁ ስም እየጠሩ የማሳተፍ ተግባርን በተመለከተ ስድስቱም መምህራን ተግባሩን ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም፡፡ ለዚህም እንደምክንያት በቃለመጠይቅ የሰጡት ምላሽ አብዛኞቹ ተማሪዎች በጅምላ የመመለስ ልማድ ስላላቸው ጥያቄ ሲጠየቁም ሆነ መልስ ሲመልሱ ስማቸውን በመጥራት በተናጥል እንዲሳተፉ ለማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡

በአጠቃላይ የምልከታው ውጤት እንደሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራኑ የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፉ የሚችሉ ልዩ ልዩ የማነሳሻ ተግባራትን ሲያከናውኑ፤ በተለያየ ምክንያት አማርኛ ቋንቋ ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው ሁኔታዎችን ሲያመቻቹ አልተስተዋሉም፡፡ በተጨማሪም የመማሪያ ክፍሉን ንፅህና በማስጠበቅ እና የወንበሮቹን አደረጃጀት ከምንም በላይ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ አለመሆናቸውን ተረድተው የማስተካከል ተግባርን ማከናወን አለመቻላቸው እና ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁም ሆነ መልስ ሲመልሱ የሚሳተፉት በጅምላ በመሆኑ የክፍሉ ፀጥታ ሲረበሽ እየተመለከቱ ተማሪዎች ባግባቡ ስማቸውን በመጥራት በተናጥል እንዲሳተፉ አላደረጉም፡፡ ይህም የተነሳሽነት

ተግባራትን በአግባቡ ተግባራዊ እንደማያደረጉ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ከተተኳሪ መምህራኑ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው አብዛኞቹ መምህራን ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የተነሳሽነት ተግባራት በተገቢው መንገድ እንደሚያከናውኑዋቸው ነው፡፡

በሌላም በኩል ተማሪዎች በትምህርቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የመምህራኑን የማነሳሳት ተግባራትን ክንውን በተመለከተ ለተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ ስምንት፡- የማነሳሳት ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የክፍል አመራር ክንውኖች | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1.1 | የእለቱን ትምህርት ከመጀመሯ/ሩ በፊት ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ ልዩ ልዩ የማነሳሻ ተግባራት ታከናውናለች/ ያከናውናል | 8 | 5.3 | 10 | 6.6 | 30 | 20 | 70 | 46.6 | 32 | 21.3 |
| 1.2 | በተለያየ ምክንያት አማርኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው ሁኔታችን ታመቻቻለች/ ያመቻቻል፡፡ | - | - | 12 | 8 | 18 | 12 | 100 | 66.6 | 20 | 13.3 |
| 1.3 | የመማሪያ ክፍሉ ንፅህና እንድንጠብቅ የሚያስችል ምክር በመለገስ ሁኔችን ታመቻቻለች / ያመቻቻል፡፡ | - | - | 20 | 13.3 | 4 | 2.6 | 76 | 50.6 | 50 | 33.3 |
| 1.4 | የወንበሮቹ አቀማመጥ የመማር ተነሳሽነትን እንዲጨምር በሚያስችል ሁኔታ ታደራጃለች/ ያደራጃል፡፡ | 9 | 6 | 10 | 6.6 | 11 | 7.3 | 53 | 35.3 | 67 | 44.6 |
| 1.5 | ተማሪዎች መልስ በመለሱም ሆነ ጥያቄ በጠየቁ ቁጥር ስማቸውን በመጥራት ተሳታፊ እንዲሆኑ ታደር ጋለች/ ያደርጋል፡፡ | 10 | 6.6 | 15 | 10 | - | - | 90 | 60 | 35 | 23.3 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያመላክተው ተተኳሪ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን ተነሳሽነት እንዲጨምር የሚያከናውኗቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት በተመለከተ

ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ነው፡፡ ስለሆነም መምህራን የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፉ የሚችሉ ልዩ ልዩ የማነሳሻ ተግባራት ከማከናወን አንፃር 8 ተማሪዎች (5.3%) በጣም እንስማማለን፣ 10 ተማሪዎች (6.6%) እንስማማለን፡፡ 30 ተማሪዎች (20%) መወሰን ይቸግረናል፣ 70 ተማሪዎች (46.6%) አንስማማም እንዲሁም የተቀሩት 32 ተማሪዎች ( 21.3%) ደግሞ በጣም እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያየ ምክንያት አማርኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት በተመለከተ 12 ተማሪዎች (8%) እንስማማለን፣ 18 ተማሪዎች (12%) መወሰንያስቸግረናል፣ 100 ተማሪዎች (66.6 %) አንስማማም እንዲሁም 20 ተማሪዎች (13.3%) በጣም አንስማማም በማለት የመለሱ ሲሆን ተማሪዎች የመማሪያ ክፍሉን ንፅህና እንዲጠብቁ የሚያስችል ምክር በመለገስ የመማር ተነሳሽነታቸው እንዲያድርባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት በተመለከተ 20 ተማሪዎች (13.3%) እንስማማለን፣ 4 ተማሪዎች (2.6%) መወሰን ይቸግረናል 76 ተማሪዎች (50.6%) አንስማማም የተቀሩት 50 ተማሪዎች (33.3%) ደግሞ በጣም አንስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡ በሌላም በኩል የወንበሮቹ አቀማመጥ የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ሊፈጥር በሚችል መልኩ ማመቻቸት በተመለከተ 9 ተማሪዎች (6%) በጣም እንስማማለን፣ 10 ተማሪዎች (6.6%) እንስማማለን፣ 11 ተማሪዎች (7.3%) መወሰን ይቸግረናል እንዲሁም 53 ተማሪዎች (35.3%) አንስማማም፣ የተቀሩት 67 ተማሪዎች (44.6%) ደግሞ ፈፅሞ እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች መልስ በመለሱም ሆነ ጥያቄ በጠየቁ ቁጥር ስማቸውን በመጥራት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግን በተመለከተ 10 ተማሪዎች (6.6%) በጣም እንስማማለን፣ 15 ተማሪዎች (10%) እንስማማለን፣ 90 ተማሪዎች (60%) አንስማማም፣ 35 ተማሪዎች (23.3%) ደግሞ ፈጽሞ እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ ከቀረቡት የተማሪዎች ምላሽ ጠቅለል አድርጎ መረዳት የሚቻለው በተጠቀሱት የማነሳሳት ተግባራት ክንውን የተተኳሪ መምህራኑ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ በአብዛኛው በክፍል ምልከታ ከተገኘው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ከተተኳሪ መምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ከምልከታ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ጋር በጣም የተጻረረ ነው፡፡

Belln (1992)፣ Borich (1988) እና Wright (1987) በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.5. መምህራን ውጤታማነት ያለውን ትምህርት ለማካሄድ በምርምር የተገኙ ልዩ ልዩ የማነሳሻ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲሁም የተለያየ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ የተለያዩ የማነቃቂያ ስልቶችን ማጎልበት እንደሚገባቸው ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚፈፀሙ የሥነ ስርዓት ችግሮችን ለመከላከል የመጀመሪያው ደረጃ ተማሪዎችን በማነሳሳት ለትምህርት ያላቸውን ፍላጎት እንዲጨምር ማድረግ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ቀዳሚ ስራ ወይም ለመማር ማስተማር ሂደት የጀርባ አጥንት እንደሆነ የሚጠቀሰው ተነሳሽነት ነው፡፡ በመሆኑም መምህሩ የመማር ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው በማድረግ የቋንቋውን ትምህርት ማካሄድ እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ከምልከታ፣ ከጽሑፍ መጠይቅ እና ከቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ አንጻር ተተኳሪ መምህራኑ እነዚህን የማነሳሻ ተግባራትን በትምህርቱ ሂደት የማከናወናቸው ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ምሁራኑ የጠቀሷቸውን ነጥቦች በአተገባበሩ ሂደት ጎልተው ያለመታየታቸው ምክንያት ምናልባትም መምህራኑ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑ፣ አዲሱ የአንድ ለአምስት የወንበር አደረጃጀት (የተማሪዎች አቀማመጥ) ተማሪዎቹ በመምህሩ ትይዩ ስለማይቀመጡ ወገባቸው የሚደገፍበት ነገር ስለሌለው ይበልጥ እንዲረብሹና እንዲሰላቹ ማድረጉ፤ መምህራኑ የተነሳሽነት ተግባራትን እንዴትና በምን ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው የማወቃቸው ሁኔታ ውስን ከመሆኑ የተነሳ ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ የራሱን ምላሽ ሰጥቷል፡፡

### 4.2.3. የተግባቦት ተግባር

በአንድ ክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመጀመርም ሆነ የተጀመረውን ትምህርት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማከናወን በመምህራኑ እና በተማሪዎች መካከል ጤናማ የሆነ ተግባቦት አልያም ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.2. ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ ለምን ቢባል ውጤታማ ተግባቦት ለስኬታማ የክፍል ውስጥ አመራር መፈጠር ከሚያስፈልጉት የመምህር የክፍል ውስጥ ተግባራት አንዱ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተተኳሪ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ሁል ጊዜ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት በማሳተፍ

የተማሪዎችን ሀሳብ የማዳመጣቸው ሁኔታን በተመለከተ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው እንደገለፁት 6ቱ መምህራን ተግባራቱን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ባልገባቸው ሃሳብ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብሎ ማስተናገድ እና ተማሪዎች እንዲፈሯቸው የሚያደርጉ ቋንቋዎችን ተጠቅመው መቅረባቸውን በተመለከተ ስድስቱም መምህራን የሰጡት ምላሽ ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁም ሆነ መልስ ሲመልሱ በትህትና ተቀብለው እንደሚያ ስተናግዷቸው እናተማሪዎች እንዲፈሯቸው የሚያደርግ ቋንቋ ፈፅሞ እንደማይጠቀሙ ገልፀዋል፡፡

ይህ ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚጠቁመው ተተኳሪ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ሁል ጊዜ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት በማሳተፍ የተማሪዎችን ሃሳብ እንደሚያዳምጡ፣ተማሪዎች ባልገባቸው ሃሳብ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብለው እንደሚያስተናግዱ እና ተማሪዎች እንዲፈሯቸው የሚያደርግ ቋንቋን ተጠቅመው እንደማያስተምሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላም በኩል የተግባቦት ተግባራትን ክንውን በተመለከተ  በተተኳሪ መምህራኑ ላይ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ምልከታ የተካሄደ ሲሆን ውጤቱም ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ ዘጠኝ፡- የተግባቦት ተግባራት ክንውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ምልከታው ያተኮረባቸው ተግባራት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | ብዛ | % | ብዛት | % |
| 3.1 | መምህሯ/ሩ ሁልጊዜ ተናጋሪ ብቻ ሳትሆን/ሳይሆን የተማሪዎችን ሃሳብ ማዳመጥ | 5 | 83.3 | 1 | 16.6 |
| 3.2 | ተማሪዎች ባልገባቸው ሃሳብ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብሎ ማስተናገድ | 5 | 83.3 | 1 | 16.6 |
| 3.3 | ተማሪዎች እንዲፈርዋት/እንዲፈሩት የሚያደርግ ቋንቋ በመጠቀም መቅረብ | 1 | 16.6 | 5 | 83.3 |
| 3.4 | የመምህሯ/ሩ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፍ የሚችል መሆን | 0 | - | 6 | 100 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያስረዳው ተተኳሪ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን ሃሳብ የማዳመጥ ክህሎታቸውን በተመለከተ አምስቱም መምህራን በጥሩ ሁኔታ ተግባሩን ሲያከናውኑ የቀሩት አንዱ መምህር ግን ትምህርቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ

ተማሪዎችን ሳያሳትፍ ያስተምራል። ሲደወል ከ 4-3 ደቂቃ ሲቀረው ብቻ ተማሪዎች ጥያቄ ካላቸው ይጠይቃል ካልተሳተፉ ወጥቶ ይሄዳል። በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎች ባልገባቸው ሃሳብ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብሎ ማስተናገድን በተመለከተ የተገኘው መረጃ አምስቱ መምህራን በተሻለ ደረጃ ተግባራዊ ሲያደርጉ ተስተውለዋል ። አንድ መምህር ግን ይህን ተግባር ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም። በአንፃሩ አንድ ተማሪ ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን አስታውሶ ሲጠይቅ መምህሩ ‹‹. . . ትናንት የትነበርክ አሁን የጠየቅከውን ጥያቄ ትናንት አስተምሬዋለሁ። ነው ወይስ አዋቂ የሆንክ መሰለህ. . .” በማለት ትህትና ባልተላበሰ አገላለጽ ምላሽ ሲሰጡ ተስተውለዋል። በተጨማሪም ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች እንዲፈርዋቸው የሚያደርግ ቋንቋ በመጠቀም መቅረብን በተመለከተ አምስቱ መምህራን ይህን ተግባር ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም። የቀሩት አንድ መምህር ግን ሀይለ ቃል በተሞላበት አገላለጽ ተማሪዎች እንዲፈሩ የሚያደርግ ቋንቋ ሲጠቀሙ ተስተውለዋል። በሌላም በኩል የመምህራኑ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፉ የሚችሉ መሆናቸውን በተመለከተ ስድስቱም መምህራን ይህን ተግባር እንደማያከናውኑ በምልከታ ጊዜ ተረጋግጧል።

በአጠቃላይ የምልከታ ውጤት እንደሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ የተማሪዎችንም ሃሳብ በተገቢው መንገድ እንደሚያዳምጡ እና ተማሪዎች ባልገባቸው ሃሳብ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብለው የማስተናገድ ትግበራቸው የተሻለ መሆኑን ነው። በተጨማሪም አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች ፈርተው እንዲያከብሯቸው የሚያደርጉ ቋንቋዎችን ተጠቅመው እንደማይቀርቡ ጭምር ከምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ይህም ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን በተራ ቁጥር 3.4 በቀረበው ጥያቄ የተተኳሪ መምህራኑ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፍ የሚችሉ አለመሆናቸው ከምልከታ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ነገር ግን ከመምህራን ቃለመጠይቅ ምላሽ የተገኘው መረጃ ከዚህ የተለየ ነው።

በሌላም በኩል ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ማሳተፋቸውን በተመለከተ ለተጠኚ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስር፡- የተግባቦት ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡-

| ተ.ቁ | የክፍል አመራር ክንውኖች | በጣም እስማማሁለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2.1 | መምህራችሁ ምን ጊዜም ተናጋሪ ብቻ ሳትሆን/ ሳይሆን የተማሪዎችን ሃሳብ ታዳምጣለች/ያዳምጣል/ | 41 | 27.3 | 67 | 44.6 | 28 | 18.6 | 12 | 8 | 2 | 1.3 |
| 2.2 | ተማሪዎች ባልገባቸው ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብላ/ብሎ ተገቢውን ምላሽ ትሰጣለች/ይሰጣል፡፡ | 18 | 12 | 71 | 47.3 | 40 | 26.6 | 21 | 14 | - | - |
| 2.3 | ተማሪዎች እንዲፈርዋት/ፈሩት የሚያደርግ ቋንቋ በመጠቀም ትቀርባለች/ ይቀርባል | 5 | 3.3 | 23 | 15.3 | 7 | 4.6 | 81 | 54 | 3 | 18 |
| 2.4 | የመምህሯ/ሩ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፉ የሚችሉ መሆን | 20 | 13.3 | 31 | 20.6 | 7 | 4.6 | 92 | 61.3 | - | - |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያመለክተው የመምህራኑ የተግባቦት ተግባራትን ክንውን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ ስለሆነም ተተኳሪ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ምን ጊዜም ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ የተማሪዎችን ሃሳብ ማዳመጣቸውን በተመለከተ 41 ተማሪዎች (27.3%) በጣም እንስማማለን፣ 67 ተማሪዎች(44.6%) እንስማማለን፣ 28 ተማሪዎች(18.6%) መወሰን ይቸግረናል እንዲሁም 12 ተማሪዎች (8%) አንስማማም እና የተቀሩት 2 ተማሪዎች (1.3%) ፈፅሞ እንደማይስማው ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ባልገባቸው ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብሎ ተገቢውን ምላሽ መስጠታቸውን በተመለከተ 18 ተማሪዎች (12%) በጣም እንስማማለን፣ 71 ተማሪዎች

(47.3 %) እንስማማለን፣ 40 ተማሪዎች ( 26.6% ) መወሰን ይቸግረናል፣ እና 21 ተማሪዎች (14%) አንስማማም በማለት ምላሻቸውን የሰጡ ሲሆን መምህራን ተማሪዎች እንዲፈረዋቸው የሚያደርግ ቋንቋ መጠቀማቸውን በተመለከተ 5 ተማሪዎች (3.3%) በጣም እንስማማለን፣ 23 ተማሪዎች (15.3%) እንስማማለን፣ 7 ተማሪዎች ( 4.6% ) መወሰን ይቸግረናል እና 81 ተማሪዎች (54%) አንስማማም እንዲሁም 27 ተማሪዎች (18%) በጣም አለመስማማታችቸውን ገልፀዋል፡፡

በሌላም በኩል የተተኳሪ መምህራኑ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፍ የሚችል መሆኑን በተመለከተ 20 ተማሪዎች (13.3%)በጣም እንስማማለን፣ 31 ተማሪዎች (20.6%) እንስማማለን እንዲሁም 7 ተማሪዎች (4.6%) መወሰን እንደሚቸግራቸው እና የተቀሩት 92 ተማሪዎች (61.3%) ደግሞ እንደማይስማሙ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው የተማሪዎች ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ተተኳሪ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ምንጊዜም ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ ተማሪዎች የሚሰነዝሯቸውን ሃሳቦች የማዳመጥ ትግበራቸው ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ባልገባቸው ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብሎ ተገቢውን ምላሽ መስጠትን በተመለከተ የመምህራኑ ትግበራ የተሻለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች እንዲፈሯቸው የሚያደርግ ቋንቋ ተጠቅመው እንደማይቀርቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላም በኩል የመምህራኑ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፉ የሚችሉ አለመሆናቸው የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ ይህ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ በብዛት በምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር እንዲሁም በተወሰነ መልኩ ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ተግባቦታዊ ተግባራት በተገቢው መንገድ የመተግበራቸው ችሎታ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.2. Moore (2001)፣ Undrwood (1987) እና Congelosi (1997) የተግባቦት ተግባራትን በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶችን አቅርበዋል፡፡ ይኸውም የመግባባት ችሎታ በመማር ማስተማር ሂደት ጥሩ የማስተማር ክንውን እንዲኖር የሚያደርግ ነው፡፡ ጤናማ የሆነ የመምህርና የተማሪዎች ግንኙነት ለትምህርቱ ስኬታማነት ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ሲባል መምህሩ ብቻ ተናጋሪ ተማሪው አድማጭ ሳይሆን ከዚህ በተሻለ መልኩ አጠቃላይ የመማሪያ ክፍሉን ስርአት ማስተካከልና መምራትንም ጭምር የያዘ መሆኑ መታወቅ

ይኖርበታል፡፡ መምህራን በትክክል የተማሪዎቻቸውን ሃሳብና አመለካከት ተረድተው መግባባት ላይ ከደረሱ የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት ለመለየት የትምህርቱን አላማም ለመወሰንና የክፍል ውስጥ ተግባራትን ለማዘጋጀት ከሚያስችል ውሳኔ ላይ መድረስ ይችላሉ፡፡ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.2 Undrwood (1987) እና Moore (2001) ከጠቀስዋቸው ዝርዝር ጉዳዮች አንፃር የተተኳሪ መምህራኑ የአተገባበር ችሎታ የተሻለ መሆኑን ከምልከታ፣ ከጽሑፍ መጠይቅ እና በከፊል ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን የመምህራን የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት የማሳተፋቸው ሁኔታ በተመለከተ መምህራኑ በቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የተሻለ መሆኑን ቢገልጽም በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ግን የመምህራኑ ትግበራ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም የመምህራኑ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፉ የሚችሉ ያለመሆናቸው ምክንያት ምናልባትም የመምህራኑ የማስተማር ልምድ አነስተኛ ከመሆኑ አንፃር የማስተማሪያ ስልቶቹን እንዴት መምረጥና መጠቀም እንዳለባቸው የማወቃቸው ሁኔታ ያልዳበረ በመሆኑ፣ ከመደበኛው ትምህርት ውጭ ሌሎች ተግባቦታዊ የሆኑ ተግባራትን ክፍል ውስጥ አምጥቶ ተግባራዊ ለማድረግ በሳምንት የተመደበው ክፍለ ጊዜ ስለማይበቃ ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ የራሱን አስተያየት ሰጥቷል፡፡

### 4.2.4. የቅጣት ተግባር

በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ ለሚፈጠሩ የሥነ ስርዓት ችግሮችን ለመከላከል የቋንቋ መምህራን ከሚወስዷቸዉ እርምጃዎች አንዱ ቅጣት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.6. ላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም መምህራን በክፍል ውስጥ በተማሪዎች የሚከሰቱ የሥነ ስርዓት ችግሮችን ለመቆጣጠር የተለያዩ የሥነ ስርዓት እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በተማሪዎች ላይ የሚወሰዱ አካላዊ ቅጣቶች፣ ከክፍል ማስወጣት፣ መምከር፣ መስደብ ወዘተ... ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ለተተኳሪ መምህራን የቅጣት ተግባራትን አተገባበር በተመለከተ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ እንደተማሪ ሊላበሱት የሚገባው ሥነ ምግባር ምን መሆን እንዳለበት የማስታወስ (የማሳወቅ) ትግበራቸው በተመለከተ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው አራቱም መምህራን ምን ጊዜም ተማሪዎች እንደተማሪ ሊኖራቸው የሚገባ ሥነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት እንደሚነግሯቸው ገልፀዋል፡፡ የተቀሩት ሁለት መምህራን ደግሞ አብዛኞቹ ተማሪዎች ታዛገሮች አይደሉም፡፡ ከዚህም አንፃር ምንም ዓይነት አስተያየትም ሆነ ምክር ቢለገሳቸው ተግባራዊ የሚያደርጉ

ባለመሆናቸው ትርፉ ድካም ነው ብሎ በማሰብ ተግባሩን እንደማያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ ተገቢ የሆነ ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እንዳላየ ሆኖ የማለፋቸውን ሁኔታ በተመለከተ ስድስቱም መምህራን ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ እንዳላየ ሆነው ሳይሆን የሚያልፉት አስፈላጊ ነው ብለው የሚያስቡትን እርምጃ እንደሚወስዱ ገልፀዋል፡፡ ይህም ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚጠቁመው አብዛኞቹ መምህራን የመማር ማስተማሩን ሂደት ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ እንደተማሪ ሊላበሱት የሚገባውን ሥነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት፣ ግዴታቸውን እና መብታቸውን እንዲያውቁ የማድረግ ተግባራትን እንደሚያከናውኑ እና ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ፡- የቤት ስራ ባይሰሩ፣ መጽሐፍ ባያመጡ ወዘተ.. ያን ያደረጉበት ምክንያት ተረድተው ተገቢ የሆነውን ምክር ከመለገስ ይልቅ ከክፍል ማስወጣትን እንደ ቅጣት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ነው፡፡ በሌላም በኩል ይህን የቅጣት ተግባር በተመለከተ በተተኳሪ መምህራኑ ላይ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ምልከታ የተካሄደባቸው ሲሆን ውጤቱም ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ አስራአንድ፡- የመምህራን የቅጣት አሰጣጥ ተግባራትን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ፡፡

| ተ.ቁ | ምልከታው ያተኮረባቸው ተግባራት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4.1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ሊያንፀባርቁት የሚገባው ባህሪ ምን መምሰል እንዳለበት ማስታወስ | 2 | 33.3 | 4 | 66.6 |
| 4.2 | ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ (የቤት ስራ ባይሰሩ፣ መጽሐፍ ባያመጡ) ተገቢ የሆነ ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እንዳላየ ሆኖ ማለፍ | 1 | 16.6 | 5 | 83.3 |

ከላይ በሠንጠረዥ አስራአንድ የቀረበው የምልከታ መረጃ እንደሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ሊላበሱት የሚገባቸው ሥነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት ማስታወስን በተመለከተ ሁለት መምህራን ተማሪዎች መጽሐፍ ሳያመጡ ሲቀሩ፣ ሲረብሹ ወዘተ ምንም እንኳ በተሰላቸ እና ሃይለቃል በተሞላበት አገላለጽ ቢሆንም ተማሪዎች እንደ መሆናቸው መጠን መጽሐፍ ይዘው መምጣት እንዳለባቸውና ትምህርቱን

በጥሞና መከታተል እንደሚገባቸው ሲናገሩ ተስተውለዋል። በአንፃሩ አራቱ መምህራን ይህን ተግባር ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም።

በሌላም በኩል ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ (የቤት ስራ ባይሰሩ፣ መጽሐፍ ባያመጡ፣ ቢረብሹ ወዘተ) ተገቢ የሆነ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እንዳላየ ሆኖ የማለፋቸውን ሁኔታ በተመለከተ አንድ መምህር ነገሮችን አይተው እንዳላዩ እንደሚያልፉ ከምልከታ የተገኘው መረጃ ያስረዳል። የተቀሩት አምስት መምህራን ግን ተማሪዎች የትኛውንም አይነት ጥፋት ሲያጠፉ በብዛት መጽሐፍ ይዘው አለመምጣት፣ ማን እንዳወራ መለየት እስከማይቻልበት ደረጃ ድረስ መንጫጫት ወዘተ... የመሳሰሉ ጥፋቶች ሲፈጸሙ ተገቢ ነው ብለው የሚያስቡትን እርምጃ ሲወስዱ ተስተውለዋል። አብዛኞቹ መምህራን የሚወስዷቸው እርምጃዎች በብዛት ከክፍል ማስወጣት፣ አልፎ አልፎም ማንበርከክ እና መማታት የመሳሰሉትን ቅጣቶች ተግባራዊ ሲያደርጉ ተስተውለዋል።

በሌላም በኩል በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ለሚፈፅሟቸው ጥፋቶች የመምህራን የቅጣት አተገባበር ሁኔታ በተመለከተ ለተጠኝ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፡- የመምህራን የቅጣት አተገባበርን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የክፍል አመራር ክንውኖች | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3.1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ሊያንጸባርቁት የሚገባ ባህሪ ምን መምሰል እንዳለበት ታስታውሳለች ያስታውሳል። | 40 | 26.6 | 60 | 40 | 10 | 6.6 | 10 | 6.6 | 30 | 20 |
| 3.2 | ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ መጽሐፍ ባያመጡ የቤት ስራ ባይሰሩ፣ ቢረብሹ ወዘተ.. ከመምከር ይልቅ ከክፍል ማስወጣት እና አካላዊ ቅጣት ትፈፅማለች/ ይፈፅማል። | 50 | 33.3 | 60 | 40 | 21 | 14 | 9 | 6 | 10 | 6.6 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያመለክተው የተተኳሪ መምህራኑ የቅጣት አሰጣጥ ትግበራቸው በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ ስለሆነም መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ሊያንፀባርቁትና ሊላበሱት የሚገባ ስነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት ማስታወስን በተመለከተ 40 ተማሪዎች (26.6%) አዎንታዊ ምላሻቸውን በመስጠት በጣም እንስማማለን፣ 60 ተማሪዎች (40%) እንስማማለን፣ 10 ተማሪዎች (6.6%) ደግሞ ለመወሰን እንቸገራለን፣ 10 ተማሪዎች (6.6%) አንስማማም እና የተቀሩት 30 ተማሪዎች (20%) ደግሞ ፈፅሞ አለመስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ መጽሐፍ ባያመጡ፣ የቤት ስራ ባይሰሩ፣ ቢረብሹ ወዘተ. መክሮ ለማስተካከል ከመጣር ይልቅ አከላዊ ቅጣትን እና ከክፍል ማስወጣትን እንደርምጃ የመጠቀማቸውን ሁኔታ በተመለከተ 50 ተማሪዎች (33.3%) በጣም እንስማማለን፣ 60 ተማሪዎች (40%) እንስማማለን፣ 21 ተማሪዎች (14%) ደግሞ ለመወሰን ይቸግረናል 9 ተማሪዎች (6%) አንስማማም እና የተቀሩት 10 ተማሪዎች (6.6%) ፈፅሞ እንደማይስማሙ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ የቀረበው መረጃ የሚያስረዳው ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ እንደተማሪ ሊላበሱት የሚገባቸውን ሥነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት የማሳወቅ ትግበራቸው በጥሩ ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያመለክት ነው፡፡ በሌላም በኩል ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ መጽሐፍ ባያመጡ፣ የቤት ስራ ባይሰሩና ቢረበሹ ምክርን ለግሶ ለማረቅ (ለማስተካከል) ከመጣር ይልቅ አካላዊ ቅጣትን እና ከክፍል ማስወጣት እንደ አንድ የቅጣት ተግባር መፈፀማቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

ይህ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ በተወሰነ መልኩ ከምልከታ እና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ከተገኙት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይህም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ እንደተማሪ ሊያንፀባርቁት የሚገባ ባህሪ ምን መምሰል እንዳለበት ማስታወሱን አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን ተግባራዊ እንደሚያደርጉት በቃለመጠይቅ ምላሻቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ተማሪዎች እና መምህራኑ የሰጡት ተመሳሳይ መረጃ ምናልባትም ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት በነበሩት ጊዜያት ተግባራዊ ተደርጎ ካልሆነ በስተቀር አጥኝዋ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ባደረገችው ምልከታ ግን ይህ ተግባር ሲከናወን አልተስተዋለም፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ማንኛውንም አይነት ጥፋት ሲያጠፉ ተገቢ የሆነውን ምክር ለግሶ ከማስተካከል ይልቅ ተማሪዎች ትምህርቱን አቋርጠው ከክፍል

እንዲወጡ ማድረግ፣ አካላዊ ቅጣትን እንደ አንድ እርምጃ ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ ከተማሪዎቹ እና ከምልከታ የተገኘው መረጃ በእጅጉ የሚመሳሰል ሲሆን ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ጋር ደግሞ በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰል ነው፡፡ ይህም መምህራኑ ተማሪዎች መጽሐፍ ሳያመጡ ሲቀሩ፣ ሲረብሹ፣ የቤት ስራ ሳይሰሩ ሲመጡ አብዛኞቹ መምህራን ዝም ብሎ ከማለፍ ይልቅ ተገቢነው ብለው የሚያስቡትን ርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ነገር ግን የሚወስዷቸው እርምጃዎች በብዛት ተማሪዎች ትምህርቱን አቋርጠው ከክፍል እንዲወጡ ማድረግ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ማንበርከክ እና አንዳንድ ጊዜ ወደ ክፍል ሲገቡ ይዘውት በሚገቡት ለበቅ በመምታት አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን የቅጣት ተግባራቸውን እንደሚተገብሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.6. Good & Brophy (1997) እና Moore (1982) እንደገለጹት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከክፍል በማስወጣት እና ትምህርቱን በማቋረጥ ቅጣት ለመውሰድ ከመፍጠን ይልቅ ተማሪዎች ከክፍል ውስጥ ሆነ ውጭ ማሳየት ያለባቸውን ባህሪያት በማስተማሩ አሊያም በትምህርቱ ላይ በማተኮር ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸውን ተማሪዎች መፍጠር አለባቸው :: በተጨማሪም እንደ ምሁራኑ ሐሳብ የሥነ ስርአት ርምጃ መውሰድ ማለት ክፍልን ማስተዳደር ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም የክፍል ውስጥ አመራርን ውጤታማ ለማድረግ ቅጣት ኅታች ነው፡፡ ስለሆነም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሥነ ስርዓት ሲጓደል ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የሚከተሉትን ጠቃሚነት ያላቸውን ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

- በመጀመሪያ ደረጃ ምን እንደተደረገ በጥልቀት መመርመርና ያጠፉትን ተማሪዎች ለየብቻቸው ነጣጥሎ ሁኔታዎችን በመጠየቅ ማጣራትና ማወቅ ይገባል፡፡
- ጥፋት ፈፃሚውን ለይቶ የጥፋቱን ተጠያቂ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡
- ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባውን የተሻለውን ሥነ ምግባር ማሳየት እንዲከተሉት መገፋፋት፣ ሊከተሉት የማይገባውን ረብሻን፣ መጥፎነትን ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳይ ሁሉ መንገር፡፡

ከዚህም አንፃር ተተኳሪ መምህራኑ ከላይ Good & Brophy (1987) የጠቀሷቸውን ተግባራት በተገቢው መንገድ የማከናወን ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ከምልከታና ከጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም በተወሰነ መልኩ ከመምህራን ቃለመጠይቅ ከተገኘው መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በቅጣት አሰጣጥም ሂደት ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ያለመከናወናቸው ምክንያት ምን ሊሆን

እንደሚችል ጥናቱ ለመገንዘብ የሞከረ ሲሆን ለዚህም እንደዋነኛ ነጥብ ሊነሳ የሚችለው አብዛኞቹ መምህራን የገዘፈ አቋም የላቸውም ከዚህም አንፃር ተማሪዎች ይንቁናል ብለው ስለሚያስቡ ተማሪዎችን ከስተር ባለ አካሄድ ከክፍል ማስወጣት፣ አካላዊ ቅጣት በመፈፀም መቅጣቱ ተማሪዎች ቅጣቱን ፈርተው ሊስተካከሉ እና እኛንም ሊያከብሩን ይችላሉ ብሎ ማሰብ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በአጠቃላይ ስለቅጣት አሰጣጥ በቂ የሆነ ግንዛቤ ማጣት እና የክፍል አመራር ክህሎት ላይ በቂ የሆነ ስልጠና አለማግኘት የመሳሰሉት እንደምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

ከዚህም አንፃር ከምልከታው፣ ከጽሑፍ መጠይቁ እንዲሁም በቃለ መጠይቁ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ሊያንቀፀባርቁት የሚገባውን ባህሪ ምን መምሰል እንዳለበት የማሳወቅ ሁኔታቸው የተሻለ ቢሆንም ተማሪዎች ማንኛውንም አይነት ጥፋት ፈፅመው ሲገኙ ተማሪዎችን ከክፈል ማስወጣት፣ማንበርከክ፣ መምታት የመሳሰሉትን የቅጣት ተግባራት ከማከናወን በስተቀር ተማሪዎችን መክሮ የማረቅ ትግበራቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡

### 4.2.5. የመምራት ችሎታ

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.7 ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራን ተግባራዊ ማድረግ ካለባቸው የክፍል ስራዎች ውስጥ አንዱ ተማሪዎች ምን መቼ እና እንዴት መስራት እንዳለባቸው ግልፅ መመሪያ ማስተላለፍ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ መምህር ለተማሪዎቹ ምን እንዴት መሰራት እንዳለባቸው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ግልፅ የሆነ መመሪያ ካልሰጠ በክፍል ውስጥ የሥነ ስርአት ወይም የአፈፃጸም ችግር ይገጥመዋል (Harmer 1991)፡፡ በዚህም መሠረት የተተኳሪ መምህራኑ የመምራት ስልት እና ችሎታቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ ለዚህም ስድስቱም መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልጽ የሆነ መመሪያ እንደሚሰጡ እንዲሁም ሁለት መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ምንም አይነት ስህተት ፈፅመው እንዲገኙ የማይፈለጉ መሆናቸው ሲገልጹ የተቀሩት አራት መምህራን ግን እንዲህ አይነቱን አቋም እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

በሌላም በኩል ስድስቱም መምህራን የተማሪዎችን ችግር እንደራስ በመቁጠር ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ በስተመጨረሻም አራቱ መምህራን ሁሉም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ እንደሚፈጥሩ የገለጹ ሲሆን የተቀሩት ሁለት መምህራን ግን ያለው የጊዜ ማነስ እና የተማሪዎቹ አለመብሰል እንደዚህ አይነቱን ተግባር ለማከናወን እንደማይመቻቸው አስረድተዋል፡፡ ይህ ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች ለሚሰርዋቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልፅ የሆነ መመሪያ እንደሚሰጡ፤ተማሪዎች ምንም አይነት ስህተት መፈፀም የለባቸውም የሚል አቋም እንደሌላቸው ዲሞክራት አመራር እንደሆኑ፤ የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር በመቁጠር ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት የሚጥሩ መሆናቸውን እንዲሁም ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ እንደሚያመቻቹ ገልፀዋል፡፡

በሌላም በኩል የመምህራኑን የመምራት ችሎታ በተመለከተ በተተኪሪ መምህራኑ ላይ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ምልከታ የተካሄደ ሲሆን ውጤቱም ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

ሠንጠረዥ አስራ ሦስት፡- የመምህራን የአመራር ሰጭነት አተገባበር በተመለከተ ምልከታዊ መረጃ

| ተ.ቁ | ምልከታው ያተኮረባቸው ተግባራት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5.1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልፅ የሆነ መመሪያ መስጠት፣ | 3 | 50 | 3 | 50 |
| 5.2 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምንም አይነት ስህተት ፈፅመው እንዳይገኙ አለመፈለግ፣ | 3 | 50 | 3 | 50 |
| 5.3 | የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር በመቁጠር ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት መጣር፣ | 0 | 0 | 6 | 100 |
| 5.4 | ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ እንዲያዳብሩ እድል መስጠት፣ | 1 | 16.6 | 5 | 83.3 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያስረዳው ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚያከናውንዋቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልጽ የሆነ መመሪያ መስጠትን በተመለከተ ሶስት መምህራን በትክክል ተግባሩን ሲያከናወኑ የተቀሩት ሶስት መምህራን ደግሞ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ተግባሩን ሲያከናወኑ አልተስተዋሉም፡፡

ከዚህም የምንረዳው መምህራኑ ተማሪዎች በሚሰርዋቸው ስራዎች ላይ አስቀድመው ግልጽ የሆነ መመሪያ የመስጠት ችሎታቸውን መሳ ለመሳ የሚመሰጠው መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ምንም አይነት ስህተት ፈጽመው እንዲገኙ አለመፈለጋቸውን በተመለከተ የተገኘው መረጃ ሦስት መምህራን ተማሪዎች ምንም አይነት ስህተት መፈጸም የለባቸውም የሚል አቋም ያላቸው ሲሆን ይህም የአምባገነን አመራር ባህሪይ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.7.1. ተገልጿል በአንፃሩ የተቀሩት ሶስት መምህራን ደግሞ ተማሪዎች ምንም ዓይነት ስህተት መፈጸም የለባቸውም የሚል አቋም ይዘው የራሳቸውን የበላይነት በማወጅ ሲያስተምሩ አልተስተዋሉም፡፡ ይህ ደግሞ የዲሞክራሲያዊ አመራር ባህርይ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.7.2. ተገልጿል፡፡

በሌላም በኩል የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግርበመቁጠር ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት የመጣር ችሎታቸውን በተመለከተ ስድስቱም መምህራን ይህን ተግባር አላከናወኑም፡፡ በመጨረሻም መምህራን ሁሉንም ከገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች ርስበርስ የሚተራረሙበትን መንገድ እንዲያጎለብቱ እድል መስጠትን በተመለከተ አንዱ መምህር የዘይቤ አይነቶችን ከፋፍሎ ለተማሪዎች የቤት ሥራ ሲሰጥ "እኔ ይህንን መስራት አልፈልግም ይቀየርልኝ" የሚሉ ተማሪዎች ሲያጋጥሙት ይህንን ጉዳይ ራሳቸው ተማሪዎች ተነጋግረው መቀየር በፈለጉት ርዕስ እንዲቀያየሩ ዕድሉን በመስጠት ተግባሩን በተወሰነ መልኩ ሲያከናውኑ ተስተውለዋል፡፡ የተቀሩት አምስት መምህራን ግን ተማሪዎች ችግሮቻቸውን እርስ በርሳቸው ተነጋግረው እንዲፈቱ በማድረግ ሳይሆን ከቻሉ መምህራኑ ራሳቸው ለመፍታት ሲጥሩ አሊያም እንዳላየ እና እንዳልሰማ ሆነው ማለፋቸው በምልከታ ጊዜ ተስተውሏል፡፡

በአጠቃላይ ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰሯቸው ትምህርታዊ ተግባራት አስቀድመው ግልጽ የሆነ መመሪያ የመስጠት ክህሎታቸው እና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምንም አይነት ስህተት ፈፅመው እንዲገኙ አለመፈለግ በተመለከተ የተተኳሪ መምህራኑ ችሎታና አመለካከት መሳ ለመሳ (በመካከለኛ ደረጃ) የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ በሌላም በኩል ተተኳሪ መምህራኑ

በተማሪዎች ላይ ለሚታዩ ማናቸውም ችግሮች እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ የመፍጠር እና የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር በመቁጠር ችግራቸውን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት የመጣራቸው ችሎታ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል። ሆኖም ግን ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው አብዛኞቹ መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን የአመራር ስጭነት ተግባራት በተገቢው መንገድ እንደሚተገብሩ ነው።

በሌላም በኩል የተጠቀሱት የአመራር ስጭነት ተግባራት በተገቢው መንገድ ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ ለተጠኝ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራአራት፡- የመምህራን አመራር ስጪነት ችሎታ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የክፍል አመራር ክንውኖች | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4.1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰርዋቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልፅ የሆነ መመሪያ አስቀድማ/ሞ ትሰጣለች/ ይሰጣል | 13 | 8.6 | 67 | 44.6 | 15 | 10 | 40 | 26.6 | 25 | 16.6 |
| 4.2 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ምንም አይነት ጥፋት እንዳያጠፉ አትፈልግም/አይፈልግም | 16 | 10.6 | 53 | 35.3 | 17 | 11.3 | 40 | 26.6 | 24 | 16 |
| 4.3 | ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ እንዲያዳብሩ እድል ትሰጣለች/ ይሰጣል | 9 | 6 | 20 | 13.3 | 11 | 7.3 | 70 | 46.6 | 40 | 26.6 |
| 4.4 | የተማሪዎችን ችግር እንደእራስ ችግር በመቁጠር ችግሩን በውይይትና በምክክር ለመፍታ ት ትጥራለች / ይጥራል። | - | | 10 | 6.6 | 8 | 5.3 | 70 | 46.6 | 62 | 41.3 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያመለክተው መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰሯቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልጽ የሆነ መመሪያ የመስጠት ችሎታቸውን በተመለከተ 13 ተማሪዎች (8.6%) በጣም እንስማማለን፣ 67 ተማሪዎች (44%) እንስማማለን፣ እንዲሁም 15 ተማሪዎች (10%) መወሰን ይቸግረናል፣ 40 ተማሪዎች (26.6%) አንስማማም የተቀሩት 25 ተማሪዎች(16.6%) ደግሞ ፈፅሞ እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መምህራኑ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ምንም አይነት ጥፋት እንዲያጠፉ አለመፈላጋቸው በተመለከተ 16 ተማሪዎች (10.6 %) በጣም እንስማማለን፣ 53 ተማሪዎች (35.3%) እንስማማለን፣ 17 ተማሪዎች (11.3%) መወሰን ይቸግረናል፤ እንዲሁም 40 ተማሪዎች (26.6%) አንስማማም እና የተቀሩት 24 ተማሪዎች (16%) ደግሞ ፈፅሞ አለመስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ በሌላም በኩል ተተኳሪ መምህራኑ ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርስ የሚተራረሙበትን መንገድ እንዲያዳብሩ እድል መስጠታቸውን በተመለከተ 9 ተማሪዎች (6%) በጣም እንስማማለን፣ 20 ተማሪዎች (13.3%) እንስማማለን፣ 11 ተማሪዎች (7.3%) መወሰን ይቸግረናል፣ እንዲሁም 70 ተማሪዎች (46.6%) አንስማማም እና የተቀሩት 40 ተማሪዎች (26.6%) በጣም አንስማማም በማለት ምላሻቸውን የሰጡ ሲሆን የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር በመቁጠር ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት መጣራቸውን በተመለከተ 10 ተማሪዎች (6.6%) እንስማማለን፣ 8 ተማሪዎች (5.3%) መወሰን ይቸግረናል፣ 70 ተማሪዎች (46.6) አንስማማም እና የተቀሩት 62 ተማሪዎች (41.3%) ደግሞ ፈፅሞ እንደማይስማሙ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ የቀረበው የተማሪዎች መረጃ እንደሚያስረዳዉ ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰርዋቸው ትምህርታዊ ተግባራት አስቀድመው ግልፅ የሆነ መመሪያ የመስጠታቸው ችሎታ መሳ ለመሳ (በመካከለኛ ደረጃ) ላይ የሚገኝ መሆኑን ሲያመላክት በተጨማሪም አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ምንም አይነት ጥፋት ፈፅመው መገኘት የለባቸውም የሚል አቋም እንደሌላቸው የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ሆኖም ግን መምህራኑ ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን እድል የመስጠት ክህሎታቸው እና የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር በመቁጠር ችግሩን በውይይትና በምክክር ለመፍታት የመጣር

ክህሎታቸው በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ ይህ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ባብዛኛው ከምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር እንዲሁም በተወሰነ መልኩ ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ ምላሽ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.7. Good and Brophy (1987) አንድ የቋንቋ መምህር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚሰርዋቸው ስራዎች ግልፅ የሆነ መመርያ የሚሰጥ ከሆነ ተማሪዎች ምን ለምን እና እንዴት መስራት እንዳለባቸው አስቀድመው ስለሚረዱ በቀረበው ትምህርት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ከፍ ያለ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡ ምሁራኑ ካነሱት ሀሳብ አንፃር ተተኳሪ መምህራኑ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት የማከናውናቸው ሀኔታ የተሻለ መሆኑን ከምልከታ እና ከጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም ከመምህራን ቃለመጠይቅ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.7.2. Arends (1997) እንደገለጹት ዲሞክራሲያዊ አመራር በመማር ማስተማር ወቅት በክፍል ውስጥ ብሩህ ድባብ በመፍጠር ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ የሚጥር ከተማሪዎች ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት ያለው እና ተማሪዎች ቢያጠፉ እንደነውር ሳይቆጥር ለማስተካከል የሚተጋ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ተተኳሪ መምህራኑ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት የማከናወናቸው ሁኔታ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ከምልከታና ከጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙት መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላም በኩል በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.7.2. Moore (2001) ያነሱት ሃሳብ ሃላፊነትን አብሮ የመውጣት ስሜት የዲሞክራት መምህር ባህሪ ነው፡፡ ይህ አይነት አመራር በማዘዝና በመታዘዝ ሳይሆን በማበረታታት ችግርን መፍታት እንዲቻል ያደርጋል፡፡ ሲያስተምርም ተማሪዎች በበቂ ሁኔታ በክፍል ውስጥ በሚያከናውኑት ማንኛውም ተግባር ላይ ያሳትፋል፣ ሃሳብ እንዲሰጡና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ፣እርስ በርስ እንዲወያዩ ይፈቅዳል፣ የተማሪዎች ችግር የራሱ ችግር እንደሆነ አስቦ ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት መጣር የዲሞክራት አመራር ባህሪ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ተተኳሪ መምህራኑ ከላይ የተጠቀሱት የአመራር ሰጭነት ተግባራት የማከናወናቸው ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆነና በከፊልም የአምባገነናዊ አመራር ባህሪ እንደሚስተዋልባቸው ከምልከታ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የአመራር ስልት የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት የሚቀንስ እና በክፍል አመራር ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.7.1. ተገልጿል። በአተገባበሩም ሂደት ከላይ እነ moore (2001) የጠቀሷቸውን ተግባራት ያለማከናወናቸው ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ

ለመገንዘብ የሞከረ ሲሆን ለዚህም እንደዋነኛ ነጥብ ሊነሳ የሚችለው ተተኳሪ መምህራኑ በክፍል አመራር አለባውያን ላይ በቂ የሆነ ስልጠና ወይም ትምህርት አለማግኘታቸው እንዲሁም በራሳቸው ተነሳሽነት የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉ መፃሕፍትን አለማንበባቸው እንደሆነ ለመገመት ተችሏል።

### 4.2.6. ምቹ ሁኔታን መፍጠር

ለክፍል ውስጥ አመራር ስኬት ሌላኛው አስፈላጊ ነገር የመምህሩና የክፍሉ አጠቃላይ ገፅታ አመቺነት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.9 ተገልጿል። በመሆኑም ስኬታማ እና ታታሪ መምህር ምን ጊዜም የመማሪያ ክፍሉን ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ግድግዳዎቹ ሁሉ ስለት ምህረት እንዲናገሩ ያደርጋል። ለምሳሌ ክፍል ማደራጀት፣ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን መጠቀም፣ የክፍሉን ንፅህና መጠበቅ፣ ለተማሪዎች የተመቻቸ አቀማመጥ መፍጠር ወዘተ. ይመለከታል። ከዚህም አንፃር በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ክህሎታቸውን በተመለከተ ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር። በዚህም መሠረት ሶስት መምህራን ከመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ አጋዥ መጻሕፍትን በመጠቀም፣ መረጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም፣ የመማሪያ ክፍሉን ንፅህና በማስጠበቅ፣ ተማሪዎችን እርስ በርሳቸው እያወያዩ በማስተማር በተቻላቸው መጠን ለመማር ማስተማሩ ስኬት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንደሚተጉ አስረድተዋል ። በአንፃሩ የተቀሩት ሶስት መምህራን ደግሞ የመማሪያ ክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ለማድረግ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት እንደማያከናውኑ ገልፀዋል። ለዚህም እንደምክንያት ያነሱት በተለይ የወንበሮችን አደረጃጀት በተመለከተ ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ድርሻ ካልተወጡ በስተቀር ተግባራቱ በመምህራን አቅም ብቻ ሊከናወኑ እንደማይችሉ እና በትምህርት ቤቱ የተዘጋጁ መርጃ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖሩን እንደሆነ ነው።

በአጠቃላይ ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ መረዳት የሚቻለው ከስድስቱ ተተኳሪ መምህራን ውስጥ ሶስቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥሩ የገለፁ

ሲሆን የተቀሩት ሶስት መምህራን ግን በትምህርት ቤቱ በቂ የሆነ የተደራጁ መርጃ መሳሪያዎች አለመኖር፣ ተማሪዎች የተለየ ነገር ለማወቅ ያላቸው ፍላጎት አናሳ መሆን፣ የመማሪያ ክፍሉ

ሁኔታ በተለይ የወንበሮቹ አደረጃጀት ተማሪዎች አመቺ በሆነ መንገድ አቀማመጣቸውን ለመቀያየር እና እንደተፈለገው እየተንቀሳቀሱ የተለያዩ ተግባራትን ለማሰራት አመቺ ባለመሆኑ መምህራኑ የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካ እንዲሆን ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ተግባራትን ለማከናወን እንዳላስቻላቸው አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም መምህራኑ የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት እንደአስፈላጊነቱ የክፍሉን በርና መስኮት በመዝጋት፣ በመክፈት አሊያም እንደነበር በመተው ወዘተ.. ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንፃር ስድስቱም መምህራን እንደ አስፈላጊነቱ ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ አጥኝዋ መምህራኑ የሰጡትን ምላሽ መገንዘብ ከቻለች በኋላ በተተኳሪ መምህራኑ ላይ ለሶስት ተከታታይ ጊዜ ምልከታ አድርጋለች፡፡ ይህም የምልከታ ሂደት ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ ተቀምጧል፡፡

ሠንጠረዥ አስራ አምስት፡-ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግራባትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ምልከታው ያተኮረባቸው ተግባራት | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | - | - | - | |
| 6.1 | የመማሪያ ክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ለማድረግ መጣር | 2 | 33.3 | 4 | 66.6 |
| 6.2 | የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት እንደ አስፈላጊነቱ የክፍሉን በርና መስኮት በመዝጋት በመክፈት አልያም እንደነበረ በመተው ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታን መፈጠር | 2 | 33.3 | 4 | 66.6 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ በተተካሪ ትምህርት በቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመማርያ ክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ ምቹና የተደራጀ እንዲሆን የማድረግ ትግበራቸውን ማለትም በምዕራፍ ሁለት ገጽ 30 እንደተገለጸው ምቹ ሁኔታን መፍጠር ሲባል ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የግድግዳ ላይ ስዕሎች፣ ፖስተሮች መጠቀም፣ የክፍሉን

ንጽሕና መጠበቅ፣ በክፍል ውስጥ ንጹህ አየር እንዲኖር ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለመማር ማስተማሩ ስኬት ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ትግበራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሁለት መምህራን የተለያዩ መረጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጭውውቶችን በማቅረብ፤ በመማርያ ክፍል ውስጥ በቂ ንፁህ አየር እንዲገባ በማድረግ በተሻለ ደረጃ ተግባሩን አከናውነዋል፡፡ በአንፃሩ የተቀሩት አራት መምህራን ግን ተለምዷዊ በሆነ መንገድ ከማስተማራቸው ውጪ የመማርያ ክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ለማድረግ ሲተጉ አልተስተዋሉም፡፡

በተጨማሪም የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት እንደ አስፈላጊነቱ የክፍሉን በርና መስኮት በመዝጋት በመክፈት አለያም እንደነበረ በመተው ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታ መፍጠርን በተመለከተ ሁለት መምህራን ወደ ክፍል ገብተው ሰላምታ ከመስጠታቸው በፊት ቀዳሚ ተግባራቸው የክፍሉን መስኮቶች ተመልክተው እንደ አስፈላጊነቱ የመክፈት እና የመዝጋት ተግባራት አከናውነዋል፡፡ በአንፃሩ የተቀሩት አራት መምህራን ግን ወደ ክፍል ገብተው የክፍሎቹን በርና መስኮቶች በመዝጋትም ሆነ በመክፈት ንፁህ አየር እንዲገባ በማድረግ ምቹ ሁኔታን ሲፈጥሩ አልተስተዋሉም፡፡ ያም ባለመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ክፍሎቹ ከመታፈናቸው የተነሳ ክፍሉ ውስጥ የሚፈጠረው ጠረን የሚረብሽ እና ለተለያዩ በሽታዎች ሊዳርግ የሚችል፤ የመማር ተነሳሽነትን ሊቀንስ የሚችል መሆኑን በምልከታ ጊዜ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከምልከታ የተገኘው መረጃ መምህራኑ ከሰጡት ቃለመጠይቅ ጋር ሲነፃፀር በአብዛኛው የተለየ ነው፡፡ ይህም መምህራኑ በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ላይ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባራትን ማከናወናቸው የገለፁ ቢሆንም ከምልከታ የተገኘው መረጃ ግን ምንም እንኳን ጥቂት መምህራን በተቻላቸው መጠን የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሰካ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሲተጉ ቢስተዋሉም አብዛኞቹ ተተካሪ መምህራን ግን ለመማር ማስተማሩ ስኬት ምቹ ሁኔታዎችን ሲፈጥሩ አልተስተዋሉም፡፡

በሌላም በኩል የምህራኑ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ክህሎት በተመለከተ ለተጠኚ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆኑ የሰጡትን ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ አስራ ስድስት፡- ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባራትን ማከናወን በተመለከተ

ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ:

| ተ.ቁ | የክፍሉ አመራር ክንውን | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | ፈጽሞ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5.1 | የመማሪያ ክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ የተደራጁና ለመማር ማስተማር ሂደት የተመቹ እንዲሆኑ ትጥራ ለች/ይጥራል፡፡ | 10 | 6.6 | 16 | 10.6 | 14 | 9.3 | 49 | 32.6 | 61 | 40.6 |
| 5.2 | የዕለቱን ትምህርት ከመጀመሯ/ ሩ በፊት እንደ አስፈላጊነቱ የክፍሎቹን በርና መስኮቶች በመዝጋትና በመ ክፈት አልያም እንደነበር በመተው ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታን ትፈጥራለች/ ይፈጥ ራል፡፡ | 19 | 12.6 | 41 | 27.3 | - | - | 40 | 26.6 | 50 | 33.3 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያመለክተው ተተካሪ መምህራኑ የመማሪያ ክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ የተደራጀና ለመማር የተመቸ እንዲሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸታቸውን በተመለከተ 10 ተማሪዎች(6.6%) በጣም እንስማማለን፣ 16 ተማሪዎች (10.6%) እንስማማለን፣ 14 ተማሪዎች (9.3%) መወሰን ይቸግራል፣ 49 ተማሪዎች (32%) አንስማማም እና የተቀሩት 61 ተማሪዎች (40.6%) ደግሞ ፈፅሞ አለመስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት እንደ አስፈላጊነቱ የክፍሎቹን በርና መስኮቶች በመዝጋት በመክፈት አለያም እንደነበር በመተው ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ችሎታቸውን በተመለከተ 19 ተማሪዎች(12.6%) በጣም እንስማማለን፣ 41 ተማሪዎች (23.3%) እንስማማለን፣ 40 ተማሪዎች (26.6%) አንስማማም፣ 50 ተማሪዎች (33.3%) ፈፅሞ አንስማማም በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ ከቀረበው የተማሪዎች ምላሽ መረዳት የሚቻለው ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባራት ክንውን በተመለከተ የተተኳሪ መምህራኑ ትግበራ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ በአብዛኛው ከክፍል ምልከታ ከተገኘው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ከተተኳሪ መምህራኑ ቃለመጠይቅ የተገኘው ምላሽ በብዛት ከምልከታ ከጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው ምላሽ ጋር የተቃረነ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ምናልባትም መምህራኑ በስራቸው ላይ የሚፈጠር አሉታዊ ተፅእኖ ሊኖር ይችላል የሚል ስጋት አድሮባቸው ሊሆን ይችላል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.9. እንደተገለጸው ስኬታማ እና ታታሪ መምህር ምን ጊዜም መማሪያ ክፍሉን ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ በተጨማሪም በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.9. Underwood (1987፣46) እንደገለጹት የማስተማሪያ ክፍሎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ሳቢና አጓጊ እንዲሆን ለማድረግ ቀጥለው የቀረቡትን ሁነቶች ማሟላት አስፈላጊ ነው፡-

- ❖ የወንበሮቹ አቀማመጥ መምህሩን እና ተማሪዎችን እንደተፈለገው ሊያንቀሳቅስ የሚችሉ መሆን፣
- ❖ ድምፅን በቀላሉ ሊያሰማ የሚያስችል ክፍል፣
- ❖ ለመማር ምቹ የሆነ ንፁህ አየር የሚገባበት መማሪያ ክፍል፣
- ❖ ጥቁር ሰሌዳው ለተማሪውም ለአስተማሪውም በትክክል ለመጠቀም የሚያስችል፣
- ❖ የክፍሉ ሁኔታ እንደተፈለገው በቀላሉ መለወጥና ማስተካከል የሚያስችል፣
- ❖ ግድግዳዎቹ ፖስተሮችን እና ስእሎችን የመሳሰሉትን ሁሉ ለመለጠፍ የሚያስችል፣
- ❖ የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳው በክፍል ውስጥ መኖርና የመሳሰሉትን ሁሉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን አሟልቶ መገኘት የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ያደርገዋል Underwood (1987፡ 46)፡፡

በመሆኑም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ተጠኝ መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በተገቢው መንገድ እንደማያከናውኗቸው ከተማሪዎች ጽሑፍ መጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕስ 2.5.9. Underwood (1987) የጠቀስዋቸው አብዛኞቹ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባራት ተተኳሪ መምህራኑ ያለመተግበራቸው ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ የራሱን አስተያየት አስቀምጧል፡፡ ይህም ቀደም ሲል Underwood የጠቀስዋቸውን አብዛኞቹ ተግባራት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለትምህርት ቤቶቹ ተገቢውን ድጋፍ ካላደረጉ በስተቀር በተተኳሪ መምህራኑ አቅም ብቻ ሊዘጋጅና ሊተገበሩ የሚችሉ ባለመሆናቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ግኝቶች የሚጠቃለሉበት እና ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ለተነሳው መሠረታዊ ጥያቄ ግኝቶችን መሠረት ያደረገ መልስ በመስጠት የመፍትሔ ሀሳብ የሚሰነዝር ነው፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲስ አበባ መስተዳደር በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ትግበራቸው ምን እንደሚመስል መገምገም ነው፡፡ በተጨማሪም መምህራን በክፍል ውስጥ አመራር ችሎታቸው ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩባቸው ተላውጦዎች ምን እንደሆኑ መለየት፣ የችግሮቹ ምንጮች (መንስዔዎች) ምን ምን እንደሆኑ በመለየት ችግሮቹን መሰረት ያደረገ መፍትሔ ምን ሊሆን እንደሚችል ምላሽ ይሰጣል፡፡ ይኸውም፡-

- የተግባቦት ትግበራ፡- መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚኖራቸው የመግባባት ችሎታ በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥሩ የማስተማር ክንውን እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከዚህም አንፃር አብዛኞቹ ተተኳሪ መምህራኑ ምንም እንኳን የማስተማር ስልታቸው ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፍ የሚችል ባይሆንም በመማር ማስተማሩ ሂደት ግን ሁል ጊዜ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ የተማሪዎችን ሀሳብ የማዳመጥ ችሎታቸው እና ተማሪዎች ግልጽ ባልሆነላቸው ጉዳይ ላይ ከመምህሮቻቸው ማብራሪያ ሲፈልጉ ጥያቄዎቻቸውን በትህትና ተቀብለው ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ክህሎታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች እንዲፈርዋቸው የሚያደርጉ ቋንቋዎችን እንደማይጠቀሙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ተተኳሪ መምህራኑ የተግባቦት ችሎታቸው ከፍተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- የእቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር፡- የመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹና ተስማሚ እንዲሆን፣ የትምህርቱ ዓላማ ግቡን እንዲመታ ከሚያስፈልጉ እና በመምህራን በቀዳሚነት መከናወን ካለባቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ እቅድ የማውጣት ስራ ነው፡፡ ተተኪ መምህራኑ አስቀድመው ባዘጋጁት እቅድ ተንተርሰው የእለቱን ትምህርት የማስተማር ትግበራቸው እና ተማሪዎች የትኛውን ትምህርት ለምን አላማ እንደሚማሩ አውቀውት እንዲሄዱ የማድረግ ትግበራቸው ግን በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የተነሳሽነት ተግባራት፡- መምህራን የመማር ማስተማር ሂደታቸው የታቀደለት ዓላማ ላይ እንዲደርስ ለማድረግ ተነሳሽነት የመፍጠር ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህም አንፃር አብዛኞቹ ተተኪ መምህራን ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ተማሪዎችን ሊያነቃቁ የሚችሉ ምንም አይነት ማነሳሻ ተግባራት ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አማርኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር የማድረግ እና መማሪያ ክፍሉን የመማር ተነሳሽነትን ሊፈጥር በሚችልበት መልኩ የማስተካከል ተግባራትን ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች መልስ ለመመለስ ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ በሚያደርጉት ተሳትፎ መምህራኑ ስም እየጠሩ አያበረታቱም፡፡ ከዚህም አንጻር ተተኪ መምህራኑ የተነሳሽነት ተግባራት ክንውናቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- የቅጣት ተግባር፡- በመማር ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ ለሚፈጠሩ የሥነ ስርአት ችግሮች ለመከላከል እና ለመቆጣጠር መምህራን የተለያዩ የስነ ስርአት እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በተማሪዎች ላይ የሚወሰዱ አካላዊ ቅጣቶች፣

ከክፍል ማስወጣት፣ መምከር እና መሳደብ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የቅጣት አተገባበርን በተመለከተ ተተኪ ሪ መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ እንደተማሪ ሊያንፀባርቁት የሚገባ ባህሪ ምን መምሰል እንደለበት የማሳወቅ ትግበራቸው ዝቅተኛ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ሲያጠፉ ለምሳሌ የመማሪያ መጽሐፍ እና ደብተር ይዘው ባይገኙ፣ የቤትና የክፍል ስራ ባይሰሩ፣ ቢረብሹ ወዘተ. እንደላየ ሆኖ ከማለፍ ይልቅ መምህራኑ ተገቢ ነው ብለው የሚያስቡትን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ ተተኪ ሪ መምህራን የሚወስዳቸው እርምጃዎች ተማሪዎች ትምህርቱን አቋርጠው ከክፍል እንዲወጡ ማድረግ፣ ማንበርከክ፣ አልፎ አልፎ መማታት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ እርምጃዎች ደግሞ ተማሪዎችን ሊያርቁ (ሊያስተካክሉ) እና ሊያስተምሩ የሚችሉ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ተተኪ ሪ የመምህራኑ የቅጣት አሰጣጥ ትግበራቸው ዝቅተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- የመምራት ችሎታ፡- መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማሪዎች ምን ዓይነት ተግባር፣ መቼና እንዴ መሰራት እንዳለባቸው ግልጽ የሆነ መመሪያ መስጠት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም መምህራን ክፍል ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ በሙሉ በመቆጣጠር የመማር ማስተማር ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን የሚያስችል የአመራር ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህም አንፃር ተተኪ ሪ መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰርዋቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልጽ የሆነ መመሪያ የመስጠት ትግበራቸው ከፍተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ምንም አይነት ጥፋት ፈፅመው መገኘት የለባቸውም በሚል አቋማቸው መሳ ለመሳ (በመካከለኛ ደረጃ) ላይ እንደሚገኝ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላም በኩል መምህራኑ ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን እድል የመፍጠር ክህሎታቸው እና የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር በመቁጠር ችግሩን በውይይትና በምክክር ለመፍታት የመጣር ትግበራቸው በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የተተኪ ሪ መምህራኑ የመምራት ትግበራቸው ዝቅተኛ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

- ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባር፡- ለክፍል ውስጥ አመራር ስኬታማነት አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ የመምህሩና የክፍሉ አጠቃላይ ገፅታ አመቺነት ነው፡፡ በመሆኑም ስኬታማና ታታሪ መምህር ምን ጊዜም የመማሪያ ክፍሉን ለመማር ማስተማሩ ሂደት

ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ከዚህም አንፃር የተተኳሪ መምህራኑ አጠቃላይ የመማሪያ ክፍሉን ገፅታ ለምሳሌ የወንበሮቹን አደረጃጀት፣ የተማሪዎችን አቀማመጥ፣ የክፍሉን ንፅህና ወዘተ.. ለመማር ማስተማር ሂደቱ አመቺ በሆነ መልኩ የማደራጀት ብቃታቸውን እና የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት እንደ አስፈላጊነቱ የክፍሎቹን በርና መስኮቶች በመዝጋት፣ በመክፈት አሊያም እንደነበር በመተው ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባራትን አላከናወኑም። ተግባሩን ያለማከናወናቸው ምክንያትም አብዛኞቹ ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባራት በመምህራኑ አቅም ብቻ ሊተገበሩ የማይችሉ በመሆናቸው እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

**ተተኳሪ መምህራኑ በክፍል አመራር ክህሎታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩባቸው ተላውጦዎች መንስኤያቸው ምን ምን እንሆኑ በጥናቱ የተገኙት ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው::**

ተተኳሪ መምህራኑ ገና ከጅምሩ ወደ መምህርነት ሙያ ሲገቡና የአማርኛ ቋንቋ መምህር ሲሆኑ በምርጫቸውና በፍላጎታቸው አለመሆኑ፤ መምህራኑ የአመራር ችሎታቸውን ሊያዳብር የሚችል በክፍል ውስጥ አመራር አላባውያን ዙሪያ በቂ የሆነ ሥልጠና እና ትምህርት አለማግኘታቸው፤ የተተኳሪ መምህራኑ የማስተማር ልምድ ዝቅተኛ መሆኑ እና የትምህርት ባለድርሻ አካላት ለመማር ማስተማር ስኬት ሲሉ በተማሪዎች፣በአስተማሪዎች እና በትምህርት ቤቶቹ አጠቃላይ ገጽታ ላይ የበኩላቸውን ድርሻ በተገቢው መንገድ አለመወጣታቸው ተጠኝ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት በክፍል አመራር ክህሎታቸው ስኬታማ እንዳይሆኑ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳሳደሩባቸው ለመረዳት ተችሏል።

## 5.2. የመፍትሔ ሃሳቦች

በጥናቱ የተገኘው ውጤት መሰረት በማድረግ በአዲ አበባ መስተዳድር በተመረጡ ሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከክፍል አመራር ክህሎት አኳያ የሚታዩባቸውን ችግሮች በማስተካከል ለወደፊቱ በተሻለ ሁኔታ የክፍል አመራር ብቃታቸውን ያሻሽሉ ዘንድ ጥናቱ የሚከተለውን አስተያየት አቅርቧል። ይኸውም፡-

- መምህራን በተሰማሩበት የማስተማር ስራ ውጤታማና የተመሰገኑ ሊሆኑ የሚችሉት ከምንም በላይ ሙያቸውን ወደውና አክብረው ሲሰሩ ነው። ነገር ግን በዚህ ጥናት ላይ በተተኳሪ መምህራኑ ላይ የታየው ችግር ሙያውን ወደውት እና ፈልገውት እየሰሩበት እንዳልሆነ ነው። ሙያውን ሳይፈልገው እና ሳይወደው የሚያስተምር መምህር ደግሞ ቋንቋን መማር የሚፈልግ ብቁ ዜጋን ሊያፈራ አይችልም። በማስተማር ስራውም ውጤታማ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም። ስለዚህ መምህራን ከቻሉ በሙያው ውስጥ እስካሉ ድረስ ለተማሪዎች ፣ ለሙያው ክብርና እንዲሁም ለራሳቸው ሲሉ የተለያዩ መጻሕፍትን እና የምርምር ስራዎችን በማንበብ ሙያውን ለመውደድ ጥረት ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል።
- ያለ ስኬታማ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ የመማር ማስተማሩን ሂደት ከግብ ማድረስ እንደማይቻል ግልጽ ነው። ይህን ችሎታ ደግሞ እውን ማድረግ የሚቻለው መምህራን ለቋንቋ መምህርነት ሲሰለጥኑ ከትምህርት እውቀት ባሻገር ስለ መሠረታዊ የክፍል ውስጥ አመራር ምንነት እና አተገባበር ለመምህራን በቂ የሆነ ስልጠና ቢሰጣቸው፤
- ለየትምህርት ቤቶቹ በክፍል ውስጥ አመራር ዙሪያ የተጻፉ መጽሀፎች እና የምርምር ውጤቶች ቢቀርቡላቸው፣
- በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የቀረበውን ትምህርት በአንክሮና በትጋት እንዳይከታተሉ ወይም ችግር እንዲፈጠር ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መምህራን የማነሳሳትን ስራ ከትምህርት በፊት ተግባራዊ አለማድረጋቸው ነው። ይህ እንዳይሆን ደግሞ መምህራን የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት የተለያዩ የማነሳሻ ተግባራትን ማቅረብ አለባቸው። በተጨማሪም መምህራን ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት እንዲወዱት እና በትጋት እንዲከታተሉት የተለያዩ ምሁራን የጠቀስዋቸውን የማነሳሻ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት እንዲጨምር ማድረግ ቢቻል፣
- የመማር ማስተማሩን ክንውን ይበልጥ ስኬታማ ለማድረግ ባለድርሻ አካላት (የትምህርት ቢሮ ሰራተኞች፣ ርእሳነ መምህራን፣ መንግስት) የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች፣ ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራኑ አመቺ የሆኑ እንደተፈለገው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ እና ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፉ የሚችሉ የመማሪያ ወንበሮችን በማቅረብ ተማሪዎች የተሻለ የመማር ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ቢቻል፣

- መምህራን  የክፍል ውስጥ አመራር ክህሎታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉ ስልጠናዎች ቢሰጣቸው እና በክፍል ውስጥ አመራር ክህሎት ዙሪያ የተቃኙ ጥናታዊ ጽሑፎች እና መጻሕፍቶችን ማንበብ ቢችሉ፣
- ርእሳነ መምህራን በስነ ምግባራቸው ወጣ ያሉና  ከመምህራኑ አቅም በላይ በሆኑ ተማሪዎች ላይ  ተገቢ የሆነውን  የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ቢችሉ።

# ዋቢ ጽሑፎች


ሒሩት ካሳው፡፡(1997)፡፡ "በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር የሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሴት እና የወንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ንፅፅራዊ ጥናት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አበበ እስጢፋኖስ፡፡(2001)፡፡ "በሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የክፍል አመራር ብቃት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አንተነህ ውዱ፡፡(1998)፡፡ "በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚገኙ በአየር ጤና ትምህርት ቤት እና በኮከብና በእናት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሻለ የክፍል አመራር ያላቸው የትኞቹ ናቸው?" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

Adams, N.(1947). *Secondary Management.* Engugu: fourth Dimension publishing Company.Ltd.

Arends, J, R.(1997). *Classroom Instruction and Management.* New York: The Graw-Hill Company Inc.

Belln, and et al.(1992). *Teaching from A Research Knowledge Based A Development and Rnewal Process.* New York: Macmillan Publishing Company.

Best,G. and Kahn,V.(1993). *Research in Education.* (7th ed.) New Delhi: Printice Hall of Indiapr vate limited.

Borich, G.(1988). *Effective Teaching Methods.* New York: Longman Inc.

__________.(1980). *Effective Teaching Method.* New York: Macmillan Publishing Company.

Bress, P.(2000). "Gender Difference in Teaching Style" *From English Teaching.38/4,26-29.*

Brown ,B.1994. *Principles of Language Teaching and Learning.* New York: Print ice Hall Regents.

Charles, M.(1998). "Class Room Mangement" The *Successful Teacher.* The Low state University Press.

Clark, H. and Star, L.(1986). *Secondary and Middle School Teaching Method.* (5th Ed)New York: Macmillan Publishing Company.

Congelosi, James.(1997).*Classroom Management Strategies.* Longman: Longm an Publishing Compnay.

Cristison,M.(1994). *The Good Language Teachers in Teacher Development Making the Right Moves.* Washington DC: United States Information Agency.

Cruic Kshank,D.(1999). *The Act of Teaching.* Boston: Mc Graw- Hall Companies, Inc.

Dighton,L.(1991). *Encyclopedia of Education.* NP. Vol 2. The Macmillan: Company the Free Press.

Dimomock. (1993). *School Based Management and School Effectiveness.* New York: Roteidge.LTJ.

Doyle, Walter. (1980). *"Classroom Organization and Management".* Inmerinc it rock Hand Book of Research on Teaching a Project of American Education (3rd ed) New York: Macmiln Publication.

Elliot, and et al.(2000). *Effective Teaching. Educational Psychology (3rd ed).* USA: Mcgraw- Hall Higher Education.

Evertson,C. and et al.(1983). *Organizing and Managing the Elmenetary School Class room.* Austin Univesity of Texas: Research and Development center for Teacher education.

Edword, A. and Galloway.(1992). *Second School Teaching and Education Psychology.* New York: Longman Publishing Company.

Freeman, L. D and Long, MH.(1991). *An Introduction to 2nd. Language Acquisition Research.* Longman Group: UK. Limited.

Gebhard, G. Jerry.(1996). *Teaching English as a Foreign or as a Second Language* .New York: University of Michigan Publishing Company

Good, Thomas. L, Brophy, Jere, E.(1987). *Looking In Classroom.* New York : Harper and Rwo Publisher.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* London and New York: Longman Pulishing Company.

Jarolimek, J. Foster Cifford, D.(1997). *Teaching and Learning in Elementary School.* New Jersy: Printice Hall.

Montague, E.(1987). *Fundamentals of Secondary School Instruction.* Columbus: Merit Publishing Company.

Moore, Chores.(1982). "Classroom Management". *The Success Teacher.* Editor Jams L- Kelly.The Low State University Press.

___________.(2001). *Classroom Teaching Skills.*(5th ed.)New York: Mc Graw Hill Inc.

Rinne,H.(1997).*Excellent Classroom Management.* New York: Weds Worth Publishing Company Milan.

Underwood, May.(1987).*Effective Class Management.* London: Longman Publisher Company.

Whitaker,P.(1995). *Managing To Learn.* New York: Longman Publishing Com pany.

Wolfagang, C.(2005).*Solving Discipline and Classroom Management.* (6th ed.) New York: John Wiley and Sons Inc.

Wright, T.(1987). *Roles of Teaching and Learner.* Oxford: Oxford University Press.

# አባሪዎች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አባሪ አንድ

# የምልከታ መከታተያ ሰነድ

አጋዥ ምልከታ አድራጊዎቹ ለምልከታ ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት የቀረበላቸውን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ የሚሞሉት የመምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ለመፈተሽ የተዘጋጀ የምልከታ መከታተያ ሰነድ /observation cheek list/

የሚያስተምሩበት ት/ቤት ስም -------------------------- ምልከታው የተካሄደበት ቦታ-------------

ክፍል/ሴክሽን ---------------------------- የምዝገባው የተደረገበት ቀን--------------

ፆታ፡- ወንድ ---------- ክፍለ ጊዜ ---------------------------------

ሴት ---------- የአገልግሎት ዘመን ---------------------

በሳምንት የሚያስተምሩት ክፍለ ጊዜ ---------------------------------------------------

ትምህርቱ የተጀመረበትና የተጠናቀቀበት ሰአት -------------------------------------

የተማሪዎች ብዛት -----------------------

**የመመዘኛ መግለጫ**

1. ተከናውኗል 2. አልተከናወነም

| ተ.ቁ | 1. ማቀድ | ታከናውናለች/ ያከናውናል | አታከናውንም/ አያከናውንም |
|---|---|---|---|
| 1.1 | የአጭርና የረዥም ጊዜ እንዲሁም የመንፈቅ ዓመት እቅድ አስቀድሞ በማዘጋጀት ማቅረብ፣ | | |
| 1.2 | ምን ለምን አላማ እንደሚያስተምር አስቀድሞ ለተማሪዎች ግልፅ ማድረግ፣ | | |
| 1.3 | አስቀድሞ በተዘጋጀው እለታዊ እቅድ መሰረት ማስተማር፣ | | |
| 2. | የተነሳሽ ተግባር | | |
| 2.1 | የእለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ሁሉንም | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተማሪዎች ሊያሳትፉ የሚችሉ ልዩ ልዩ የማነሳሻ ተግባራት ማከናወን፣ | | |
| 2.2 | በተለያየ ምክንያት አማርኛ ቋንቋ ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነት | | |
| 2.3 | የመማሪያ ክፍሉ ንፅህና፣ የመማር ተነሳሽነትን እንዲጨምር ማድረግ፣ | | |
| 2.4 | የወንበሮቹ አቀማመጥ የመማር ተነሳሽነትን እንዲጨምር ማድረግ፣ | | |
| 2.5 | ተማሪዎች መልስ በመለሱም ሆነ ጥያቄ በጠየቁ ቁጥር ስማቸውን በመጥራት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ | | |
| 3 | የተግባቦት ተግባር | | |
| 3.1 | መምህሯ/ሩ ሁል ጊዜ ተናጋሪ ብቻ ሳትሆን/ይሆን የተማሪዎችንም ሀሳብ ማዳመጥ፣ | | |
| 3.2 | ተማሪዎች ባገባቸው ሀሳብ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብሎ ማስተናገድ፣ | | |
| 3.3 | ተማሪዎች እንዲፈሯት/እንዲፈሩት የሚያደርግ ቋንቋ በመጠቀም መቅረብ፣ | | |
| 3.4 | የመምህሯ/ሩ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ሊያሳትፉ የሚችል መሆኑ፣ | | |
| 4 | የቅጣት ተግባር | | |
| 4.1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ሊያንፀባርቁት የሚገባ ባህሪ ምን መምሰል እንዳለበት ማስታወስ፣ | | |
| 4.2 | ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ (የቤት ስራ ባይሰሩ፣ መጽሐፍ ባያመጡ) ተገቢ የሆነ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እንዳላየ ሆኖ ማለፍ፣ | | |
| 5 | የመምራት ችሎታ | | |
| 5.1 | የተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሆኖ ከክፍል ውጭ ለሚያከናውናቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልፅ የሆነ መመሪያ መስጠት፣ | | |
| 5.2 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምንም አይነት ስህተት ፈፅመው እንዲገኙ አለመፈለግ፣ | | |
| 5.3 | የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር በመቁጠር ችግሩን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት መጣር፣ | | |
| 5.4 | ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ እንዲያጎለብቱ (እንዲያዳብሩ) እድል መስጠት፣ | | |
| | ምቹ ሁኔታን መፍጠር | | |
| 6.1 | የመማሪያ ክፍሉ አጠቃላይ ገፅታ ምቹና የተደራጀ እንዲሆን ለማድረግ መጣር፣ | | |
| 6.2 | የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት እንደ አስፈላጊነቱ የክፍሉን በርና መስኮት በመዘጋት/በመክፈት አሊያም እንደነበረ በመተው ወዘተ. ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፡፡ | | |

## አባሪ ሁለት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

### በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

**ውድ ተማሪዎች፡**

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ በሚመለከት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእናንተን ቀና ትብብር ሲታከልበት በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቅንነት ተመልክታችሁ ትክክለኛ ምላሽ እንድትሰጡኝ ስጠይቅ የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናትና ምርምር ጉዳይ ብቻ የሚውል መሆኑን በትህትና አረጋግጣለሁ፡፡

ውድ የሆነ ጊዜህን/ሽን በመስዋት ይህንን መጠይቅ በመሙላት ስለተባበርሸኝ/ከኝ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናዬና አቀርባለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡**

- በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም
- መጠይቁን በሌላ ሰው ማስሞላት አይቻልም

**ክፍል አንድ**

መመሪያ 1፡ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክለኛውን መልስ ስጪ/ጥ

1.1 ፆታ
  ወንድ -------------------
  ሴት ---------------------
1.2 እድሜ-------------------
1.3 የምትማርበት/ሪበት/ ትምህርት ቤት ስም -------------------------

ክፍል ሁለት

መመሪያ ሁለት፡- ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች አምስት አማራጮችን ይዘዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ አንድ ብቻ ነው፡፡ ጥያቄዎቹን በማንበብ ትክክለኛ መልስ ነው ብለሽ/ ብለህ የምታስቢውን/ በውን መመዘኛ መርጠሽ/ህ በሳጥኑ የ "✓" ምልክት በማድረግ መልሽ/ስ፡፡

የመመዘኛ መግለጫዎች

1. በጣም እስማማለሁ 2. እስማማለሁ 3. መወሰን ይቸግረኛል

4. አልስማማም 5. ፈፅሞ አልስማማም

| ተ.ቁ | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ይቸግረኛል | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተነሳሽነት ተግባር | | | | | |
| 1.1 | የእለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ የሚችል ልዩ ልዩ የመነሳሻ ተግባራት ታከናውናለች/ያከናውናል፡፡ | | | | | |
| 1.2 | በተለያየ ምክንያት አማርኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎችን በመለየት የመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው ሁኔታዎችን ታመቻቻለች/ያመቻቻል፡፡ | | | | | |
| 1.3 | የመማሪያ ክፍሉ ንፅህናን እንድንጠብቅ የሚያስችል ምክር በመለገስ ሁኔታዎችን ታመቻቻለች/ያመቻቻል፡፡ | | | | | |
| 1.4 | የወንበሮቹ አቀማመጥ የመማር ተነሳሽነትን እንዲጨምርልን ሁኔታዎችን ታመቻቻለች/ ያመቻቻል፡፡ | | | | | |
| 2 | የተግባቦት ተግባር | | | | | |
| 2.1 | መምህራችሁ ምንጊዜም ተናጋሪ ብቻ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሳትሆን/ይሆን የተማሪዎችን ሀሳብ ታዳምጣ ለች /ያዳምጣል፡፡ | | | | | |
| 2.2 | ተማሪዎች ባልገባቸው ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ በትህትና ተቀብላ/ብሎ ተገቢውን ምላሽ ትሰጣለች/ ይሰጣል፡፡ | | | | | |
| 2.3 | ተማሪዎች እንዲፈሯት/ፈሩት የሚያደርግ ቋንቋ በመጠቀም መቅረብ፣ | | | | | |
| 2.4 | የመምህሯ/ሩ የማስተማር ስልት ተማሪዎችን በተለያየ ክፍል ውስጥ የግባቦታዊ ተግባራት የሚያሳትፉ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 3 | የቅጣት ተግባር | | | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች እንደ ተማሪ ክፍል ውስጥ ሊያንፀባርቁት የሚገባቸውን ባህሪ ምን መምሰል እንዳለበት አስቀድማ/ሞ ለማስታወስ ትሞክራለች/ይሞክራል፡፡ | | | | | |
| 3.2 | ተማሪዎች ጥፋት ሲያጠፉ ጥፋተኛውን ለብቻ ለይታ/ቶ ምክር ከመለገስ ይልቅ በጅምላ (ሁሉንም ተማሪ) ትቀጣለች/ ይቀጣል፡፡ | | | | | |
| 3.3 | ተማሪዎች ማንኛውንም ጥፋት ሲያጠፉ ለምሳሌ፡- (የቤት ስራ ባይሰሩ፣ መጽሐፍ ባያመጡ፣ ቢረበሹ/ ተገቢ የሆነ ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እንዳላየች/የ በቸልታ ታልፋለች/ ያልፋል፡፡ | | | | | |
| 4 | የመምራት ችሎታ | | | | | |
| 4.1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰርዋቸው ትምህርታዊ ተግባራት ግልፅ የሆነ መመሪያ አስቀድማ/ሞ ትሰጣለች/ይሰጣል፡፡ | | | | | |
| 4.2 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ምንም አይነት ጥፋት እንዲያጠፉ አትፈልግም/አይፈልግም፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.3 | ሁሉንም ነገር እኔ ላርም ከማለት ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበትን መንገድ እንዲያጎለብቱ (እንዲያዳብሩ) እድል ትሰጣለች/ ይሰጣል። | | | | | |
| 4.4 | የተማሪዎችን ችግር እንደራስ ችግር ቆጥራ/ሮ ችግራቸውን በፍጥነት በውይይትና በምክክር ለመፍታት ትጥራለች/ይጥራል። | | | | | |
| 5 | ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ተግባር | | | | | |
| 5.1 | የመማሪያ ክፍሉን አጠቃላይ ገፅታ ለመማር የተመቹና የተደራጀ እንዲሆኑ ትጥራለች/ ይፈጥራል። | | | | | |
| 5.2 | የዕለቱን ትምህርት ከመጀመርሯ/ሩ አስቀድሞ /ማ እንደ አስፈላጊነቱ የክፍሎቹን በርና መስኮቶች በመዝጋት/በመክፈት አልያም ለመማር ማስተማሩ ሂደት ምቹ ሁኔታን ትፈጥራለች/ ይፈጥራል። | | | | | |

መመሪያ ሶስት፡- ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብበህ/ሽ በክፍት ቦታዎቹ ላይ

የራስሽን/ሽን አጠር ያለ አስተያየት ስጪ/ስጥ

1. አማርኛ ቋንቋ ለመማር ፍላጎት አለሽ/ህ ------------------------------------------
ለምን ---------------------------------------------------------------------------
---------------------------------------------------------------------------------
---------------------------------------------------------------------------------
2. በክፍል ውስጥ ጥፋት ስታጠፋ/ፊ መምህርህ/ሽ ለማስተካከል የምትጥረው/የሚጥረው በምን መልኩ ነው? ______________________________________________
_____________________________________________________________________
_____________________________________________________________________
3. መምህራችሁ የእለቱን ትምህርት ከመጀመሯ/ሩ በፊት ትምህርቱን ለምን አላማ እንደምትማሩ አስቀድሞ/ማ ታሳውቃችኋለች/ያሳውቃችኋል? ---------------------------
አዎ ካልክ/ሽ እንዴት ?__________________________________________________
_____________________________________________________________________
_____________________________________________________________________
4. መምህራችሁ በመማር ማስተማር ሂደት የምትወያዩበትና የምትከራከሩበትን ተግባራት በክፍል ውስጥ ታቀርባለች/ያቀርባል?__________አዎ ካልሽ/ካልክ ምን አይነት ተግባራት? ______________________________________________________
_____________________________________________________________________
_____________________________________________________________________

5. መምህራችሁ አማርኛ ቋንቋ ለመማር ተነሳሽነት እንዲያድርባችሁ የምትጠቀመው/ የሚጠቀመው የማስተማር ስልት ምን ይመስላል?_______________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________

6. በክፍል ውስጥ ጥፋት ስታጠፉ አስተማሪያችሁ ምን አይነት የቅጣት እርምጃ ትወስዳለች/ ይወስዳል-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

7. በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪዎች አቀማመጥ ምን አይነት ነው?--------------------------------------------------------------ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ ነው?----------------ለምን?------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

8. ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ መልስ ለመመለስ፣ ከተማሪዎች ጋር እርስ በርስ ለመወያየት የሚያስችል እድል መምህራችሁ ትሰጣችኋለች/ ይሰጣችኋል?-------------------------------

9. በአጠቃላይ ስለመምህራችሁ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ድክመትና ጥንካሬ ምን አይነት አስተያየት አላችሁ?

   ሀ. ጠንካራ ጎን __________________________________________________________________________________________________________

   ለ. ደካማ ጎን __________________________________________________________________________________________________________

# አባሪ ሶስት

**ክፍል ሶስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዶ ቦታዎችን በመሙላትና አስተያየት በመስጠት ለተጠየቁት መረጃዎች ትክክለኛ መልስ ይስጡ።**

1. ወደ መምህርነት ሙያ የገቡት ፈልገው ነው?------------------
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት በምርጫዎ ነው?-------------
3. በአሁኑ ሰዓት የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመሆንዎ ደስተኛ ነዎት? -------
   ለምን?________________________________________________
   ________________________________________________
4. መሠረታዊ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታዎን ሊያዳብር የሚችል ትምህርት አሊያም ስልጠና ወስደዋል?________________________________
5. ስነ ስርዓት የሚያከብሩ፣ የሚያረፍዱ፣ የሚቀሩ፣ የቤትና የክፍል ስራ የማይሰሩ፣ መጽሐፍና ደብተር የሚያመጡ፣ የሚረብሹ ተማሪዎችን በምን መልኩ ለማስተካከል ይሞክራሉ? ________________________________
   ________________________________________________
6. ሁሉም ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ መንገድና መሣሪያዎች አሉ?-------------ካሉ ምን ምን ናቸው?
7. በክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ ተማሪ መራሽ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ? አዎ ካሉ ምን በማድረግ?________________________________
   ________________________________________________
8. የመማሪያ ክፍሉ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ እንዲሆን የሚያከናውኑት ተግባር አለ?-----------------ካለ ይግለጹ ________________________
   ________________________________________________
   ከሌለ ምክንያት ይግለጹ ________________________________
9. የተማሪዎች አቀማመጥ ምን ይመስላል? --------------------ለመማር ማስተማሩ እና ለክፍል ውስጥ ሂደቱ አመቺ ነው?________________________________
10. ክፍል ውስጥ ገብተው የእለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት የሚያከናውኑት ተግባር ምንድነው?

11. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እስካሉ ድረስ ምንም አይነት ጥፋት ፈፅመው መገኘት የለባቸውም የሚል አቋም አለዎት? ______________________

12. ተማሪዎች ለሚሰርዋቸው ስራዎች አስቀድመው ግልጽ የሆነ መመሪያ ይሰጥዋቸዋል? ______________________

13. በእቅድ የተመሠረተ ትምህርት ተግባራዊ ያደርጋሉ? ______________________

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ መሆኑን እና በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ____________________ ፊርማ ______________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አዲስ አበባ

ግንቦት 2004 ዓ.ም